# መቐለ ዩኒቨርሲቲ

## የሕብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

## (አማርኛን) በተግባራዊ ሥነልሳን ማስተማር

## የድሕረ-ምረቃ መርሐ-ግብር

በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፎች የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት ግምገማ

(ከተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ RBT 2001 እይታ አንፃር)

**በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ማስተማር**

**ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪ በከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት**

**በ**

**ተስፋይ ካሕሳይ**

**መቐለ ዩኒቨርሲቲ**

2018 ዓ.ም

# “በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፎች የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት ግምገማ”

(ከተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ 2001 ስርጭት እይታ አንፃር)

## መቐለ ዩኒቨርሲቲ

## የሕብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

## ድሕረ ምረቃ መርሀ ግብር

## በተግባራዊ ሥነልሳን አማርኛን ማስተማር

## ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪ በከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

**በ**

**ተስፋይ ካሕሳይ**

**አማካሪዎች**

**ዶክተር ተክለሐይማኖት ገብረፃዲቅ**

**አቶ ተስፋይ ሞላ**

**መቐለ ዩኒቨርሲቲ**

2018 ዓ.ም

# መቐለ ዩኒቨርሲቲ

## የሕብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል


## አማርኛን በተግባራዊ ሥነልሳን ማስተማር

## የድሕረ-ምረቃ መርሐ-ግብር

"በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፎች የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት ግምገማ

(ከተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ (RBT 2001) እይታ አንፃር)"

በ


ተስፋይ ካሕሳይ


የማረጋገጫ ፊርማ (Approval sheet)

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ______________________ | __________________ |
| አማካሪ | ፊርማ |
| ______________________ | __________________ |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |
| ______________________ | __________________ |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |
| ______________________ | __________________ |

# የባለቤትነት መግለጫ

እኔ ተስፋይ ካሕሳይ አብራሐ፣ cssl/ps0121/10፣ በመቐለ ዩኒቨርሲቲ የሕብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የአማርኛ ዲፓርትመንት ተማሪ በመሆኔ፣ ይህን ጥናት በርእስ "በ2008 ዓ/ም ታትመው ስራ ላይ ባሉ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፎች ውስጥ ያሉ የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀትን ከተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ (RBT, 2001) የዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት እይታ አኳያ መገምገም።" የተመራማሪው የመጨረሻ የጥናት ውጤት እንደሆነ እመሰክራለሁ።

የመግለጫ ይዘቶች፡-

1. ይህ ጥናት ሙሉ በሙሉ የእኔ ስራ ነው።
2. ከሌሎች ምንጮች የተወሰዱ ይዘቶች በትክክለኛ ማጣቀሻ (citation) እና በማጣቀሻ ዝርዝር (reference list) ተጠቅሰዋል።
3. የፕላጃሪዝም (plagiarism) ምንም ዓይነት ችግር የለበትም።
4. ይህ ጥናት ቀደም ሲል ለሌላ ዲግሪ ወይም የትምህርት ዓላማ አልቀረበም።
5. የጥናቱ ውጤት በትክክል የተተነተነ እና በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ ነው።
6. ሁሉም ስነ ምግባራዊ መስፈርቶች (የተሳታፊዎች ፈቃድ፣ የመረጃ ሚስጥራዊነት፣ የማጣቀሻ ትክክለኛነት) ተከብረዋል።

የአጥኚው ፊርማ፦________________________________

ሙሉ ስም፦________________________________

ቀን፦________________________________

# ምስጋና (Acknowledgement)

በመጀመሪያ ይህን ጥናት ለማጠናቀቅ ጥንካሬ፣ ጥበብ ፣ጤና እና ጊዜ ሰጥቶ እዚህ ላደረሰኝ ልኡል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይድረሰው። ሲጨንቀኝ አጽናንተው፣ሲያመኝ አረጋግተው ሞራል ሰጥተው ቀለምና ስነ ምግባር ትህትናን አስንቀው ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ በታላቅ ትዕግስት፣ በባለሙያነት እና በወቅታዊ ግብረ-መልስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ይህን ጥናት እንዳጠናቅቀው ላደረጉኝ ልዩ ምስጋናዬን ለአማካሪዬ ለክቡር *ዶክተር ተክለሐይማኖት ገብረፃዲቕ* እገልፃለሁ። እንዲሁም ለአጋዥ አማካሪዬ አቶ ተስፋይ ሞላ አመሰግኖታለሁኝ! ውድ ወንድሜም፣ ጓደኛዬም ዶክተር ገብረስላሴ ተስፋይ ሞያዊ ክህሎትህን አበርክተህልኛል እና ኑርልኝ! የመጠይቅ ጥያቅዬዎችን እና የትንተና ውጤቶችን በመገምገምና በማስተካከል ሙያዊ ክህሎታቸውን ላበረከቱልኝ መምህር መለስ እና መምህር ንጉስ ሕሉፍ ከልብ አመሰግናለሁኝ። እና ትንተናውለውዱ ወላጅ እናቴ እንዳባት እንደናት ሳይሰለቻት አውሁንም ድረስ ድጋፏ እና ፍቅሯ ያልነፈገችኝ ወ/ሮ መድህን በርሀ ልዩ ምስጋና አቀርባለሁ። በትምህርት መንገዴ ሁሉ ላሳየሽኝ ድጋፍ፣ ተስፋ እና ፍቅር ያላንቺ ይህ ሥራ አይጠናቀቅም ነበር። ሲደክመኝ አበርትተሽ፤ ሲደብረኝ አዝናንተሽ፤ ተስፋ ሰጥተሽ ሲጨንቀኝ ተጨንቀሽ፤ ከጎኔ ቁጭ ብለሽ፤ ጥናቱ እንዲጠናቀቅ ላደረግሺው ሁሉ ውዱ ባለቤቴ ኪሮስ ታደል ክብር ምስጋና ይገባሻል! ይኸው ተጠናቀቀ ውዴ! ለክፍል ጓደኞቼ፣ ለስራ ባልደረቦቼ እና ቃለ-መጠይቅ ያደረጉት አንድ የመጽሐፍ አዘጋጅ እና የዓይደር አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የክፍሉ መምህራን እጅግ አመሰግናለሁ። ምክንያቱም ጊዜያቸውን፣ ልምዳቸውን እና አስተያየታቸውን በተከፈተ ልብ ስለሰጡኝ። በመጨረሻም፣ ለመቐለ ዩኒቨርሲቲ ቤተ-መፃሕፍት፣ ለዓይደር አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን እና አስተዳደር ላደረጋችሁልኝ የገንዘብና ሞራል ድጋፍ ከልብ አመሰግናለሁኝ። ይህ ሥራ የብዙዎች ድጋፍ ውጤት ነው። ሁሉም የተጠቀሱም ሆኑ ያልተጠቀሱ እጅግ አመሰግናለሁ!

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

**የማረጋገጫ ፊርማ** (Approval sheet) ................................... i

**የባለቤትነት መግለጫ** ............................................. ii

**ምስጋና** (Acknowledgement) .......................................iii

**ማውጫ** ........................................................... iv

**የሰንጠረዥ ዝርዝር** ............................................. viii

**ስዕላዊ መግለጫ** ................................................... ix

**የምህፃረ ቃላት ዝርዝር** ........................................... x

***አጠቃሎ (Abstract)*** ......................................... xi

**ምዕራፍ አንድ፦ መግቢያ** ........................................... 1

1.1 **የጥናቱ ዳራ** ........................................................... 1

1.2 **የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት** ................................................ 4

1.3 **የጥናቱ ዓላማ** ........................................................ 5

*1.3.1 **አጠቃላይ ዓላማ** ...................................................... 5*

***ዝርዝር ዓላማዎች*** ...................................................... *5*

1.4 **የጥናቱ ጠቀሜታ** .................................................... 6

1.5 **የጥናቱ ወሰን**........................................................... 7

1.6 **የጥናቱ ውሱኑነት**....................................................... 8

1.7 **በጥናቱ የቃላት አጠቃቀም ፍቺዎች** (working definition) ................. 9

**ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት**....................................... 11

2.1 **ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት** ............................................. 11

2.1.1 **የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምንነት** ..........................................11

*2.1.2 **የቋንቋ መማሪያ መጽሐፎች ተገቢነት** ....................................12*

*2.1.3 **የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ግምገማ አስፈላጊነት**...........................12*

*2.1.4 **የአምዳዊ አደረጃጀት ምንነት**............................................14*

*2.1.5 **አምዳዊ አደረጃጀት ተገቢነት በቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ ግምገማ አጠቃላይ እይታ** ..............................................................15*

*2.1.6 በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አምዳዊ አደረጃጀት ቁልፍ መርሆዎች.........16*

*2.1.7 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፎች በአምዳዊ አደረጃጀት ሲገመገሙ...........17*

*2.1.8 ተለጣጣቂነት (Content Coherence) እና ተከታታይነት (content continuity) ..........................................................................18*

*2.1.9 ብሉምስ ታክሶኖሚ (Bloom's Taxonomy 1956)......................19*

*2.1.10 የተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ ቲኦሪ (RBT,2001) .................21*

2.2 የተዘማጅ ጥናቶች ቅኝት .......................................................25

**ምዕራፍ ሶስት የአጠናን ዘዴ ........................................... 28**

3.1 የጥናት ስልት .....................................................................28

3.2 የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች..............................................29

*3.2.1 ሰነድ ፍተሻ........................................................................30*

*3.2.2 ቃለ መጠይቅ.....................................................................30*

3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ.........................................................31

*3.3.1 የክፍል ደረጃና የመጽሐፍ አመራረጥ.....................................31*

*3.3.2 የመጽሐፉ አዘጋጆች ናሙና አመራረጥ..................................32*

*3.3.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ.............................................32*

3.4 የመረጃ ምንጮች ..................................................................33

3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ..........................................................33

**ምዕራፍ አራት፦ የመረጃ ትንተና ..................................... 36**

4.1 የክሂሎች ዓምዳዊ ይዘት ትንተና በ9ኛ ክፍል መጽሐፍ ከRBT ስርጭት አኳያ .......................................................................................36

*4.1.1 በ9ኛ ክፍል የማንበብ ክሂል ይዘቶች ትንተና .............................37*

*4.1.2 በ9ኛ ክፍል የማዳመጥ ክሂል ይዘቶች ትንተና............................40*

*4.1.3 በ9ኛ ክፍል የመፃፍ ክሂል ይዘቶች ትንተና...............................43*

*4.1.4 በ9ኛ ክፍል የመናገር ክሂል ይዘቶች ትንተና .............................45*

*4.1.5 ማጠቃለያ ዓላማ አንድ (9ኛ ክፍል መጽሐፍ)............................47*

4.2 የክሂሎች ዓምዳዊ ይዘት ትንተና በ10ኛ ክፍል መጽሐፍ የRBT ስርጭት ...49

*4.2.1 የማንበብ ክሂል ይዘቶች ትንተና በ10ኛ ክፍል............................49*

*4.2.2 የማዳመጥ ክሂል ይዘቶች ትንተና የRBT ስርጭት........................52*

*4.2.3 የመፃፍ ክሂል ይዘቶች ትንተና............................................54*

*4.2.4 የመናገር ክሂል ይዘቶች ስርጭት ........................................55*

*4.2.5 ማጠቃለያ ዓላማ ሁለት 10ኛ ክፍል ......................................57*

4.3 በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል መካከል ያለው ዓምዳዊ አደረጃጀት (RBT) ስርጭት .58

*4.3.1 መሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች እና ተከታታይነት በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል መካከል .....................................................................59*

*4.3.2 ከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎች እና ተለጣጣቂነት በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል መካከል .....................................................................60*

*4.3.3 በክሂሎች መካከል የተግባራት ምጥጥን እና ተከታታይነት...............60*

*4.3.4 ተለጣጣቂነት እና የመሰረታዊ ደረጃዎች ተከታታይነት.................61*

*4.3.5 ማጠቃለያ ዓላማ ሶስት...................................................62*

4.4 የቃለ መጠይቅ ትንተና ......................................................65

*4.4.1 ከመጽሐፍ አዘጋጅ የተገኘ መረጃ........................................65*

*4.4.2 ከመምህራን የተገኘ መረጃ.................................................66*

*4.4.3 የሶስቱ መረጃዎች ውህደት (Triangulation) ............................67*

**ምዕራፍ አምስት፦ማጠቃለያ እና መፍትሔ ሐሳቦች.................... 69**

5.1 ማጠቃለያ..............................................................69

5.2 መፍትሔ ሐሳቦች ........................................................71

**ዋቢዎች ........................................................... 74**

**አባሪዎች ......................................................... 79**

አባሪ 1 የማንበብ ክሂል 9ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ ..........................79

አባሪ 2 የማዳመጥ ክሂል 9ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ ..........................80

አባሪ 3 የመፃፍ ክሂል 9ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ ............................81

አባሪ 4 የመናገር ክሂል 9ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ ............................81

አባሪ 5 የማንበብ ክሂል 10ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ .........................82

አባሪ 6 የማዳመጥ ክሂል 10ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ ........................83

አባሪ 7 የመፃፍ ክሂል 10ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ...........................83

አባሪ 8 የመናገር ክሂል 10ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ .........................84

አባሪ 9 ከምዕራፍ 1-10 ድምር ውጤት አራቱም ክሂሎች 9ኛ ክፍል...........................85

አባሪ 10 ከምዕራፍ 1-10 ድምር ውጤት አራቱም ክሂሎች 10ኛ ክፍል ........................86

አባሪ 11 የማንበብ ክሂል ተግባራት ትንተና 9ኛ ክፍል መጽሐፍ ..................................87
አባሪ 12 የማንበብ ክሂል ተግባራት ትንተና 9ኛ ክፍል መጽሐፍ ..................................93
አባሪ 13 የመናገር ክሂል ተግባራት ትንተና 9ኛ ክፍል መጽሐፍ.................................100
አባሪ 14 የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ትንተና 9ኛ ክፍል መጽሐፍ ...............................105
አባሪ 15 የማንበብ ክሂል ተግባራት ትንተና 10ኛ ክፍል መጽሐፍ................................109
አባሪ 16 የመፃፍ ክሂል ተግባራት ትንተና 10ኛ ክፍል መጽሐፍ .................................114
አባሪ 17 የመናገር ክሂል ተግባራት ትንተና 10ኛ ክፍል መጽሐፍ ................................118
አባሪ 18 የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ትንተና 10ኛ ክፍል መጽሐፍ..............................124
አባሪ 19 ለ9ኛ እና 10ኛ ክፍል ትግርኛ ቋንቋ መጽሐፍ አዘጋጆች የተዘጋጀ ከፊል ነፃ ቃለ መጠይቅ ..........................................................................129
አባሪ 20 ለትግርኛ ቋንቋ መምራህን የተዘጋጀ ከፊል ነፃ ቃለ መጠይቅ ...........................132
አባሪ 21 በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ መምህራን መግለጫ........................................135
አባሪ 22 በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ የመጽሐፍ አዘጋጅ መግለጫ ................................136

# የሰንጠረዥ ዝርዝር


ሰንጠረዥ 4.1.1 .......... 37
ሰንጠረዥ 4.1.2 .......... 40
ሰንጠረዥ 4.1.3 .......... 43
ሰንጠረዥ 4.1.4 .......... 45
ሰንጠረዥ 4.2.1 .......... 49
ሰንጠረዥ 4.2.2 .......... 52
ሰንጠረዥ 4.2.3 .......... 54
ሰንጠረዥ 4.2.4 .......... 56
ሰንጠረዥ 4.3 ሀ .......... 59
ሰንጠረዥ 4.3 ለ .......... 59

# ስዕላዊ መግለጫ

ሰእል 2.1.8 LOTS እና HOTS........................................................ 19
ስእል 2.1.9 የ1956ቱ BT ........................................................... 20
ስእል 2.1.10 (RBT 2001) ........................................................ 22
5ስእል 2.1.10 ሀ Knowledge Dimension ......................................... 24

# የምህፃረ ቃላት ዝርዝር

| ምህፃረ ቃል | ሙሉ ቃል | ትርጉም |
|---|---|---|
| A3 | Apply | መተግበር |
| A4 | Analyze | መተንተን |
| C6 | Create | መፍጠር |
| E5 | Evaluate | መገምገም |
| HOTS | Higher-Order Thinking Skills | ከፍተኛ የማሰብ ደረጃዎች |
| LOTS | Lower-order Thinking | መሰረታዊ የማሰብ ደረጃዎች |
| R1 | Remembering | ማስታወስ |
| RBT | Revised bloom’s Taxonomy | የተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ |
| U2 | Understand | መረዳት |

# አጠቃሎ (Abstract)

*ይህ ጥናት በ2008 ዓ.ም. በኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር የታተሙና በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በመደበኛ ትምህርት ቤቶች እና በርቀት ትምህርትቤቶች ስራ ላይ የዋሉ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ የተማሪ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ያሉ የቋንቋ ክህሎት ተግባራት ዓምዳዊ አደረጃጀት (vertical alignment) ከተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ (Revised Bloom's Taxonomy – RBT, Anderson & Krathwohl, 2001) እይታ አንፃር መገምገም ዋና ዓላማ አድርጎ ወስዷል። የጥናቱ ስልት ተጋናኝ ትይዩ ቅይጥ ዘዴ (convergent parallel mixed-methods design) ተጠቅሟል። በመር የይዘት ትንተና (directed content analysis) በጠቅላላ 779 ተግባራት (9ኛ ክፍል 407፣ 10ኛ ክፍል 372) በ Anderson & Krathwohl (2001) መሰረት ተመድበው ተተንትነዋል፤ በተጨማሪም በዓላማ ተኮር ናሙና ዘዴ የተመረጡ ከመፃሕፍቱ ዋና አዘጋጅ (1) እና ከ30 ዓመት በላይ ልምድ ካላቸው የሁለተኛ ድግሪ ትግርኛ ቋንቋ መምህራን (3) ጋር ከፊል-የተዋቀረ ቃለ መጠይቅ ተካሂዷል። ውጤቶቹ እንደሚያሳዩት በሁለቱም ክፍሎች ከጠቅላላ ተግባራት ዝቅተኛ የማሰብ ክህሎት (LOTS) 90.37% (~90) ሲሆን፤ ከፍተኛ የማሰብ ክህሎት ደግሞ (HOTS) 9.63% (~10) ይህም ማለት በ9ኛ ክፍል 11.06% እና በ10ኛ ክፍል 8.06% ማለት ነው። ስለሆነም ከ9ኛ ወደ 10ኛ ክፍል HOTS በ3% (regression in cognitive progression) ቀንሷል። እንዲሁም በማንበብ እና በማዳመጥ ክሂሎች ውስጥ በ10ኛ ክፍል HOTS በቅደም ተከተል ከ3% እና 5% ወደ 0% ወርዷል። ይህ የሆነበት ዋና ምክንያት ክሂሎቹ በዚህ የክፍል ደረጃ በተከታታይነት ባለመቅረባቸው መሆኑ አጥኚው አረጋግጧል። በምዕራፎች ውስጥ እና በክፍሎቹ መካከል ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት በከፍተኛ ደረጃ አልተመጣጠነም። የቃለ መጠይቅ ውጤቶችም ይህን አረጋግጠዋል፤ መፃሕፍቱ ተገቢና ግልጽ የሆነ ሞዴል አለመጠቀማቸው፣ የአንድን መጽሐፍ ምዕራፎች በግለሰብ ደረጃ ተከፋፍለው መዘጋጀታቸው ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንዳይኖራቸው አድርገዋል። ጥናቱ መፃሕፍት በቡድን እና በRBT መሰረት እንዲዘጋጁ፣ የመፃሕፍት አዘጋጆችና መምህራን ቀጣይነት ያለው ስልጠና እንዲያገኙ፣ ከፍተኛ የማሰብ ክህሎት የሚያዳብሩ ተግባራት እንዲጨመሩ ይመከራል።*

# ምዕራፍ አንድ፦ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች በትምህርት ስርዓት ውስጥ ማካተት ያለው ጠቀሜታ በመገንዘብ ለተማሪዎች በእውቀት፣ በአስተሳሰብና፣ በክህሎት ረገድ መሰረታዊ ለውጥ እንዳለው የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ጥናቶች ያመለክታሉ። በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ ሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) "በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ የተመሰረተ የመድብለ ቋንቋ ትምህርትን መጠቀም ለተማሪዎች በስነ ልቦናዊ አስተሳሰብ የላቀ ከፍታ እንዲደርሱ ያግዛቸዋል።" በማለት UNESCO (2016፣ 21) ይገልፃል። እንዲሁም "በኢትዮጵያም በተለይ በትግራይ ክልል የትግርኛ ቋንቋ በእናት ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለው ሚና ተመሳሳይ ነው።" MoE (2010፣ 27)።

የቋንቋ መማርያ መፃህፍት በቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጡ መሳርያዎች ናቸው። በተማሪዎች ተሳትፎም ተጽዕኖ ያሳድራሉ። እንደ Tomlinson (2011:38) ገለፃ "ውጤታማ የቋንቋ መማርያ መፃህፍት የተማሪዎች ፍላጎት ለማሟላት የተነደፉ ሲሆኑ የቋንቋ እውቀትን በአሳታፊና ከአውደ ጽሑፉ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ነገሮች ላይ ያተኩራሉ።" ይህ ሐሳብ ከMcGrath (2013:86) ተምሳሳይነት አለው። እሱም ይዘትን ከትምህርታዊ ዓላማዎች ጋር የማመጣጠን አስፈላጊነት አጽንኦት ይሰጣል። "የትምህርት መሳርያዎች ውጤታማ የመማር ልምድን እንዲያሳድጉ ስልታዊ በሆነ መልኩ መገምገም አለባቸው።" በማለት ይገልፃል።

የቋንቋ መማርያ መጽሐፍ በአምዳዊ አደረጃጀት ተገቢነት መነጽር መገምገም ውጤታማ የቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር ያደርጋል። የመማርያ መሳርያዎቹ መገምገም ለመምህራን ተጨማሪ እውቀትና ክሂሎች ከመሙላት በዘለለ ለተማሪዎቻቸው የተለያዩ ፍላጎቶች የሚያሟሉ የትምህርት መሳርያዎችን በተሻለ ሁኔታ መለየት እንዲችሉ ያደርጋል። ይህንን ሀሳብ በተመለከተ Cunningsworth (1995፡126) "የዓምዳዊ አደረጃጀት ተገቢነት በቋንቋ መማርያ መጽሐፍ ግምገማ ውስጥ ሁለንተናዊና የተቀነባበረ ማዕቀፍ ሊመቻችና ሊካተት ይገባል። ይህ ማዕቀፍ የተለያዩ መመዘኛዎች የያዘ ሲሆን ከትምህርት ደረጃዎች ጋር የመማርያ መጽሐፍ ይዘትን ከቋንቋ ክሂሎች ደረጃዎች ጋር መወሐድ አለበት ።" ይላል ።

እንደ Cunningsworth (1995:55) እና Tyler (2013:87) ገለፃ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲደራጁ በሁለት ዓይነት መንገድ ከፍሎ ማየት ይቻላል። እነሱም "አንደኛው የቋንቋ ትምህርትን በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች መካከል የሚኖራቸው ግንኙነት ጎናዊ (Horizontal) የሚባለው ሲሆን ሁለተኛው የቋንቋ ትምህርት ይዘት ተዋርዳዊ አደረጃጀት (vertical) በመባል የሚታወቀው ነው።" በማለት ይገልጹታል።

ዓምዳዊ (ተዋረዳዊ) አደረጃጀት (vertical alignment) ከመጀመርያው የክፍል ደረጃ አንስቶ እስከ ላይኛው ያለው የክፍል ደረጃ የዓንድ የትምህርት ዓይነት ግንኙነት የሚያሳይ ነው። ባጠቃላይ የትምህርት ይዘቶች ከታች ወደ ላይ ያለውን አደረጃጀት ዝምድና የሚመለከት ሲሆን በውስጥ ሁለት አበይት ክፍሎች ያካትታል። እነሱም "የይዘት ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት ናቸው።" በማለት Tyler (2013:94) ያብራረዋል።

የይዘት ተከታታይነት በአንድ የትምህርት ዓይነት ውስጥ የተካተቱ የትህርት ይዘቶች በተከታታይነት መደጋገምን የሚገለጽበት ነው። ለምሳሌ የቃል ትምህርት ድግግም፣ በድግግም ውስጥ የሚታይ እድገት፣ መስፋት መጥበብን ጨምሮ ማደራጀትን ያመለክታል። ይህ ማለት በመጀመርያ የቀረበው ይዘት እስከ መጨረሻው ያንን ይዘት መድገም ማለት ሳይሆን በየምዕራፉ እና በየደረጃ ክፍሉ እንደ መጣኝነቱ እየተለጠጠ ወይም እየሰፋ የሚሄድ ነው። ይህን ሐሳብ አስመልክቶ Cunningsworth (1995:120)፥ Richards (2001:55) እና Tyler (2013:91) በተመሳሳይ "ተከታታይነት አንድ የትምህርት ይዘት ሳይቆራረጥ በየምዕራፉ እና በየክፍል ደረጃው ተደጋግሞ መቅረቡን የሚያሳይ ነው።" በማለት ያብራራሉ።

የይዘት ተለጣጠቂነት በየምዕራፉም ሆነ በየክፍል ደረጃው የሚዘጋጁ የትምህርት ይዘቶች እድገት የሚታይበት ነው። ይህም ማለት ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ፣ ከግልጽ ወደ ውስብስብ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ በሆነ መልኩ መደራጀትን ያመለክታል። Cunningsworth (1995: 121) ፥ Richards (2001:56) እና Tyler (2013:92) "ተለጣጣቂነት የይዘቱ መደጋገም ሳይሆን በተመረጡ ርእሰ ጉዳይ ይዘት የሚሰጠው ትምህርት እየሰፋ እና እየከበደ መዘጋጀቱን ያመለክታል።" በማለት ይገልጹታል። ስለሆነም ተለጣጣቂነት የተለያዩ የሚመስሉ ይዘቶች እርስ በርስ ያላቸው ትስስርን፣ ቁርኝትን እና መደጋገፍን ያመለክታል።

ለምሳሌ፦ ፊደል፣ ቃል፣ ሐረግ፣ ዓረፍተ ነገር፣ ድርሰት፣ ጽህፈት፣ ንባብ፣ ንግግር ወዘተ የሆኑ የእውቀት ክሂሎች ከታች ወደ ላይ የሚደረደርበት ነው።

"በመማሪያ መፃህፍት የዓምዳዊ አደረጃጀት ቅንጅት ከተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ (RBT) እይታ አኳያ የግንዛቤ ለውጥ በማምጣት ቀጣይነት ያለው የዕውቀት እድገትን ያረጋግጣል።" በማለት Anderson & Krathwohl (2001፣8) ይገልፁታል። በተጨማሪም Garcia & wing (2014፣126) "ይህ አካሄድ በትምህርት ደረጃዎች ከተራ የማስታወስ፣ የመረዳት እና የመተግበር ችሎታዎች ወደ ከፍተኛ የመተንተን፣ መገምገምና መፍጠር ችሎታ ያሸጋግራል ።" በማለት ያረጋግጣሉ። በአጠቃላይ ከምሁራን ሐሳብ መረዳት የሚቻለው የመማሪያ መፃሕፍት ተግባራትና ክህሎቶች ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ በሆነ መልኩ ሲደራጁ የተማሪዎችን የማሰብ ችሎታ ቀስ በቀስ እያሰፉና እያጎለበቱ ወደ ፈጠራ ደረጃ እንደሚያደርሱ ነው።

በመሆኑም በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የምዕራፎች ተያያዥነት፣ ከአንዱ የክፍል ደረጃ ወደ ቀጣዩ የክፍል ደረጃ የተግባራት ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንዴት እንደተደራጀ በጥናት መገምገሙ አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል። በተለይ በ2008 ዓ.ም. ታትመው በመላው ኢትዮጵያ ስራ ላይ የዋሉት እኒህ መጻሕፍት ይህን መሰረታዊ መርህ መከተል ችለው እንደሆን የመገምገም አስፈላጊነት ይፈጥራል። ይህ ጥናት የተማሪዎች የቋንቋ ክህሎት ተከታታይነት ያለው ተለጣጣቂነት እንዲኖር፣ ከዝቅተኛ የማሰብ ደረጃ (LOTS) ወደ ከፍተኛ የማሰብ ደረጃ (HOTS) በተገቢ መልኩ እንዲሸጋገር መፍትሄ ለመፈለግና ለትምህርት ባለድርሻ አካላት መረጃ ለማቅረብ ያለመ ነው።

*ቁልፍ ቃላት፡- ዓምዳዊ አደረጃጀት፣ ተለጣጣቂነት፣ ተከታታይነት፣ የተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ (RBT)፣ ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃ (HOTS)፣ ዝቅተኛ የዕውቀት ደረጃ (LOTS)።*

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በኢትዮጵያ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስርዓት ውስጥ የቋንቋ ትምህርት ጥራት ለማሳደግ የመማርያ መፃህፍት ይዘት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በተለይ ደግሞ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር 2008ዓ/ም በተዘጋጁ የሁለተኛ ደረጃ የትግርኛ ቋንቋ የተማሪው መማርያ መፃህፍት በ9ኛ እና 10ኛ የክፍል ደረጃ በዋናነት የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር የተዘጋጁ ቢሆኑም፤ በእነዚህ መጽሐፎች ውስጥ ያሉ ተግባራት የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት (vertical alignment) ተገቢ መሆኑ ጥያቄ ውስጥ ይገባል።

እነዚህ በስራ ላይ ያሉ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡ ተግባራት[ ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት እንዳላቸው ወይም ከተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ Anderson & Krathwohl (2001) RBT የዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት ጋር የሚስማሙ መሆናቸው ገና በቂ ትንተና አላገኙም። በተለይ ደግሞ በአንድ ምዕራፍ ውስጥ ያሉ ተግባራት ከቀደምት ምዕራፍ ጋር ተያይዘው የሚቀጥሉ እንደሆኑ፤ በምዕራፎች መካከል ያሉ ተግባራት ስለመመጣጠናቸው፤ ከ9ኛ ወደ 10ኛ የክፍል ደረጃ ያለው የክሂሎች ተለጣጣቂ እድገት ስለመኖር፣ እና ዝቅተኛ (LOTS) እና ከፍተኛ (HOTS) የማሰብ ደረጃዎች በተገቢ መጠን ስለመካተታቸው በዚሁ ክፍል የተጠኑ ጥናቶች ኣጥኚው በቂ መረጃ ማግኘት አልቻለም። ይህ ችግር የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎች ተከታታይ እድገት ሊያውክ፣ የመማር ፍላጎትን ሊቀንስ፣ እና በመጨረሻም የትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ስለዚህ፣ በ2008 ዓ/ም ታትመው ስራ ላይ ባሉ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፎች ውስጥ ያሉ የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት ከ Anderson & Krathwohl (2001) RBT እይታ አኳያ ምን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ በመረጃ የተደገፈ ምላሽ መስጠት አስፈልጓል።

ስለሆነም በ9ኛ ክፍል እና 10ኛ ክፍል ትግርኛ የተማሪው መጽሐፍት ክሂሎችን ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች (መልመጃዎች) በያንዳንዱ ምዕራፍ ያላቸው የይዘት ተከታታይነትን እስከ መጨረሻው ምዕራፍ አንድነታቸው እና ተያያዥነታቸውን ጠብቀው ሳይቆራረጡ ዘልቀው ይሆን? እንዲሁም በያንዳንዱ ምዕራፍና እና በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች መካከል ይዘቶቹ ወይም ተግባራቶች ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ከጠባብ ወደ ሰፊ ከቅርብ ወደ ሩቅ፣ ከግልጽ ወደ ውስብስብ፣

ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ በሆነ መልኩ በመደራጀት የይዘት ተለጣጣቂነትን ጠብቀው ቀርበው ይሆን? እንዲሁም በምዕራፎች መካከል ያለው የተግባራት ስርጭት መጠን በመማርያ መፅሃፎቹ ዓምዳዊ አደረጃጀት ተጽኖ ይኖራቸው ይሆን? ባጠቃላይ ዓምዳዊ ኣደረጃጀታቸው ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎችን አጥኚው ለመመርመር እና ለመመለስ ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ በዚሁ ርእስ እንዲያጠና ተነሳስቷል።

# 1.3 የጥናቱ ዓላማ

## 1.3.1 አጠቃላይ ዓላማ

በ2008 ዓ/ም ታትመው ስራ ላይ ባሉ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፎች ውስጥ ያሉ የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀትን ከተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ Anderson & Krathwohl (2001) RBT የዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት እይታ አኳያ መገምገም። የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ ሲሆን ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ የሚመነጩ ዝርዝር ዓላማዎች (Specific Objectives) እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### ዝርዝር ዓላማዎች

1.3.2.1 በ9ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፍ ውስጥ በየምዕራፉ የቀረቡ ክህሎቶች ዓምዳዊ አደረጃጀትን (ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት) ከ Anderson & Krathwohl (2001) የዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት እይታ አኳያ መገምገም።

1.3.2.2 በ10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፍ ውስጥ በየምዕራፉ የቀረቡ ክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀትን (ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት) ከ Anderson & Krathwohl (2001) የዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት እይታ አኳያ መገምገም።

1.3.2.3 በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፎች መካከል ያሉ ክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀትን (ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት) ከ Anderson & Krathwohl (2001) የዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት እይታ አኳያ መገምገም። የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎች ተካተውበታል።

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በ2008 ዓ.ም. ታትመው ሥራ ላይ የዋሉ የ9ኛና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ የክህሎት ዓምዳዊ አደረጃጀት ጉድለቶችን በመለየት ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

- ለተማሪዎች፦ ይህ ጥናት መጽሐፎቹ የተሻለ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንዲኖራቸው በማድረግ የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎት ቀጣይነት ያለው እድገት ያረጋግጣል። በተለይ ከዝቅተኛ የማሰብ ደረጃ (LOTS) ወደ ከፍተኛ የማሰብ ደረጃ (HOTS) በተገቢ መልኩ እንዲሸጋገሩ፣ የመማር ፍላጎታቸው እንዲጨምርና በመጨረሻም በብሔራዊ ፈተናና በሌሎች የአካዳሚክ አፈፃፀም ላይ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ያግዛል።
- ለመምህራንና ትምህርት ተቋማት፦የመጻሕፍቱን ድክመቶች በመለየት ተጨማሪ የማስተማር ዘዴዎችን እንዲያዘጋጁ፣ የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎት ሽግግር እንዲያቀላጥፉና በክፍል ውስጥ የHOTS ተግባራትን እንዲያስተምሩ ያስችላል።
- ለመጻሕፍት አዘጋጆች፡ ዝቅተኛና ከፍተኛ የማሰብ ክህሎት (LOTS & HOTS) በተመጣጣኝ መጠን ለማካተት ተግባራዊ መመሪያ ይሰጣል።
- ለትምህርት ፖሊሲ አውጪዎችና ሥርዓተ-ትምህርት አዘጋጆች፡ የትግርኛና የሌሎች ቋንቋዎች መማሪያ መጻሕፍት ይዘት ማሻሻያ ፖሊሲዎችን ለመንደፍ ተጨባጭ መረጃ ያቀርባል።
- ለተመራማሪዎችና ለቀጣይ ጥናቶች፡ በትግርኛ ወይም በሌሎች ቋንቋዎች የመማሪያ መጻሕፍት ይዘት ትንተና ለማድረግ መሰረታዊ ሞዴልና ዘዴ ይሆናል።

በመጨረሻም ይህ ጥናት በትግርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን የክህሎት እድገት በማጠንከር የኢትዮጵያ ትምህርት ጥራት ለማሻሻል የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በ2008 ዓ/ም ታትመው ስራ ላይ ባሉ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀትን ከተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ Anderson & Krathwohl (2001) እይታ አኳያ እንዴት እንደተደራጀ መፈተሽ ነው።

- ★ የይዘት ወሰን፦ ጥናቱ በትግርኛ መማርያ መጽሐፎች ውስጥ በየምዕራፉ የቀረቡ የማንበብ፣ ማዳመጥ፣ መፃፍ እና መናገር ተግባራትን (exercises) ብቻ ይመለከታል፤ የመማሪያ መጽሐፍ ዋና ጽሑፍ፣ ምሳሌዎች፣ ወይም ሌሎች ክፍሎች አጥኚው ከሚኖረው ጊዜና በጀት አኳያ ስለሚከብድ እና ስለሚሰፋ፤ የጥናቱ ይዘት ወሰን በኪሂሎች ተግባራት ዓምዳዊ አደረጃጀት ላይ ብቻ እንዲያተኩር ተደርጓል።
- ★ የደረጃ ወሰን፦ ጥናቱ በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል ብቻ የተወሰነ ሲሆን፣ ጥናቱ ከዚህ አልፎ ወደ ሌላ የደረጃ ክፍል አይሸጋገርም። ምክንያቱም የአጥኚው የማስተማርና የስራ ልምድ ከሌሎች የክፍል ደረጃ በበለጠ በዚህ የክፍል ደረጃ የተሻለ በመሆኑ ነው።
- ★ የቋንቋ ወሰን፦ የዚህ ጥናት የቋንቋ ወሰኑ በትግርኛ መማርያ መጽሐፎች ብቻ የተወሰነበት ምክንያት አጥኚው ምንም እንኳን ከነበረው የስራ ልምድ እና እውቀት በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ማጥናት ቢችልም ከሁለቱም በበለጠ ጥያቄው ያስነሱበት እነዚህ የትግርኛ መፃህፍት ናቸው።
- ★ የጊዜ ወሰን፦ ጥናቱ በ2008 ዓ/ም ታትመው ስራ ላይ ባሉ መጽሐፎች ብቻ የተወሰነ ሲሆን፣ ከዚህ በፊት የታተሙትን ከዚህ ኣስቀድሞ ማጥናቱ ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚጎላ እና እነዚህን የሚተኩ መፅሐፎች እስካሁን ባለመታተማቸው ምክንያት እንዲወሰኑ ሆነዋል።

- ★ የዘዴ ወሰን፡ ይህ ጥናት በተጋናኝ ትይዩ ቅይጥ ዘዴ (convergent parallel mixed-methods design) ላይ የተመረከዘ ሲሆን፣ የመረጃ ምንጮቹ የተማሪ መጻሕፍት (ሰነድ) እና የተመረጡ ባለሙያዎች (አዘጋጅና መምህራን) ብቻ ናቸው። ስለዚህ የተማሪዎች አካዳሚያዊ አፈፃፀም፣ የብሔራዊ ፈተና ውጤት፣

የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ ወይም ተማሪዎችን ያካተተ ጥናት አይካተትም። እነዚህ ወሰኖች ጥናቱን በተወሰነ እና በሚቻል መጠን ለማጠናቀቅ ያስችላሉ።

## 1.6 የጥናቱ ውሱኑነት

ይህ ጥናት ሲካሄድ የሚከተሉት ውስንነቶች አጋጥመውታል።

1. የመምህር መመሪያ መጽሐፍ፣ መርሐ ትምህርት፣ የስርዓተ ትምህርት ሰነድ፣ በክፍል ውስጥ የሚጨመሩ ተጨማሪ ቁሳቁሶች እና የተማሪዎች አካዳሚያዊ አፈፃፀም ስላልተካተቱ፣ የመፃሕፍቱ ይዘት በተማሪዎች ላይ ያለውን ተጨባጭ ተጽዕኖ በቀጥታ መለካት አልተቻለም። ይህ በውጤቱ ትርጓሜ ላይ አንድ የተወሰነ መረጃ ክፍተት አስከትሏል።

2. የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች ቁጥር ውስን (አንድ አዘጋጅና ሶስት መምህራን) በመሆኑ፣ የተገኘው ዓይነታዊ መረጃ ለሌሎች አውዶች ሙሉ በሙሉ ሊዛወር አይችልም። ይህም በውጤቱ ላይ የተወሰነ የአጠቃላይ ትርጓሜ ክፍተት ይፈጥራል።

3. የተማሪዎችን የብሔራዊ ፈተና (EGSEC) ውጤት፣ የክፍል ውስጥ አጭር እና ማጠቃለያ ውጤቶች ወይም የተማሪዎችን ቀጥተኛ አስተያየት ስላልተካተተ፣ የመፃሕፍቱ ይዘት በተማሪዎች ላይ ያለውን ተጽዕኖ በሙሉ መግለጽ አልተቻለም። ይህ በውጤቱ ላይ ተጨማሪ የተጽዕኖ መረጃ ክፍተት አስከትሏል።

እነዚህ ውስንነቶች ቢኖሩም ጥናቱ በተመረጡት መጻሕፍት ውስጥ ያለውን የዓምዳዊ አደረጃጀት በተጨባጭ መልኩ በመግለጽ በቂ አስተዋጽኦ አበርክቷል። የተጠቀሱት ውስንነቶች ለቀጣይ ጥናቶች የተሻለ አቅጣጫ ያመላክታሉ።

## 1.7 በጥናቱ የቃላት አጠቃቀም ፍቺዎች (working definition)

| ቃል | ፍቺ (Definition) | በጥናቱ ውስጥ አጠቃቀም |
|---|---|---|
| ዓምዳዊ አደረጃጀት (Vertical Alignment) | በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች መካከል ያለው የይዘት፣ የክህሎትና የውጤት ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት (Webb, 1997; Schmidt et al., 2005) | ከ9ኛ ወደ 10ኛ ክፍል የትግርኛ ቋንቋ ክሂሎች እና የማሰብ ደረጃዎች ቀስ በቀስ መጨመር አለመኖሩን መለካት |
| ተከታታይነት (Continuity) | በአንድ የክፍል ደረጃ ውስጥ ከምዕራፍ ወደ ምዕራፍ ያሉ ይዘቶችና ተግባራት ያላቸው ተያያዥነትና ተመሳሳይነት (Tyler, 1949) | በ9ኛ ወይም 10ኛ ክፍል መጽሐፍ ውስጥ ተመሳሳይ የቋንቋ ክሂል በሁሉም ምዕራፎች ያለማቋረጥ በተያያዥነትና በተከታታይነት መቀጠል። |
| ተለጣጣቂነት (Sequential Coherence) | ከአንድ ክፍል ደረጃ ወደ ቀጣይ ክፍል ደረጃ የሚደረግ የይዘትና የማሰብ ደረጃ ቀስ በቀስ መጨመር (Anderson & Krathwohl, 2001) | ከ9ኛ ወደ 10ኛ ክፍል የHOTS መቶኛ ከ11.06% ወደ 8.06% በ-3% ቅናሽ ማሳየቱ |
| የተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ Anderson & Krathwohl (2001) RBT (Revised Bloom's Taxonomy) | የብሉም ታክሶኖሚ የተሻሻለ ስሪት (2001) ሲሆን የማሰብ ሂደቶችን በስድስት ደረጃዎች Remember (R1), Understand (U2), Apply (Ap3), Analyze (A4), Evaluate (E5), Create (C6) ነው። (Anderson & Krathwohl, 2001) | በመጽሐፍቱ ውስጥ ያሉ ተግባራትን ወደ ስድስት ደረጃዎች (R1–C6) መመደብና መቶኛ መወሰን የሚያስችል መሳሪያ። |

| ቃል | ፍቺ (Definition) | በጥናቱ ውስጥ አጠቃቀም |
|---|---|---|
| ዝቅተኛ ደረጃ የማሰብ ክህሎት(LOTS)(Lower-Order Thinking Skills) | የመሰረታዊ የማሰብ ደረጃዎች (R1, U2, Ap3) – መስታወስ፣ መረዳት፣ መተግበር (Blooms, 1956)። | በ9ኛ ክፍል 93.1%፣ በ10ኛ ክፍል 91.9% |
| ከፍተኛ ደረጃ የማሰብ ክህሎት (HOTS) | የከፍተኛ የማሰብ ደረጃዎች (A4, E5, C6) – መተንተን፣ መገምገም፣ መፍጠር (Anderson & Krathwohl, 2001)። | ከ11.02% ወደ 8.06% ቀንሷል |
| የይዘት ትንተና (Content Analysis) | የመጽሐፎች እና ሰነዶች ይዘት በስርዓትና በተጨባጭ መስፈርት መመደብና መተንተን (Krippendorff, 2018፤ Stemler, 2001) | በዚህ ጥናት በ2008 ዓ.ም. የ9ኛና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መጽሐፍት ውስጥ ያሉ 779 ተግባራትን በ Anderson & Krathwohl (2001) RBT መሠረት መመደብና መቶኛ መወሰን። |
| ተግባር (Activity/Task) | በመጽሐፉ ውስጥ ለተማሪ የተዘጋጀ የቋንቋ ልምምድ (ጥያቄ፣ ልምምድ፣ ፕሮጀክት)። | ጠቅላላ 779 ተግባራት ተተነተኑ። |

# ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምንነት

Richards (2001፣251) "የማስተማረያ መፃህፍት በአብዛኛው የቋንቋ ትምህርት ወሳኝ እና ቁልፍ መሳርያዎች ናቸው። የመምህርና የተማሪ መጽሐፍ፣ በየድርጅቱ የሚዘጋጁ የትምህርት መሳርያዎች የግል የትምህርት መሳርያዎች ወዘተ በክፍል ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎች ግብአት በመሆን ቋንቋ እንዲማሩ የሚያግዙ መሳርያዎች ናቸው።" በማለት ይገልፀዋል። ከዚህ ሐሳብ የምንረዳው የቋንቋ ማስተማርያ መሳርያዎች ቋንቋ በማስተማር ሂደት ተማሪዎች የበለጠ ከትምህርቱ ተጠቃሚ የሚያደርጉና የመማርና የማስተማር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ ግብአቶች ናቸው ማለት ይቻላል።

በትምህርት መዋቅር ስርዓት ወሳኝ ከሚባሉ መሳርያዎች አንዱ እና ቀዳሚው ማስተማርያ መጽሐፍ ነው። ይህ የትምህርት መሳርያ ምንም ዓይነት አጋዥ መሳርያ በሌለበት ቦታ ለመምህርና ለተማሪዎች ቁልፍ መሳርያ ሆኖ ያገለግላል። Awasthi (2006፣1) "እንደሚለው መማርያ መጽሐፍ ለመምህሩ ማስተማርያ ለተማሪዎች ደግሞ መማርያ መሳርያ ነው።" ይለዋል።

ከዚህ ሐሳብ ባልተለየ Hornby (2005፣158) "ማስተማርያ መጽሐፍ ለአንድ የትምህርት ዓይነት የሚዘጋጅ የትምህርት መሳርያ ሲሆን በተለይ በኮሌጅ እና በትምህርት ቤቶች የሚዘጋጅ ነው።" በማለት ይገልፀዋል።

እንዲሁም Brown (2001፣141) "የመማርያ መጽሐፍ ስርዓተ ትምህርት መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ የሚውል ነው።" ይለዋል። ስለሆነም እኒህ የትምህርት መሳርያዎች በጥንቃቄ በሚመለከታቸው አካላት ተዘጋጅተው የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማ እንዲሆን የራሳቸውን ድርሻ የሚጫወቱ ቁልፍ መሳርያዎች መሆናቸውን እንረዳለን።

### 2.1.2 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፎች ተገቢነት

Graves (2000:158) እንደገለፀው "ተገቢነት ከበርካታ ወሳኝ ነገሮች ጋር ይገናኛል። ማለትም የባህል ውክልና፣ ለተለያዩ ተማሪዎች ተደራሽነት፣ እና በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉትን የማስተማር ዘዴዎችን ያካትታል ።" ከዚህ ሐሳብ ጋር በተያያዘ Meyer & Garrison (2015:88) "ውጤታማ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የተማሪዎችን የተለያዩ ባህላዊ ዳራዎች የሚያንፀባርቁ መሆን አለባቸው። ይህም ከልምዳቸው እና አመለካከታቸው ጋር የሚስማሙ የትምህርት መሳርያዎች እንዲቀርብላቸው ይረዳል። ስለሆነም ከተለያዩ ባህሎች የተውጣጡ ትክክለኛ ጽሑፎችን ማካተት እና ተማሪዎችን ሊያራርቁ የሚችሉ አመለካከቶችን ወይም አድሎአዊ ድርጊቶችን ማስወገድን ያካትታል ።" በማለት ይገልጹታል።

በተጨማሪም ተደራሽነት በጣም አስፈላጊ ነው። የመማሪያ መፃህፍት የተለያዩ የቋንቋ ብቃቶችን እና የመማሪያ ዘዴዎችን ማሟላት እለባቸው። በመማርያ ክፍል ውስጥ የተለያየ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች አካታች በሆነ መንገድም መቅረብ አለባቸው። ይህን ሐሳብ በተመለከተ "ሁሉን አቀፍ እና አካታች የሆነ ትምህርት የተለያየ ዳራ እና ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ከትምህርቱ ጋር ትርጉም ባለው መንገድ እንዲሳተፉ ያስችላቸዋል።" በማለት Rose & Meyer (2002:159) ይገልፁታል።

እንደ Nation & Webb (2011:38) ገለፃ "ውጤታማ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፎች መስተጋብራዊ እና ተማሪን ያማከለ እካሂዶችን ማካተት አለባቸው።" በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ቃልን በማስታወስ ወይም በተደነገጉ የሰዋስው ህጎች ላይ ይሚያተኩሩ የመማሪያ መጽሐፍት ተማሪዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ላይሳተፉ ይችላሉ። በምትኩ በፕሮጀክት ላይ የተመሰረተ ትምህርትን፣ የትብብር ተግባራትን እና ወሳኝ የአስተሳሰብ ልምምዶችን ማካተት በቋንቋ አጠቃቀም ላይ ጥልቅ ግንዛቤን እና ብቃትን ያሳድግላቸዋል።

### 2.1.3 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ግምገማ አስፈላጊነት

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፎች የቋንቋን ትምህርት ለማስተማር ዋና መሳርያዎች ናቸው። ለተማሪዎች እንደ ግብአት እንዲሁም ለአስተማሪዎች ስርዓት ትምህርታቸውን

ለማዋቀር እንደ መመሪያ ሆነው ያገለግላሉ። የትምህርት መዋቅሩ እየተሻሻለ ሲመጣ ውጤታማ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አስፈላጊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይሄዳል። ስለዚህ የነዚህ የመማሪያ መጽሀፍት ምዘና አግባብነታቸው፣ ውጤታማነታቸው እና ከወቅታዊ የቋንቋ ትምህርት ጋር ያላቸውን ጠቀሜታ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

ስለሆነም የመማሪያ መፃህፍት በቋንቋ የመማር ሂደት ውስጥ መሰረታዊ መሳሪያዎች ናቸው። የስርአተ ትምህርት አሰጣጥን በመቅረጽ እና የተማሪ ተሳትፎ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ። በቋንቋ ትምህርታዊ እና የእውቀት (ኮግኒቲቭ) ሳይንስ ምርምር ውስጥ የሚወጡ የተዋቀሩ ይዘቶችን ያቀርባሉ። እንደ Tomlinson (2011፣124) ገለፃ፣ "ውጤታማ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት የተማሪዎnችን ፍላጎት ለማሟላት የተነደፉ ሲሆኑ የቋንቋ ዕውቀትን አሳታፊ ሆነው ከዓውዱ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ነገሮች ላይ ያተኩራሉ።" ይህ ስሜት በ McGrath (2013፣187) ተስተጋብቷል። እሱም "ይዘትን ከትምህርታዊ ዓላማዎች ጋር ማመጣጠን አስፈላጊነት አጽንዖት ይሰጣል።" ይህም የትምህርት መሳርያዎቹ ውጤታማ የመማር ልምድን እንዲያሳድጉ ስልታዊ በሆነ መልኩ መገምገም አለባቸው ማለት ነው።

በአጠቃላይ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ግምገማ ትምህርታዊ መሳርያዎች የታለመላቸውን ዓላማ እንዲያሟሉ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። የቋንቋ እውቀትን እና ተግባቦትን ያሳድጋል። ስለሆነም ውጤታማ የግምገማ ሂደት የመማሪያ መጽሐፍትን በአግባቡ እንዲተነተኑ ያበረታታል። የቋንቋ ተማሪዎች እና አስተማሪዎች የሚያሻሽሉ ጥያቄዎችን ያሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ግሎባላይዜሽን እና ቴክኖሎጂ በቋንቋ ትምህርት ላይ ተጽእኖ እያሳደሩ በመጡ ቁጥር የመማሪያ መጽሐፍትን ጥራት በየጊዜው የመከለስ እና የመገምገም አስፈላጊነት ጥያቄ አያስፈልገውም። በትምህርት መሳርያዎች ጥራት የወደፊት መሻሻያዎችን ተሳትፎን እና የቋንቋ ክህሎቶችን ተግባራዊ አጠቃቀምን የሚያበረታቱ ተማሪን ያማከሉ አቀራረቦችን ማስቀደም አለበት። ውጤታማ ዓምዳዊ አደረጃጀት ቀለል ያለ የመማር ልምድን ያመቻቻል፣ተማሪዎች ቀደምት ዕውቀት ላይ እንዲገነቡ ያስችላቸዋል፣ይህም ለቋንቋ ትምህርት እጅግ በጣም ወሳኝ ነው።

## 2.1.4 የአምዳዊ አደረጃጀት ምንነት

"አምዳዊ አደረጃጀት በተመሳሳይ የትምህርት ዓይነት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ያላቸውን የይዘት ተከታታይነትን እና ተለጣጣቂነትን እንደሚያመለክት" Schmidt et al., (2005፣ 546) ይገልፃል። በቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ወደ ክፍል ሲገቡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ውስብስብ የሆኑ የቋንቋ አወቃቀሮችን፣ የቃላት አጠቃቀምን እና የተግባቦት ተግባራትን እንደሚያጋጥሟቸው ያረጋግጣል። በአምዳዊ አደረጃጀት የተስተካከለ የቋንቋ ሰርዓተ ትምህርት ቀስ በቀስ የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር ያስችላል። ይህም ለቋንቋ ዕውቀት እና ክሂሎች አስፈላጊ የሆነ የመማሪያ ልምድን ይፈጥራል።

እንደ Porter (2002፣7) "የስርአተ ትምህርት ውጤታማነት በአብዛኛው የሚለካው በግምገማ፣ በማስተማሪያ ቁሳቁሶች እና በትምህርት ደረጃዎች መካከል ባለው አደረጃጀት ነው።" ይላል። ከዚህ ሐሳብ አኳያ የመማሪያ መፃህፍትን ለአምዳዊ አደረጃጀት መገምገም ምን ያህል ከክልል ወይም ከሐገር አቀፍ የትምህርት ማዕቀፎች እና በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች ምን መማር እንዳለባቸው ከሚወስኑ መለኪያዎች ጋር ምን ያህል እንደሚገናኙ ዝርዝር ትንታኔ ያስፈልገዋል። ለምሳሌ የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የትረካ አወቃቀሩን ቢያስተዋውቅ ነገር ግን በሚቀጥሉት ክፍሎች በዚህ ጽንሰ-ሀሳብ ላይ መገንባት ካልቻለ፣ ተማሪዎች እየገፉ ሲሄዱ ግንዛቤያቸውን እንደገና ለመገንባት ሊታገሉ ይችላሉ። ይህም በትምህርታቸው ላይ ክፍተቶችን ያስከትላል። ስለዚህ ጠንካራ የግምገማ መመዘኛ ጽንሰ ሀሳቦች እንዴት እንደሚተዋወቁ፣ እንዴት እንደሚጠናከሩ እና በሁሉም ተከታታይ የመማሪያ መጽሀፍት ላይ በጥንቃቄ ከቀዳሚው ደረጃ ክፍል ወደቀጣይ ደረጃ ክፍል ከቀላል ይዘቶች ወደ ውስብስብ የሆኑ ይዘቶች መሸጋገር እነዳለባቸው መመርመርን ማካተት አለበት። ይህን ሐሳብ Forehand (2010፣ 4) "በታደሰው የብሉምስ ታክሶኖሚ ቲኦሪ መሰረት የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎችን ወደ ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ (HOTS) እንዲሸጋገሩ የተዘጋጀ መሆን አለበት። በተለይ ከመሰረታዊ ደረጃዎች (LOTS) ወደ ውስብስብ አስተሳሰብ (HOTS) ቀስ በቀስ መሸጋገር ተገቢ ነው።" በማለት ይገልጽዋል።

### 2.1.5 አምዳዊ አደረጃጀት ተገቢነት በቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ ግምገማ አጠቃላይ እይታ

በትምህርታዊ አውዶች ውስጥ ዓምዳዊ አደረጃጀት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ወይም በስርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ የመማሪያ ዓላማዎች ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት እድገት ያመለክታል። በቋንቋ ትምህርት ውጤታማ የመማሪያ መጽሀፍ ግምገማ የትምህርት መሳርያዎቹ የመማር ደረጃዎችን እንዲያሟሉ ብቻ ሳይሆን የተማሪዎችን ድምር እና ተከታታይነት ያለው የትምህርት ልምድን እንዲያመቻቹ ለማረጋገጥ የዓምዳዊ አደረጃጀት መረዳትን ይጠይቃል። ይህን ሐሳብ እነ Anderson በታደሰው የብሉምስ ታክሶኖሚ ቲኦሪ ውስጥ እንደሚከተለው ሐሳቡን ያጠናክሩታል። “የትምህርት ዓላማዎችን በሁለት ዋና ዋና ደረጃዎች ይከፈላሉ። እነሱም መሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች የሚባሉት (Lower-Order Thinking Skills (LOTS)) ማስታወስ (Remembering)፣ መረዳት (Understanding)፣ መተግበር (Applying) እና ከፍተኛ የእውቀት ደረጃ (Higher-Order Thinking Skills (HOTS) ትንተና (Analyzing)፣ ግምገማ (Evaluating)፣ ፈጠራ (Creating) ናቸው። ተማሪዎች ለዘመናዊ ትምህርት እንዲዘጋጁ በHOTS ላይ ተጨማሪ ትኩረት እንዲደረግ ይመከራል።” Anderson & Krathwohl (2001፣ 67–68) በማለት ይገልፁታል። ይህም ማለት የትምህርት ይዘቶች ወይም ዓላማዎች አለያም ተግባራቶች ሲዘጋጁ ከቀላል ወደከባዳ ሳይቆራረጡ መዘጋጀት እንዳለባቸው ይገልፃሉ።

አምዳዊ አደረጃጀት ስርዓተ ትምህርቱን በተለያዩ የትምህርት እርከኖች ማገናኘትን ያካትታል። ይዘቱ በቅደም ተከተል የተደራጀ መሆኑን በማረጋገጥ ቀደም ሲል በነበረው እውቀት ላይ የተመሰረተ ነው። ይህ አካሄድ ተደጋጋሚነትን ለማስወገድ፣ የክሂሎች እድገትን ለማመቻቸት እና ግምገማዎችን ከትምህርት ደረጃዎች ጋር ለማጣጣም አስፈላጊ ነው። እንደ McTighe & Wiggins (2013፣120) “ውጤታማ ዓምዳዊ አደረጃጀት እንደሚያመለክተው እያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ስርዓተ ትምህርት ተማሪዎች ቀደም ብለው የተገኙ ክህሎቶችን በማጠናከር የወደፊት የትምህርት ግቦችን እንዲያሳኩ መርዳት አለበት።” በማለት ይገልፃሉ። እንዲሁም

### 2.1.6 በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አምዳዊ አደረጃጀት ቁልፍ መርሆዎች

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አምዳዊ አደረጃጀት አስፈላጊነት ተማሪዎች በተደራጀ እና ወጥ በሆነ የመማሪያ መንገድ ብቃትን እንዲያዳብሩ ከማስፈለጉ ነው። የቋንቋ ክሂሎችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ለማዳበር በአምዳዊ አደረጃጀት የተስተካከለ የቋንቋ ስርዓተ ትምህርት አስፈላጊ ነው። ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ብቃት እስከ ሁለተኛ ደረጃ እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከፍተኛ ብቃቶችን አሟልተው መዘጋጀታቸው እጅግ ብጣም ወሳኝ ነው። ይህ አደረጃጀት የመማሪያ መፃህፍት የክፍል ደረጃ መመዘኛዎችን ብቻ ሳይሆን ተማሪዎችን በቀጣይ የትምህርት ጉዟቸው ብቃታቸው ለስኬት በሚያዘጋጅ መልኩ መቀረፃቸውን ያረጋግጣል።

አካታች ትምህርት (Comulative Education):-አምዳዊ አደረጃጀት ሁሉን አቀፍ ትምህርትን ያበረታታል። እያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች በተቀመጡ ይዘቶች ዓላማ ላይ የሚገነባ ነው። ለምሳሌ:- በመጀመሪያው የክፍል ደረጃ የተዘጋጁ ቃላት ቀጣዩ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች ከአዲስ ይዘት ጋር ጥልቅ ግንኙነት እንዲኖራቸው ለማድረግ እንደገና መታየት እና መስፋፋት አለባቸው።" በማለት Hirsch (2006፣384) ይገልፀዋል።

እንዲሁም Snow&Uccelli (2009፣127) "ከክፍል ደረጃዎቹ ባሻገር ያለው ወጥነት፣የመማሪያ መጽሐፍቱ ጭብጥ፣ በቋንቋ አወቃቀሮች እና በባህላዊ ይዘቶች ውስጥ ወጥ የሆነ እድገት ማቅረብ አለባቸው። የመማሪያ መጽሐፍትን ለዚህ ወጥነት መገምገም ተማሪዎች ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው ክፍል ያለችግር መሸጋገራቸውን ያረጋግጣል።

የክፍል ደረጃ (Grade level) ፡- ውጤታማ አምዳዊ አደረጃጀት ማለት የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ይዘት ከክፍል ደረጃዎች ጋር ብቻ ሳይሆን በትምህርት ባለስልጣናት ከተቀመጡት አጠቃላይ የስርአተ ትምህርት ግቦች ጋር መጣጣም አለበት። ይህ የመማሪያ መጽሐፍት በተናጥል ጥቅም ላይ እንዳልዋሉ ነገር ግን የበለጠ ሰፊ የትምህርት ማዕቀፍ አካል መሆናቸውን ያረጋግጣል።" Van de Wall et al. (2013፣157) ።

## 2.1.7 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፎች በአምዳዊ አደረጃጀት ሲገመገሙ

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፎችን በአምዳዊ አደረጃጀት በሚገመገሙበት ጊዜ አስተማሪዎች እና የስርዓተ-ትምህርት አዘጋጆች አምዳዊ አደረጃጀት ለመገምገም የተወሰኑ መመዘኛዎችን መጠቀም ይችላሉ።እንደ Fang (2006፣ 499) ገለፃ "የይዘት ተከታታይነት፣ የመማሪያ መጽሀፉ ይዘት ምን ያህል ከቀደምት እና ከወደፊቱ የስርዓተ ትምህርት ደረጃዎች ጋር እንደሚገናኝ መመርመር። ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች የገቡ ክህሎቶች በኋላኞቹ የክፍል ደረጃዎች ተመልሰዋል? ተስፋፍተዋል? ለምሳሌ፣ ጽሑፎችን የማንበብ ውስብስብነት ከተማሪዎች የእውቀት (ኮግኒቲቭ) እድገት ጋር መጨመር አለበት።" በማለት ይገልጸዋል።

ከላይ እንደተገለጸው የክሂሎች እድገት እንደ ማንበብ፣ መፃፍ፣ መናገር እና ማዳመጥ ያሉ የቋንቋ ክሂሎች እድገትን መገምገምን ሲሆን እነዚህ ችሎታዎች ሳይቆራረጡ በተከታታይነት፣ በውስብስብነት እና በጥልቀት ማደግ አለባቸው። ይህን ሐሳብ በታደሰው የብሉምስ ታክሶኖሚ ቲኦሪ መሰረት የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎችን ወደ ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ (HOTS) እንዲሸጋገሩ የተዘጋጀ መሆን አለበት። "በተለይ ከመሰረታዊ የዕውቀት ደረጃዎች (LOTS) ወደ ውስብስብ አስተሳሰብ (HOTS) ቀስ በቀስ መሸጋገር ተገቢ ነው።" በማለት Forehand (2010፣ 4) ይገልጽዋል።

የግምገማ ውህደት፡- በመጽሐፍቱ ውስጥ የተካተቱት ግምገማዎች እንደደረጃ ክፍሉ ግልጽ ግንዛቤን የሚያንፀባርቁ መሆን አለባቸው። እነሱ በክፍል ደረጃ የሚጠበቁትን ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች በትምህርታቸው ከዚያ ነጥብ እንዲያዳብሩ የሚጠበቅባቸውን አጠቃላይ ዕውቀትና ክሂሎች ለመለካት የተነደፉ መሆን አለባቸው። አምዳዊ አደረጃጀት የቋንቋ መማሪያ መፃህፍትን ለመገምገም ወሳኝ መርህ ሲሆን አስተማሪዎች ለተማሪዎች ወጥነት ያለው እና ሁሉን አቀፍ የመማር ልምድ እንዲኖራቸው ማድረግ። የአካታች ትምህርት ወጥነት እና የይዘቶች አደረጃጀት መርሆችን በማክበር፣ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፎች የተማሪዎችን የቋንቋ እድገት በትምህርታዊ ጉዞአቸው በብቃት ሊደገፉ ይችላሉ። በመጨረሻም፣ በቋንቋ ትምህርት ማዕቀፎች ውስጥ አምዳዊ አደረጃጀት ማረጋገጥ ማለት ውጤታማ እና አሳታፊ የትምህርት ቁሳቁሶችን መፍጠር ተችልዋል ማለት ነው።

## 2.1.8 ተለጣጣቂነት (Content Coherence) እና ተከታታይነት (content continuity)

"የይዘቶች ተለጣጣቂነት በትምህርት መሳርያዎች ውስጥ ያሉ ይዘቶች ከአንድ ደረጃ ወደ ቀጣይ ደረጃ በተለጣጣቂ እና በተሻሻለ መልኩ መጨመርን ያመለክታል። ይህ ተማሪዎች ውስብስብ ደረጃዎችን እንዲያገኙ ያደርጋል።" Marzano (2003 ፣52)። በዚህ ጽንሰ ሀሳብ መሰረት "ተለጣጣቂነት የተማሪ ችሎታ መጨመርን ያረጋግጣል ምክንያቱም የቀደም እውቀት ለቀጣይ እውቀት መሰረት ይሆናል።" በማለት Webb (1997 ፣18)ያጠነክረዋል ። እንደ ሙሁራኑ አባባል ይዘቶች በትኩረትና በጥልቀት ከቀለለ እውቀት ከበድ ወዳለ እውቀት እና ክሂሎች እንዲሸጋገሩ የትምህርት ቁሳቁሶች በጥንቃቄ መዘጋጀት እንዳለባቸው መረዳት ይቻላል።

እንዲሁም እንደ Porter (2002፣ 9) "ተለጣጣቂነት በዓምዳዊ አደረጃጀት ውስጥ የይዘቶች ጥልቀት እና ስፋት መጨመርን ያመለክታል። ይህ ተማሪዎች ከመሰረታዊ ደረጃ (LOTS) ወደ ከፍተኛ ደረጃ (HOTS) እንዲሸጋገሩ ያስችላል ።" በማለት ሲገልፀው ይዘቶች ከቀላል ወደ ከባድ ቀስ በቀስ መጓዝ እንዳለባቸው እንረዳለን።

ተከታታይነት በተመለከተ የትምህርት ቁሳቁሶች ተግባራት ሳይቆራረጡ በቅደም ተከተል ከመጀመርያው ምዕራፍ ወደ ቀጣይ ምዕራፍ ከቀዳሚው ደረጃ ክፍል ወደ ቀጣዩ ደረጃ ክፍል ፍሰታቸውን ጠብቀው መዘጋጀት አለባቸው። ሐቲ ይህን ሐሳብ ሲያጠናክረው "በተለይ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው፣ የማንበብ፣ የመፃፍ ተከታታይነት የተማሪ ብቃትን ያሳድጋል።" Hattie (2012፣ 92) ።

ከ Anderson & Krathwohl (2001) ስርጭት እይታ አንፃር ስንመለከተው ደግሞ፣ የይዘቶች ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት በእውቀት ደረጃዎች መካከል ያለውን ተከታታይ እና ተለጣጣቂ ይዘት መጨመር ያመለክታል። ለምሳሌ፣ ከመተግበር (Apply) ወደ መገምገም (Evaluate) ከዚያም ወደ መፍጠር (Create) ቀስ በቀስ መጨመር ተማሪዎች ወሳኝ አስተሳሰብ እንዲያዳብሩ ያግዛል። Anderson & Krathwohl (2001 ፣78) ። ይህን ሐሳብ በተመለከተ በስእላዊ መግለጫ እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል።


*ከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎች*

High order thinking skill

***መሰረታዊ የእውቀት***

***ደረጃዎች***

Low order thinking skill





ሰእል 2.1.8 LOTS እና HOTS

በአጠቃላይ ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት በትምህርት ቁሳቁሶች ውስጥ የዓምዳዊ አደረጃጀት መሰረት ናቸው። ከ Anderson & Krathwohl (2001) እይታ አንፃር ደግሞ "እነዚህ ጽንሰ ሀሳቦች ተማሪዎች ከመሰረታዊ የእውቀት ደረጃ ወደ ከፍተኛ የእውቀት ደረጃ በተከታታይ እና በተለጣጣቂ መልኩ እንዲሸጋገሩ ያረጋግጣሉ።" Marzano (2003 ፣58) ። ስለሆነም የትምህርት መሳሪያዎች በጥንቃቄ ሳይዛነፉ እርስ በርሳቸው እየተመጋገቡ ተሳስረው ተማሪዎቻችን ወደ ከፍተኛ የአስተሳሰብ አድማስ መጓዝ እንዲችሉ ተደርገው መዘጋጀት እንዳለባቸው መረዳት ይቻላል።

## 2.1.9 ብሉምስ ታክሶኖሚ (Bloom's Taxonomy 1956)

የመጀመሪያው የብሉምስ ታክሶኖሚ በ1956 በቤንጃሚን ብሉም እና ቡድኑ የተሰኘው የትምህርት ዓላማዎችን በሶስት ዋና መስኮች የከፋፈለ የመጀመሪያው ቲዎሪ ነው። ከእነዚህም ውስጥ በጣም ታዋቂው የእውቀት መስክ (Cognitive Domain) ነው። "የማሰብ ችሎታን የእውቀት መስክ (Cognitive Domain) በስድስት ደረጃዎች ከቀላል ወደ ውስብስብ እንደ ፒራሚድ አድርጎ ያቀርባል" Bloom et al., (1956፣ 201) ።




*ስእል 2.1.9 የ1956ቱ BT*

"ብሉም እና ቡድኑ ይህን ታክሶኖሚ ያወጡት የትምህርት ዓላማዎችን፣ ፈተናዎችን ለመዘርጋት፣ ትምህርትን ለመገምገም እና ተማሪዎችን ወደ ከፍተኛ የማሰብ ደረጃ ለማሳደግ ነበር። ይህ ቲዎሪ ከ40 ዓመታት በላይ በዓለም ዙሪያ የትምህርት ስርዓቶች መሰረታዊ መሳሪያ ሆኖ ቆይቷል።" Krathwohl (2002፣ 212) ። በተመሳሳይ Anderson & Krathwohl (2001 ፣3) እንደሚሉት "የ1956ቱ ታክሶኖሚ በዓለም ዙሪያ ተቀባይነት ያገኘበት ምክንያት የትምህርት ዓላማዎችን በስርዓት እና በተዋረድ አድርጎ መከፋፈሉ ነው። ይህም መምህራን፣ የመጽሐፍ አዘጋጆች፣ ፈተና አዘጋጆች እና ፖሊሲ አውጪዎች የጋራ ቋንቋ እንዲኖራቸው አድርገዋል ።" በማለት በአንድ ቋንቋ ይገልፁታል።

Marzano (2003፣ 136) እና Hattie (2012፣ 47) በተመሳሳይ እንደሚሉት፣ "የ1956ቱ የብሉም ታክሶኖሚ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ ለመሆን በጣም ተስማሚ ከሆኑት ቲዎሪዎች አንዱ ነው። ይህም የመማር-ማስተማር ሂደቱን ከቀላል ወደ ውስብስብ በሆነ መልኩ እንዲከናወን እና እንዲደራጅ ያደረገ ሲሆን፣ ይህ ቲዎሪ የተማሪዎችን ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ (Higher-Order Thinking Skills) ለማዳበር መሰረታዊ መሳሪያ ሆኖ ቆይቷል።" በማለት ሲገልፁት ጠቅለል ባለ መልኩ በትምህርት ስርዓት ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ እንዲመጣ ምክንያት የሆነ የዘመኑ ምጡቅ ቲኦሪ

እንደነበር እና አውሁን ወደ ደረስንበት የትምህርት ስርዓት ትልቅ ድልድይ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

## 2.1.10 የተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ ቲኦሪ (RBT,2001)

የታደሰው የብሉምስ ታክሶኖሚ በ2001 በLorense Anderson እና Devid Krathwohl የ1956ቱን ታክሶኖሚ በሙሉ አድሰው ያወጡት ዘመናዊው የትምህርት ቲኦሪ ነው። ዋና ዋና ለውጦቹ ደግሞ ስሞቹ ከስም ወደ ግስ መቀየር፣ የመጨረሻው ደረጃ ከመገምገም (Evaluation) ወደ ፈጠራ (Create) መቀየር እና የእውቀት ልኬት (Knowledge Dimension) መጨመር ናቸው።

Anderson & Krathwohl (2001፣ xxii) በጽሐፋቸው እንዳስቀመጡት፣ "ይህ ማሻሻያ የተደረገው የ1956ቱ ታክሶኖሚ በ45 ዓመታት ውስጥ ያጋጠሙትን ችግሮች ለማስወገድ፣ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የትምህርት ፍላጎቶችን ለማሟላት እና የተማሪዎችን ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ (HOTS) በተሻለ ሁኔታ ለማዳበር ነው ።" በማለት መነሻ ሐሳባቸውን ያስቀምጣሉ።

የAnderson & Krathwohl (2001) ስድስት ደረጃዎች ከታች ወደ ላይ ውስብስብነትን በመጨመር ደረጃ እንደሚከተለው መጥቀስ ይቻላል።

1. ማስታወስ (Remember) → መረጃን መጥቀስ፣ መዘርዘር፣ መለየት
2. መረዳት (Understand) → ማብራራት፣ ማጠቃለል፣ ምሳሌ መስጠት
3. መተግበር (Apply) → የተማረውን በአዲስ ሁኔታ መጠቀም

→ ማስታወስ (Remember) + መረዳት (Understand) + መተግበር (Apply) =መሰረታዊ የእውቀት ደረጃ (LOTS) እነዚህ ቀስ በቀስ እንደየ ደረጃ ክፍሉ፣ ተማሪዎች ዕድሜ፣ ማህበረ ኢኮኖሚ ማእከል በማድረግ ቀለል ባሉ ይዘቶች ደረጃ በደረጃ የሚማሩበት ነው።


4. መተንተን (Analyze) → መከፋፈል፣ መከራከር፣ ምክንያትና ውጤት ማየት

5. መገምገም (Evaluate) → መፈተሽ፣ መከራከር፣ ውሳኔ መስጠት፣ ተገቢነት መገምገም

6. መፍጠር (Create) ← ከፍተኛው ደረጃ → መንደፍ፣ መፃፍ፣ ማፍለቅ፣ አዲስ ነገር መፍጠር

→ መተንተን (Analyze) + መገምገም (Evaluate) + መፍጠር (Create)= ከፍተኛ የእውቀት ደረጃ (HOTS) ፣ እዚህ ላይ ተማሪዎች በሂደት ቀለል ባሉ ተግባራት ሲለማመዱ ቆይተው ከበድ ፣ ጠጠር ብለው ተማሪዎች እንደየ እድሚያቸው ቀስበቀስ ወደ ምርምርና ፈጠራ የሚሸጋገሩበት ከፍተኛ ደረጃ ነው።

እነዚህ ደረጃዎች የመማር ማስተማር ትምህርት ዓላማዎችን ለመቆጣጠር ምን ያህል ወሳኝ እንደሆኑና ቀለል ባለ መንገድ መጠቀም እንደምንችል መረዳት ይቻላል። ቀጥሎ በቀረበው ስእል የእወቅት ደረጃዎች ከላይ ወደታች እና ከታች ወደላይ በመገኛ ቋንቋቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል።





*4ስእል 2.1.10 (RBT 2001)*

Anderson & Krathwohl (2001) በፈጠራ እና በግምገማ መከከል የተደረገው ለውጥ በተመለከተ በዓለማችን ለውጥ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ሐሳቡን በተመሳሳይ ደረጃ ይገልፁታል። Krathwohl (2002 ፣215) በግሉ የግምገማ መጽሐፉ እንዳስቀመጠው፣ "ፈጠራ "Create" የመጨረሻውና ከፍተኛው ደረጃ የሆነበት ምክንያት ዘመናዊው ዓለም የሚፈልገው እውቀትን መቀበል ብቻ ሳይሆን አዲስ ነገር መፍጠር፣ መፈጠር እና ፈጠራን መጠቀም ስለሆነ እና፤ ከ1956ቱ ታክሶኖሚ የተሻለ የሆነው የተማሪ የእውቀት ለውጥን በተሻለ ሁኔታ የሚተነትን እና የሚለካ ስለሆነ ነው።" ይለዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው በተለይ የፈጠራ (Create) ደረጃ መኖር ተማሪዎች በ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚያስፈልገውን የፈጠራ ችሎታ፣ የችግር መፍቻ ችሎታ እና የፈጠራ አስተሳሰብ እንዲያዳብሩ እንደሚያደርግ ነው። Hattie (2012፣ 52) እና Marzano & Haywood (2021፣ 89) "RBT ከ1956ቱ ታክሶኖሚ የተሻለው የተማሪ እድገትን በተሻለ ሁኔታ የሚያንፀባርቅ እና የሚለካ ስለሆነ ነው። በተለይ የፈጠራ (Create) ደረጃ መኖር ተማሪዎች በዘመናዊው ዓለም የሚያስፈልገውን የፈጠራ ችሎታ እና የችግር መፍቻ ችሎታ እንዲያዳብሩ ያደርጋል።" በማለት በግምገማና በፈጠራ መካከል የተደረገው ለውጥ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ይገልፁታል።

በተጨማሪም እነ Mazengia et al. (2019፣28) ደግሞ "የRBT ትልቁ ጥንካሬ የእውቀት ልኬት (Knowledge Dimension) መጨመሩ ነው። ይህም የእውቀት ዓይነቶችን (Factual, Conceptual, Procedural, Metacognitive) በግልጽ በመለየት መምህራን እና መጽሐፍ አዘጋጆች የትኛውን ዓይነት እውቀት በምን ደረጃ ማስተማር እንዳለባቸው በተሻለ መንገድ እንዲያቅዱ አድርጓል ።" በማለት ምን ያህል ግልጽና ጥንካሬን ፈጥሮ እንደታደሰ የሚደግፍ ሐሳብ መሆኑን እንረዳለን። የእውቀት

ደረጃዎች አቀማመጣቸው በሚመለከተው የሰንጠረዥ ስእል በግልጽ ቀርቧል።



The two-dimensional framework

The Cognitive Process Dimension

The Knowledge Dimension

| | remember | understand | apply | analyze | evaluate | create |
|---|---|---|---|---|---|---|
| Fact | Remember facts | Understand facts | Apply Facts | Analyze using Facts, Concepts, Principles and Procedures | Evaluate using Facts, Concepts, Principles and Procedures | Create using Facts, Concepts, Principles and Procedures |
| Concept | Remember concepts | Understand concepts | Apply Concepts | | | |
| Procedure | Remember procedures | Understand procedures | Apply Procedures | | | |
| Meta.cognitive | Remember metacog. strategies | Understand Metacog. Strategies | Apply Metacog. Strategies | Analyze Meta. Strategies | Evaluate Metacog. Strategies | Create Metacog. Strategies |
| | Knowledge | | skill | Ability | | |

*ስእል 2.1.10 ሀ Knowledge Dimension*

## 2.2 የተዘማጅ ጥናቶች ቅኝት

እስካሁን በቀጥታ በትግርኛ ቋንቋ የክሂሎች ይዘቶች አምዳዊ አደረጃጀት ከታደሰው የብሉምስ ታክሶኖሚ ትንተና ስርጭት እይታ አኳያ ትኩረት በማድረግ የተካሄደ ጥናት ማግኘት አልተቻለም። ይህ ሲባል ይህን ርዕስ እንደ ዋና የጥናት ርእሰ ጉዳይ አንስቶ ከዘመናዊው የአግባብነት ጽንሰ ሀሳብ አኳያ የመረመረ ጥናት አለመኖሩን ለመጠቆም እንጂ በጥቅሉ በትግርኛ ቋንቋ ክሂሎችም ሆነ ሌሎች ዓውድ ላይ በተናጠል ምንም አይነት ጥናት አልተገኘም ለማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። ስለሆነም ከስር የተዘረዘሩት ቀደምት ጥናቶች ማንሳቱ በጥናታቸው ያነሷቸውን ጥያቄዎች፣ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የተጠቀሙባቸው የአጠናን ዘዴዎች እና ያገኟቸውን ግኝቶች ለመገንዘብ ስለሚያስችል በሁለት ሀገር አቀፍ  የትምህርት ዓይነቶች ማለትም አንድ የኢንግሊዘኛ እና ሁለት የስነ ዜጋ እና ስነ ምግባር ባጠቃላይ ሶስት የተማሪ መጽሐፎች፤ ትኩረት ያደረጉ ጥናቶች ተቃኝተዋል።

ስለሆነም ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው የኢትዮጵያ ስርዓተ ትምህርት መሰረት አድርገው በተዘጋጁ የተማሪ መፅሐፍ ከተደረጉ ጥናቶች Seyd (2023) በእንግሊዘኛ፣ Tefera (2022) እና Demeke (2021) የስነ ዜጋ እና ስነ ምግባር ትምህርት መማርያ መፃህፍት በጠቅላላ ሶስት ጥናታዊ ቅኝቶች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተዛምዶ እና ልዩነት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የመጀመርያው ተመሳሳይ ጥናት Seyd (2023) በኢትዮጵያ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የእንግሊዝኛ መማርያ መጽሐፎች ውስጥ ያሉ የንግግር ተግባራትን ከተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ እይታ አንፃር መተንተን አጠቃላይ ዓላማ ይዞ ምርምሩን ያካሄደ ሲሆን፤ ጥናቱ በተለይ የንግግር ተግባራት መሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች፣ እና የከፍተኛ የማሰብ ደረጃዎች (HOTS) ስርጭትን ያጠናል። ስለሆነም በመጽሐፎቹ ውስጥ ያሉ የንግግር ተግባራት (speaking tasks, activities, questions) በ Anderson & Krathwohl (2001) ስድስቱ የእውቀት ደረጃዎች መሰረት በማድረግ ተከፋፍለዋል። የውጤት ትንተናው Seyd (2023) እንዳመለከተው፣ በመጽሐፍቱ ውስጥ ያሉ የንግግር ተግባራት በተለይ ዝቅተኛ የማሰብ ደረጃዎች (LOTS) ላይ ያተኮሩ ናቸው። ዝርዝር ስርጭቱ በውጤት ቅደም ተከተል መተግበር (Apply) 60%፣ መተንተን (Analyze)

25%፣ መፍጠር (Create) 5%፣ መረዳት (Understand) 8%፣ መገምገም (Evaluate) 2%፣ ማስታወስ (Remember) 0% ሲሆን፤ ይህ ውጤት እንደሚያሳየው፣ LOTS በድምሩ 68% ይይዛል፤ ይህም የንግግር ተግባራት በተለይ በተግባራዊ ያተኮሩ መሆናቸውን ያመለክታል። ነገር ግን "መፍጠር" ከፍተኛው የማሰብ ደረጃ በጣም ዝቅተኛ (5%) ውጤቱ ያመለክታል። Seyd (2023) እንደሚገልፀው፤ ዝቅተኛ የእውቀት ደረጃዎች ተግባራት የበላይነት መኖር የተማሪዎችን የንግግር ፈጠራ ችሎታ ሊገታ ይችላል። seyd (2023) ከዚህ ጥናት ያለው ልዩነት የዓምዳዊ አደረጃጀት (vertical alignment) አለማጥናቱ፤ በእንግሊዝኛ የትምህርት ዓይነት መሆኑ፤ በተቀሩት ሶስት ክሂሎች በጥናቱ አለማካተቱ ተጠቃሽ ናቸው።

በሁለተኛ ደረጃ ላይ የተቃኘው የሐገር ውስጥ ጥናት Tefera (2022) በኢትዮጵያ የ10ኛ ክፍል የስነዜጋ እና ስነ ምግባር መማርያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ የተግባር ይዘቶችን ከተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ እይታ አኳያ መገምገም ይዞት የሚነሳ አጠቃላይ አላማ ሲሆን፣ጥናቱ በተለይ የእውቀት ደረጃዎች ስርጭትን፣ የተግባር መልመጃዎች ዓይነቶችን ሲሆን፣ የከፍተኛ የማሰብ ደረጃዎች HOTS ተሳትፎን አጥንቷል። (Content Analysis) ዘዴን በመጠቀም ተካሂዷል። የ10ኛ ክፍል የስነ ዜጋ እና ስነ ምግባር ትምህርት መማርያ መጽሐፍ (2008 ዓ/ም) ሙሉ በሙሉ ተመርምሯል። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ተግባራት፣ ጥያቄዎች፣ እና እንቅስቃሴዎች በ Anderson & Krathwohl (2001) ስድስቱ የእውቀት ደረጃዎች መሰረት ተከፋፍለዋል። የውጤት ትንተና በመቶኛ (%) እና በቁጥር ተደርጎ ቀርቧል።የጥናቱ ውጤትም Tefera (2022) እንዳመለከተው፣ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ተግባራት በተለይ ከፍተኛ የማሰብ ደረጃዎች (HOTS) ላይ ያተኮሩ ናቸው። ዝርዝር ስርጭቱ እንደሚከተለው ነው። መተንተን (Analyze) 45%፣ መገምገም (Evaluate): 30%፣ መፍጠር (Create) 15%፣ መተግበር (Apply): 8%፣ መረዳት (Understand): 2%፣ ማስታወስ (Remember): 0% ድምር ውጤት እንደሚያሳየው ደግሞ HOTS 90% LOTS ደግሞ 10% ይይዛል፤ ይህም የስነ ዜጋ እና ስነ ምግባር ትምህርት ዓላማዎች ከ (የዜግነት እሴት፣ የውሳኔ አሰጣጥ፣ የችግር መፍቻ) ጋር የተገኘው ውጤት እንደሚጣጣም አረጋግጧል።

Tefera (2022) ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ተመሳሳይነት በኢትዮጵያ ስርዓተ ትምህርት በተቀረፀው የ10ኛ ክፍል የስነ ዜጋ እና ስነ ምግባር የመማርያ መፅሐፍ ማጥናቱ እና Anderson & Krathwohl (2001) ቀዳሚ ሞዴል ተጠቅሞ የተማሪዎችን የዕውቀት ደረጃ (Cognetive level) መገምገሙ ሲሆን፤ ልዩነታቸው ደግሞ ዓምዳዊ አደረጃጀት አለማጥናቱ እና በተከታታይ የክፍል ደረጃ ትኩረት አለማድረጉ፤ እንዲሁም የተለያዩ የትምህርት ዓይነት መሆናቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የመጨረሻ እና ሶስተኛው ተዛማጅ ጥናት ከላይኛው ተመሳሳይ የትምህርት ዓይነት የሆነው በDemeke (2021) የተጠናው ሲሆን፤ ከዚህ ጥናት ጋር በብዙ ነጥቦች ላይ ተመሳሳይነት አላቸው። ሁለቱም በኢትዮጵያ ስርዓተ ትምህርት ውስጥ በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የተማሪ መጽሐፎች ላይ ያተኮሩ እንደመሆናቸው፤ በተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ (Revised Bloom’s Taxonomy – Anderson & Krathwohl (2001) መሰረት የተግባራትን የእውቀት ደረጃ በይዘት ትንተና (content analysis) እና በመር አቀራረብ (directed approach) ያጠኑ ሲሆን፤ የDemeke ጥናት ውጤት እንደሚያመላክተው በመጽሐፎቹ ውስጥ የከፍተኛ ደረጃ የእውቀት ተግባራት (HOTS) ድርሻ በጣም ዝቅተኛ (<20%) መሆኑን እና የመሰረታዊ ደረጃ ተግባራት (LOTS) እጅግ በጣም የበላይነት ያላቸው መሆናቸውን አረጋግጠዋል። በመካከላቸው ተመሳሳይነት እንዳላቸው ሁሉ ልዩነቶችም አሏቸው። የDemeke ጥናት በስነዜጋ እና ስነምግባር መጽሐፎች ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ይህ ጥናት ደግሞ በትግርኛ ቋንቋ መጽሐፎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፤ በተጨማሪም ይህ ጥናት በተግባራቱ ዓምዳዊ አደረጃጀት (vertical alignment) ላይ ብቻ ሳይሆን በያንዳንዱ ደረጃ ክፍል ያሉ የምዕራፎች ተያያዥነትም ትንተና ያካተተ ነው፤ የDemeke ጥናት ደግሞ በዓምዳዊ አደረጃጀት ማለትም ከ9ኛ ወደ 10ኛ ክፍል ያለው ተያያዥነት ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። በአጠቃላይ የDemeke (2021) ጥናት በኢትዮጵያ የተማሪ መጽሐፎች ውስጥ የHOTS ዝቅተኛነት ችግር መዋቅራዊ ችግር መሆኑን አረጋግጧል።

# ምዕራፍ ሶስት የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናት ስልት

በ2008 ዓ/ም ታትመው ስራ ላይ ባሉ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፎ ውስጥ ያሉ የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀትን ከተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ Anderson & Krathwohl (2001) የዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት አይታ አኳያ መገምገም። የሚለውን የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የጥናቱ ንድፍ ቅይጥ (Mixed Approach Method) ተጠቅሟል። ከዓይነታዊ (Descriptive Qualitative Method) ገላጭ የምርምር ስልትን እንዲሁም፤ መጠን ገላጭ (Descriptive quantitative Method) በማጣመር ተጠንቷል። ይህ የሆነበት ዋና ምክንያት ጥናቱ የሚሰበስባቸው መረጃዎች ከዓይነታዊ በቃላት ገለፃ፤ እንዲሁም በመጠን የተገኙ መረጃዎች በቁጥር፣ በመቶኛ እና በሰንጠረዥ መቅረብ ስላለባቸው ነው።

በይዘት ትንተናው (content analysis) ውስጥ መር የይዘት ትንተና (directed content analysis) ተጠቅሞ ተግባራቱ በተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ (Anderson & Krathwohl, 2001) መሰረት ተመድበው ተተንትነዋል። ይህን ሐሳብ Hsieh & Shannon (2005፣ 1281) "መር የይዘት ትንተና (directed content analysis) ቀድሞ ከተሰጠ ቲዎሪ ወይም ግኝት በመነሳት የመጀመሪያ ኮዶችን ይፈጥራል።" ይህ አቀራረብ ተግባራቱን በተጨባጭ የእውቀት ደረጃዎች መለየት፣ መቁጠርና መቶኛ ማስላት አስችሏል። በዚህም መሰረት "የይዘት ትንተናው ቁጥራዊ ውጤቶችን (frequency & percentage) በማፍራት የመልእክት ባህሪያትን በስልታዊ፣ በተጨባጭና በቁጥራዊ መንገድ መገምገም ነው።" በማለት Neuendorf (2017) እና Hsieh & Shannon (2005)። ሲገልፁት፤ ባጠቃላይ ከምሁራኑ ሐሳብ የምንረዳው መር የይዘት ትንተና ለዚህ ጥናት የተግባራት ከቀላል ወደ ከባድ መደራጀት ብሎም ተከታታይነታቸውን ለመገምገም ወሳኝ መሆኑን ነው።

ተጋናኝ ትይዩ ቅይጥ ስልት (Convergent Prallel Mixed-Methods Design) በመጠቀም፤ የይዘት ትንተናው ቁጥራዊ ውጤቶች እና ከቃለ-መጠይቅ የተገኘው ዓይነታዊ መረጃ በተመሳሳይ ጊዜ ተሰብስቦ፣ በተናጠል ተተንትኖ፣ ከዚያም ውጤቶቹ ተነፃጽረው ተተርጉመዋል። እንደ Creswell & Poth (2018፣ 54) "ይህ ስልት የመጽሐፎቹ ይዘት በተጨባጭ መለኪያዎች መለካት እና በተመሳሳይ ጊዜ

የተሳታፊዎቹ አመለካከት እና ልምድ በጥልቀት መረዳት የሚያስችል ነው።" እንደገለፁትም ተተግብሯል።

ሲጠቃለል ቅይጥ የጥናት ስልት የተመረጠበት ዋና ምክንያት መጠናዊ (Quantitative) በ2008 ዓ/ም ታትመው ስራ ላይ ያሉትን የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ የተማሪ መጽሐፎች ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂሎች ተግባራት በመጠናዊ ትንተና ዘዴ ተተንትነዋል። ይህ ዘዴ በተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ (Anderson & Krathwohl፣ 2001) መሰረት ለመገምገም ምን ያህል ወሳኝ መሆኑ Krippendorff (2019፣ 24) "የእውቀት ደረጃዎችን በተጨባጭ መለየትና መቁጠር ስለሚያስችል ተመራጭ ነው።" ይሉታል። ዓይነታዊ (Qualitative) ከመጽሐፍ አዘጋጅ 1 ሰው እና ከልምድ ያላቸው መምህራን 3 ሰዎች የተገኘው መረጃ በገለፃ ወይም በሐተታ መልክ ተተንትነዋል። እንደ Braun & Clarke (2006፣ 79) ገለፃ፣ "የጭብጥ ትንተና በመረጃ ውስጥ ያሉ ስርዓቶችን (ጭብጦችን) ለመለየት፣ ለመገምገምና ገለፃ ለማድረግ የሚያስችል ዘዴ ነው። ቢያንስ መረጃ ሰብስበን በበለፀገ ዝርዝር በማደራጀት ይገለፃል።" ይህ ዘዴ ተሳታፊዎች ስለ መጽሐፉ ያላቸውን እይታ፣ ልምድና አስተያየት በጥልቀት ለመረዳት ተስማሚ ሆኖ ተገኝቷል። የውጤቶች መቀናጀት (Integration) የሰነድ ትንተና ውጤት ፤ ከቃለ መጠይቅ ትንተና ውጤት ጋር (Triangulation) ተነፃጽሯል። እንደ Creswell & Plano Clark (2018፣ 219) ገለፃ፣ "በተቀናጀ ስልት ውስጥ የመጠናዊ እና የዓይነታዊ ውጤቶች መቀናጀት የጥናቱን ትክክለኛነት እና ታማኝነት በእጅጉ ያጠናክራል።" በማለት የውጤቶች መቀናጀትን ለውጤቱ ታማኝነት ወሳኝ መሆኑ ያረጋግጣሉ። ስለዚህ ይህ የተቀናጀ ትይዩ ቅይጥ ስልት የመጽሐፉን ይዘት በቁጥር በመለካት እና የባለሙያዎችን እይታ በመግለጽ የጥናቱ ዓላማ እንዲሟላ አድርጎታል።

## 3.2 የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች

ይህ ጥናት እንደ ቅይጥነቱ ሁለት ዋና ዋና የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች ተጠቅምዋል። እነሱም ሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ ሲሆኑ፤ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 3.2.1 ሰነድ ፍተሻ

ዋናው የመረጃ ምንጭ በ2008 ዓ/ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጁና ስራ ላይ ያሉ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ የተማሪ መፃህፍት ናቸው። በመጽሐፎቹ ውስጥ ያሉ የቋንቋ ክሂሎች ተግባራት በአጠቃላይ 779 በተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ (Anderson & Krathwohl, 2001) መሰረት ለመገምገም የሰነድ ፍተሻ መሳርያ (Checklist) ተዘጋጅቶ ተተግብሯል።

ይህ መሳርያ ስድስት ዋና ዋና የእውቀት ደረጃዎችን ያካተተ ነው። እነሱም ማስታወስ (Remembering)፣ መረዳት (Understanding)፣ መተግበር (Applying)፣ መገምገም (Analyzing)፣ መገምገም (Evaluating) እና መፍጠር (Creating) ሲሆኑ፤ እያንዳንዱ ተግባር በእነዚህ ደረጃዎች መሰረት ተመድቦ በኤክሴል(Excel) ውስጥ ተደራጅተዋል። "ይህ መሳርያ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ተግባራት በተጨባጭና በስርዓት መለየት ያስችላል።" Creswell (2014፣ 201)።

### 3.2.2 ቃለ መጠይቅ

የመጽሐፉን ይዘት ከተግባራዊ ልምድ አኳያ ለመረዳት ከሚከተሉት ተሳታፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ተካሂዷል። በዚህ ጥናት ውስጥ ከፊል የተዋቀረ ቃለ መጠይቅ (Semi-structured Interview) ተጠቅሟል።

እንደ ያለው (2011፣179)፣ "ከፊል ነፃ የተባለበት ምክንያት መላሹ የራሱን ሀሳብ ለመስጠት ነፃ የሚያደርገውና በተወሰኑ አማራጮች ተገድቦ የግል ሀሳቡን እንዳይገልጽ ማዕቀብ የሚያደርግበት አይደለም"። በማለት ይገልፀዋል።

ስለሆነም ይህ የቃለ መጠይቅ ዓይነት የተመረጠበት ምክንያት መላሾች ተጨማሪ አስተያየት እንዲሰጡ ስለሚያስችል፤ የተግባራዊ ተሞክሮን በጥልቀት ለመረዳት ተስማሚ ስለሆነም ጭምር ነው።

ስለዚህ የመጽሐፉ ዋና አዘጋጅ 1 ሰው፣ በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል ትግርኛ ቋንቋ ከሚያስተምሩ ልምድ ያላቸው መምህራን 3 ሰዎች ጋር ቃለ መጠይቁ ግልጽ እና ተግባቦታዊ በሆነ መንገድ ተተግብሯል። በጥናቱ ዓላማ መሰረት የተዘጋጁ ቃለ መጠይቆቹ በድምጽ ተቀርፀው፣ በተሳታፊዎች ፈቃድ ተካሂደዋል፤ ሆኖም ግን

የመጽሐፎቹ አዘጋጅ ባለ ሙያ ለመቀረጽ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምክንያት ሐሳቦቹን በማስታወሻ ለማደራጀት ተችሏል። በመምህራን አማካይ የአንድ ቃለ መጠይቅ ርዝመት 26′ ደቂቃ ተቀርጾዋል። Creswell & Poth (2018፣ 149)። "ይህ መሳርያ የመፃፉን ይዘት ከተግባራዊ ልምድ አኳያ በጥልቀት ለመረዳት ያስችላል።" በማለት ይገልፁታል።

ባጠቃላይ ሁለቱም መሳርያዎች ማለትም ሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ እርስ በርስ የሚደጋገፉ ሆነው ተተግብረዋል። የጥናቱ ቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ተገቢነት እና ከጥናቱ ዓላማዎች ያላቸው ተዛምዶ 33 ዓመት የስራ ልምድ እና በትግርኛ ቋንቋ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው አንድ መምህር እና አንድ የዓብዪ ዓዲ የልዩ ፍላጎት የኮሌጅ መምህር ተረጋግጠው ስራ ላይ ውለዋል። ስለሆነም የመጽሐፉ የክሂሎች ይዘት ተግባራት በሚገባ በቁጥር እና በሐተታ ተገምግመው እና ተመሳክረው በተጨባጭ በትንተናው ስር ቀርበዋል፤ ይህም የጥናቱን ታማኝነት እና ተጨባጭነትንም ትንተናው በነዚህ ባለሙያዎች መገምገሙ (Triangulation of Data Sources) ከፍ እንዲል ያደርገዋል።

## 3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ይህ ጥናት ቅይጥ ዘዴን በመጠቀሙ ለመጠናዊ እና ለዓይነታዊ ክፍል የተለያዩ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች ጥናቱ ላይ ተግብሯል።

### 3.3.1 የክፍል ደረጃና የመጽሐፍ አመራረጥ

የጥናቱ ዋና ሰነድ በ2008 ዓ/ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጁና በትግራይ ክልል ስራ ላይ ባሉት የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ የተማሪ መፃህፍት ናቸው። እነዚህ ክፍሎች በዓላማዊ ናሙና አመራረጥ ዘዴ (Purposive Sampling) ተመርጠዋል። የተመረጡበት ምክንያት፤ በኢትዮጵያ ስርዓተ ትምህርት መሰረት እንደ የኢትዮጵያ ትምህርት ሚኒስተር ገለፃ "የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከ9ኛ–12ኛ የመጨረሻ ደረጃ በመሆን የተማሪዎች ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ (HOTS) መጠናከር አለበት።" MoE (2010፣ 8) ። ስለሆነም በዚህ ጥናት ከመጨረሻው ሳይክል የመጀመርያ የሆነው ከ9ኛ-10ኛ ክፍል መማርያ መጽሐፍ ከፍተኛውን የማሰብ ችሎታ በሚያዳብር መልኩ መዋቀሩን ለመፈተሽ ተመርጧል።

### 3.3.2 የመጽሐፉ አዘጋጆች ናሙና አመራረጥ

የመጽሐፉ ዋና አዘጋጆች ሶስት ባለሙያዎች ተመርጠው የነበሩ ቢሆንም 2ቱ በጡረታ እና በጤና ምክንያት ባለመገኘታቸው 1 በስራ ላይ ያሉ ዋና አዘጋጅ ብቻ በመገኘታቸው በዓላማዊ ናሙና አመራረጥ ዘዴ (Purposive Sampling – Expert Sampling) ተመርጠዋል። የተመረጡበት ምክንያት ደግሞ፦

- መጽሐፉን በቀጥታ ያዘጋጁት እና የይዘቱን ዓላማ በጥልቀት ስለሚያውቁ።
- በአዘገጃጀት ሂደቱ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ ስለነበሩ።
- በትምህርት አወቃቀር እና በትግርኛ ቋንቋ ትምህርት ረገድ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ስለሆኑ ነው።

ስለሆነም የመጽሐፉ ዋና አዘጋጆች በባለሙያ ናሙና አመራረጥ ዘዴ (Expert Sampling) ዓላማ ተኮር ተመርጠዋል። እንደ Patton (2015፣ 267) ገለፃ፣ "ይህ ዘዴ ተመራማሪው ከሌላ ሰው የማያገኘው ጥልቅ እውቀት በሚያስፈልገው ጊዜ ይጠቀማል።" በዚህ ጥናት ውስጥ የመጽሐፉን ዓላማና የተግባራቱን ሁኔታ በጥልቀት መልስ መስጠት የሚችለው ዋና አዘጋጁ ብቻ ስለሆነ በዚህ ዘዴ ተመርጧል።

### 3.3.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በ9ኛና 10ኛ ክፍል ትግርኛ ቋንቋ ቢያንስ 30 ዓመታትና ከዚያ በላይ ያስተማሩ መምህራን (3 ሰዎች) በዓላማዊ ናሙና አመራረጥ ዘዴ (Purposive Sampling – Criterion Sampling) ተመርጠዋል። የተመረጡበት መስፈርት ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል።

- ከ2008 ዓ/ም ጀምሮ መጽሐፉን በቀጥታ ያስተማሩ ስለሆኑ።
- በትግርኛ ቋንቋ ትምህርት ቢያንስ ከ30 ዓመታት በላይ ልምድ ያላቸው ስለሆኑ።
- የመጽሐፉን ይዘት ከተግባራዊ ልምድ አኳያ ለመገምገም ችሎታ ያላቸው እና በሞያው የሁለተኛ ዲግሪ ባለ ሞያ መሆናቸው ጭምር ነው።

እነዚህ መምህራን አጥኚው ከሚሰራበት ዓይደር አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሆን ተብለው ተመርጠው የተለያዩ ልምዶችን እንዲወክሉ ተደርገዋል።

ባጠቃላይ ሁሉም ናሙናዎች (መጽሐፎቹ፣ አዘጋጆች እና መምህራን) በዓላማዊ ናሙና አመራረጥ ዘዴ (Purposive Sampling) ተመርጠዋል። እንደ Creswell (2014፣ 158) ገለፃ "ይህ ዘዴ በተለይ ለቅይጥ ጥናት ተስማሚ ነው። ምክንያቱም የተመረጡት ተሳታፊዎች የጥናቱን ዓላማ በተሻለ መልኩ ለመመለስ በቂ እውቀትና ልምድ ያላቸው ሆነው ስለሚመረጡ ነው።" በማለት ይገልፀዋል።

## 3.4 የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት በ2008 ዓ/ም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር በተዘጋጁና በመላው ሐገሪቱ ስራ ላይ በዋሉ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ የተማሪ መጽሐፍት ላይ የተካሄደ ነው። የመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለገሉትም እነዚህ የተማሪ መፃህፍት ናቸው።

ስለሆነም የመጽሐፉ ዋና አዘጋጅ በመቐለ ከተማ በትግራይ ትምህርት ቢሮ የሚሰሩ ባለሙያ ሲሆኑ፤ ቃለ መጠይቁ በቢሮው ውስጥ ተካሂዷል። የተቀሩት ሶስት መምህራን ደግሞ በመቐለ ከተማ ዓይደር ክፍለ ከተማ በሚገኘው ዓይደር አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ፣ የማስተርስ ዲግሪ ባለሙያዎች እና ከ30 ዓመታት በላይ የስራ ልምድ ያላቸው ናቸው። ቃለ መጠይቆቹም በትምህርት ቤቱ ውስጥ በተረጋጋ አካባቢ ተካሂደዋል።

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ጥናቱ ከታቀደለት ዓላማ እንዲደርስ ተገቢ የመረጃ መተንተኛ ስልት በትኩረትና በተገቢው መንገድ መምረጥ ግድ ይላል። ስለሆነም የመረጃ አተናተን ዘዴ ሂደታዊ እና ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ለመተንተን ምን ያህል ትኩረት ማድረግ እንዳለብን ለመግለጽ "ጥሩ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ አዘጋጅቶ፣አስተማማኝና ትክክለኛ መረጃ ሰብስቦ፣የተገኘው መረጃ በተገቢው መንገድ ካልተተነተነ ዞሮ ዞሮ መጨረሻው ስህተት ነው የሚሆነው ወይም ምርምሩ መሆን ወደማይገባው አቅጣጫ እንዲጓዝ ይሆናል።" ያለው (2011፣233) በማለት ይገልፀዋል።

በመሆኑም ይህ ጥናት የተቀናጀ ትይዩ ቅይጥ ዘዴ (Convergent Parallel Mixed Methods Design) በመጠቀሙ የመረጃ ትንተናውም በሁለት ትይዩ እና እርስ በርስ በሚደጋገፉ መልኩ ተካሂዷል። Creswell & Plano Clark (2018፣ 218–225) ገለፃ፣ "የመጠን እና የዓይነት መረጃዎች በተናጥል ተተንትነው፤ ከዚያም ውጤቶቹ ተነፃጽረው (triangulation) መተርጎም አለባቸው።" በማለት ጠንካራነቱን ይገልፁታል። በተመሳሳይ መንገድ Creswell & Poth (2018፣ 260) "ውጤትን በሁለት ወይም ከዚያ በላይ (Triangulation) ማመሳከርያ መሳርያዎች ማረጋገጥ የመረጃው ታማኝነት ከፍ ያደርገዋል።" በማለት ይገልፁታል።

ከዚህ አኳያ አንደኛው መጠንን መሰረት በማድረግ በ2008 ዓ/ም የታተሙ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ የተማሪ መጽሐፎች ውስጥ ያሉ 779 የቋንቋ ክሂሎች ተግባራት 9ኛ ክፍል (407) ፣ 10ኛ ክፍል (372) ይዘቶች ተለይተው በይዘት ትንተና ዘዴ ተተንትነዋል። የመጀመርያው ስራ የነበረው ኮድ ማድረግ (Coding) ሲሆን፣ እያንዳንዱ ተግባር በተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ (Anderson & Krathwohl, 2001) መሰረት ተከፋፍሏል። እነሱም መሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች LOTS የሚባሉት፤ ማስታወስ (R1)፣ መረዳት (U2)፣ መተግበር (A3) እና ከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎ (HOTS) የሆኑት፤ መተንተን(A4)፣ መገምገም(E5)፣ መፍጠር (C6) ናቸው። ቀጥሎም ድግግሞሽ እና መቶኛ በማስላት በማይክሮሶፍት ኤክስኤል (Microsoft Excel) ውስጥ የእያንዳንዱ የእውቀት ደረጃ ድግግሞሽ፣ በመቶኛ እና በሰንጠረዥ ተዘጋጅተዋል፤ የምዕራፎች ተያያዥነት በመገምገም በአንድ የክፍል ደረጃ መጽሐፍ ውስጥ ከምዕራፍ ወደ ምዕራፍ የእውቀት ደረጃ ተከታታይነት ተፈትሿል። በመጨረሻም የዓምዳዊ ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት በመገምገም (Vertical Alignment) ከ9ኛ ወደ 10ኛ ክፍል የHOTS እና LOTS መጨመር ወይም መቀነስ ተተንትኗል ።

ሁለተኛው ዓይነትን መሰረት በማድረግ የሚሰበሰቡ መረጃዎች በዋናነት ስለሰነዱ በቃለ መጠይቅ ከመምህራን እና ከመጽሐፉ አዘጋጅ የተገኘ መረጃ ከቁጥር ይልቅ ቃላትን ተጠቅሞ ለመተንተን በበለጠ ስለሚመች በገለፃ መልክ በማቅረብ በዓይነታዊ የምርምር አቅጣጫ ተከትሎ ተተንትኗል። ስለሆነም ለመጽሐፍ አዘጋጅ አንድ ባለሙያ ለሶስቱም ዓላማዎች ከክፍል ደረጃ በስተቀር ተመሳሳይነት ያላቸው ለያንዳንዳቸው አራት አራት ጥያቄዎች እና አንድ ማጠቃለያ ጥያቄ በድምር አስራ ሶስት ጥያቄዎች፤

እንዲሁም የረጅም ዓመታት የስራ ልምድ ያላቸው የደረጃ ክፍሉ ሶስት መምህራን ለያንዳንዱ ዓላማ አራት አራት ጥያቄዎች እንዲሁም አንድ አንድ የማጠቃለያ ጥያቄዎች በድምር አስራ አምስት ጥያቄዎች ተዘጋጅተው አንድ የልዩ ፍላጎት የዓብዪ ዓዲ መምህር እና አንድ የበርካታ ዓመታት የስራ ልምድ ያላቸው የትግርኛ ቋንቋ የሁለተኛ ዲግሪ ባለሙያ የሆኑ መምህር ተገምግመው ማስተካከያ ከተሰጣቸው በኋል ስራ ላይ የዋሉ ሲሆኑ፤ መረጃው ተሰብስበው ከተተነተኑ በኋላም የመረጃዎቹ አስተማማኝነት እና ትክክለኛነት ከቃለ መጠይቅ እና ከሰነድ ፍተሻው የተገኙ መረጃዎች ተመሳሳይነታቸውን በእነዚህ ባለሙያዎች ከተረጋገጡ በኋላ የተገኘው የቃለ መጠይቅ መረጃ ያቀረቡትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ በዓይነታዊ ትንተና ዘዴ እንዲሁም ከመጽሐፍቱ 779 ተግባራት የተገኙ መረጃዎች በቀዳሚ የይዘት ትንተና (Dairect content analysis) መሰረት ተተንትኗል።

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት መተንተኛ ዘዴ በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች የሚደራጁቱ በዓይነታዊ የመረጃ ስልት ሲሆን የተመረጠበት ዋና ምክንያት ጥናቱ በገለፃ መልክ በመቅረቡ ሲሆን ሌላኛው ከሰነድ ፍተሻው በመር (directed content analysis) መሰረት የተገኙ መረጃዎች ደግሞ በቁጥር፣ በመቶኛ እና በሰንጠረዥ መልክ ስለሚቀርቡ መጠንን መሰረት አድርገው የሚተነተኑ ሲሆን ሁለቱም በማጣመር በቅይጥ የትንተና ዘዴ ይተነተናሉ።

# ምዕራፍ አራት፦ የመረጃ ትንተና

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ ውጤቶችን ከይዘት ትንተና እና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በዋናነት በሰንጠረዥ መልክ የቀረቡ መረጃዎች በአጠቃላይ በቅይጥ የመረጃ ስልት (mixed method) ቀርበዋል። ትንተናው በጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች መሰረት ተደራጅቶ የይዘቶች ዓምዳዊ አደረጃጀት ተገቢነት ማለትም (ተከታታይነትን እና ተለጣጣቂነትን) ከተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ Anderson & Krathwohl (2001) የእውቀት ደረጃዎች ስርጭት እይታ አኳያ በጥልቀት ይመረምራል።

## 4.1 የክሂሎች ዓምዳዊ ይዘት ትንተና በ9ኛ ክፍል መጽሐፍ ከRBT ስርጭት አኳያ

ጥናቱ "በ2008ዓ/ም ታትመው ስራ ላይ ባሉት የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል የትግርኛ ቋንቋ መማርያ መጽሐፎች የክሂሎች አምዳዊ አደረጃጀት ተገቢነት ከተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ የዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት እይታ መሰረት በማድረግ እንዴት እንደተደራጁ መገምገም።" የሚል አጠቃላይ ዓላማ ያለው ሲሆን ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ ከሚመነጩት ዝርዝር ዓላማዎች መካከል አንዱ ከሆነው፣ በ9ኛ ክፍል የትግርኛ መጽሐፍ በያንዳንዱ ምዕራፍ የቀረቡ ክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት (vertical alignment) ማለትም የይዘቶች ተከታታይነት እና (የይዘቶች ተለጣጣቂነት ከእውቀት ደረጃዎች RBT ስርጭት እይታ አኳያ መገምገም የሚል ሲሆን ከዚህ አላማ አኳያ ትንተናው እንደሚከተለው (በማንበብ፣ ማዳመጥ፣ መፃፍ እና መናገር) በቅደም ተከተል ከዓላማው አንፃር ቀርቧል።

## 4.1.1 በ9ኛ ክፍል የማንበብ ክሂል ይዘቶች ትንተና

**የማንበብ ክሂል 9ኛ ክፍል**

| Cognitive level | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምዕራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 18 | 75 | 7 | 21 | 1 | 7.1 | 6 | 38 | 6 | 25 | 26 | 76 | 7 | 26 | 9 | 39 | 19 | 100 | 7 | 37 | 106 | 45.3 |
| U2 | 6 | 25 | 27 | 79 | 13 | 93 | 9 | 56 | 17 | 70.8 | 8 | 24 | 9 | 33 | 14 | 61 | 0 | 0 | 9 | 47 | 112 | 47.9 |
| A3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 6.3 | 1 | 4.17 | 0 | 0 | 5 | 19 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 5.3 | 8 | 3.42 |
| sub total | 24 | 100 | 34 | 100 | 14 | 100 | 16 | 100 | 24 | 100 | 34 | 100 | 21 | 78 | 23 | 100 | 19 | 100 | 17 | 89 | 226 | 96.6 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 6 | 22 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 6 | 2.56 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| C6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 11 | 2 | 0.85 |
| sub total | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 6 | 22 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 11 | 8 | 3.42 |
| TOTAL | 24 | 100 | 34 | 100 | 14 | 100 | 16 | 100 | 24 | 100 | 34 | 100 | 27 | 100 | 23 | 100 | 19 | 100 | 19 | 100 | 234 | 100 |

*ሰንጠረዥ 4.1.1 የማንበብ ክሂል 9ኛ ክፍል*

### *4.1.1.1 መሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች (LOTS) በማንበብ ክሂል 9ኛ ክፍል*

በምዕራፍ 1 R1 75%፣ U2 25%፣ ምዕራፍ 2 U2 79.41%፣ ምዕራፍ 3 U2 92.86%፣ ምዕራፍ 6 R1 76.47% እና ምዕራፍ 9 R1 100% ውስጥ ጎልቶ ይታያል። ከዚህ ትንተና እንደምንረዳው ተማሪዎችን ለማስታወስ (R1) እና ለመረዳት (U2) እንዲዘጋጁ ያደርጋል። ይህም የይዘቶች ተከታታይነት በመሰረታዊ ደረጃዎች (LOTS) ላይ እንዳለ ያመለክታል።ይህን ሐሳብ አስመልክቶ እነ Cunningsworth (1995፣ 120)፣ Richards (2001፣ 55) እና Tyler (2013:91) በተመሳሳይ "ተከታታይነት አንድ የትምህርት ይዘት ሳይቆራረጥ በየምዕራፉ እና በየክፍል ደረጃው ተደጋግሞ መቅረቡን የሚያሳይ ነው።" በማለት ያብራራሉ። ነገር ግን በዚህ የማንበብ ክሂል ይዘቶቹ ተከታታይነታቸው ቀለል ባሉ የእውቀት ደረጃዎች ላይ የተገደቡ ናቸው። ይህም የይዘቶች ተለጣጣቂነት እጥረትን ያሳያል። ለምሳሌ በመጽሐፉ ገጽ 2፣ 3፣ 4፣ 6፣ 16… ወዘተ ባጠቃላይ በመጽሐፉ የማንበብ ክሂል የቀረቡ የቅድመ ምንባብ ፣ የማንበብ ግዜ እና ድህረ ምንባብ ጥያቄዎች ውስጥ ምዕራፍ 7 ገጽ 109 መመርያ 3 ነገሮች በማወዳደር እና በማነፃፀር ትንታኔ እንዲሰጡ የሚያደርግ ምሳሌ ጥያቄ 3, "ካብ ጽሒይን ንፋስን ንመን ትድግፉ? ንምንታይ?" እና ሌሎች ተመሳሳይ አምስት ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚመለሱ ጥያቄዎች፣ እንዲሁም ተማሪዎችን የማፍለቅ ክህሎት የሚያበረታታ ገጽ 162 መመርያ 3 እና 4 እያንዳንዳቸው አንድ አንድ ጥያቄ በስተቀር ሌሎቹ 226 ማለትም (96.58%) ጥያቄዎች ተማሪዎች በቀላሉ ተረድተው የሚመልሷቸው ለምሳሌ የማስታወስ (remembering) ጥያቄዎች ገጽ 4 መመርያ ለ "ብመሰረት ምንባብ ቀፂሎም ንዝቐረቡ ሕቶታት ቅኑዕ መልሲ ንዝሐዘ ፊደል ምረፁ።

ጥያቄ ቁጥር 6, "ቋንቋ ካብ ምንታይ እዩ ዝጅምር? ሀ/ ካብ ስያመ ለ/ ካብ ስራሕ ሐ/ ካብ ትምህርቲ መ/ ካብ እምነት" እንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች በተከታታይነት እስከመጨረሻ ቢኖሩም ተማሪዎቹ ምንባቡን በጥልቀት ተረድተው እንዲተነትኑ፣ እንዲገመግሙ እና እንዲያፈልቁ ከማድረግ ይልቅ ጥያቄዎቹ ምረጥ፣ ዘርዝሩ፣ አስታውስ ፣ በቅደም ተከተል አስቀምጥ፣ ተርጉም፣ ግልጽ አድርግ፣ ለይ ፣ አዛምድ ፣ ጥራ ፣ …ወዘተ የሚሉ የመቋጫ ቃላት የያዙ ሲሆኑ፤ እንዲሁም የተቀሩት የመረዳት (understanding) ጥያቄዎች ደግሞ አስረዳ፣ ግለጽ፣ ጽሁፍ አቀናጅ፣ አጠቃልል፣ ተወያይ፣ ተርጉም እና ሌሎች ናቸው። ለበለጠ መረጃ በአባሪ 11 በገጽ 91 ጥያቄዎቹ ቀርበዋል። የማንበብ ተግባራት በመሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች LOTS በተለይ በ (R1 እና U2) ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ከአጠቃላይ ይዘት በአማካይ የምዕራፉን 93.16% ይሸፍናሉ። ስለሆነም የመሰረታዊ ደረጃዎች (LOTS) የበላይነት መያዙ ተማሪዎችን ለመሰረታዊ እውቀት ያዘጋጃል ነገር ግን ወደ ውስብስብ አስተሳሰብ እንዲሸጋገሩ አያደርግም። ስለሆነም የይዘት ተለጣጣቂነት በተገኘው መረጃ እምብዛም አይታይበትም። ባጠቃላይ መሰረታዊ የእውቀት ደረጃ በዚህ ክሂል ውስጥ በሁሉም ምዕራፎች የበላይነት ኖሮት ከፍተኛ ተግባራት በማካተት ተከታታይነትን እንዳለው ቢያመለክትም ወደ ከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎች ቀስ በቀስ አለመሸጋገሩ ውጤቱ ያሳያል።

#### *4.1.1.2 ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃዎች (HOTS) በማንበብ ክሂል 9ኛ ክፍል*

በ9ኛ ክፍል የማንበብ ክሂል ከHOTS ስርጭት እይታ (A4፣ E5 እና C6) ከጠቅላላ ይዘት 3.41% በቁጥር ከ234 ተግባራት 8 በጣም ዝቅተኛ ጥያቄዎች ተካተዋል። ይህም በምዕራፍ 7 (A4 22.22%) እና ምዕራፍ 10 (C6 10.53%) ብቻ ይገኛሉ። E5 ሙሉ በሙሉ የለም። በመጠኑም ቢሆን በነዚህ ሁለት ምዕራፎች የይዘቶች ተለጣጣቂነትን ይታያል። ለምሳሌ በገጽ 162 ከድህረ ማንበብ ጥያቄዎች መመርያ III እና IV "ክትዕ ንኽካየድ ዘድልዩ አካላት እንመን ምዃኖም ዘርእይን ሕድሕድ አካል አብቲ ክትዕ ዝህልዎ ብጽሒት እንታይ ምዃኑ ዝገልጽን ሐፂር ዓንቀጽ ጽሐፉ።" የሚል በመመርያ III ያለው ጥያቄ ሲሆን ተማሪዎች ምንባቡን በጥልቀት ደጋግመው እንዲያነቡ እና በራሳቸው አባባል አንቀጽ እንዲጽፉ ማድረጉ የተማሪዎች የፈጠራ ክህሎት እንዲያድግ ቢያደርግም በተከታታይ እና በተለጣጣቂነት አልቀረበም። ይህን ግኝት ለማጠናከር Cunningsworth (1995:121)፥ Richards (2001:56) እና Tyler (2013:92)

በተመሳሳይ የይዘት ተለጣጣቂነት ማለት የይዘቱ መደጋገም ሳይሆን በተመረጡ ይዘቶች ትምህርቱ እየሰፉ እና እየከበደ መዘጋጀቱን ያመለክታል። በማለት ይገልፁታል። ስለሆነም የምሁራኑ ሐሳብ መሰረት በማድረግ ከዚህ የትንተና ውጤት የምንረዳው የይዘቶች ተከታታይነትን የተገደበ መሆኑን ነው፤ ምክንያቱም HOTS በተወሰኑ ምዕራፎች ብቻ ስለሚገኙ ነው። ስለሆነም የHOTS ውስንነት ተማሪዎችን ለወሳኝ አስተሳሰብ (critical thinking) በተለጣጣቂነት እንዳይዘጋጁ ያደርጋል።

### *4.1.1.3 የምዕራፎች ምጥጥን እና ተከታታይነት በማንበብ ክሂል 9ኛ ክፍል*

የተግባራት ብዛት በምዕራፎች መካከል አልተመጣጠነም። ለምሳሌ አብዛኛው ቁጥር ምዕራፍ 2 እና 6 እያንዳንዳቸው 34 ተግባራት አሏቸው ፤ ምዕራፍ ሶስት 14 ተግባራት ፤ ምዕራፍ አስር ደግሞ 19 አነስተኛ ቁጥር ያሏቸው ተግባራትን አካትተዋል። ይህ ጭብጥ የይዘቶች ተከታታይነትን ይገድባል። ምክንያቱም ተማሪዎች በአንዳንድ ምዕራፎች ውስጥ ብዙ ልምምድ እያገኙ በሌሎች ውስጥ አነስተኛ እድል አላቸው። በዚህ የትንተና ውጤት ውስጥ የተግባራት አለመመጣጠን የይዘቶች ተለጣጣቂነትንም በተመሳሳይ መንገድ እጥረት እንዲኖር ያደርጋል፤ ምክንያቱም ተማሪዎች ተከታታይነት ያሏቸው ይዘቶች ካለመማራቸው የተነሳ ተከታታይነት ያለው የክሂሎች ዕውቀት በተለጣጣቂነት አያገኙም። ይህም ማለት ለምሳሌ፦ ፊደል፣ ቃል፣ ሐረግ፣ ዓረፍተ ነገር፣ ድርሰት፣ ጽህፈት፣ ንባብ፣ ንግግር ወዘተ በተመለከቱ ተግባራት በአራቱም የቋንቋ ክሂሎች በተከታታይነት እየሰፉ መሄድ ሲገባቸው ተደጋጋሚ በሆኑ የማስተዋል ጥያቄዎች መጽሐፉ ተጨናንቋል።

### *4.1.1.4 የተለጣጣቂነት ስርጭት በማንበብ ክሂል 9ኛ ክፍል*

በመጀመሪያ ምዕራፎች ማለትም ከ1–6 ውስጥ LOTS ሙሉ በሙሉ የበላይነት አለው፤ ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን ቀለል ባሉ ይዘቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል። ቀጥለው በሚመጡ ምዕራፎች (7 እና 10) ውስጥ HOTS ትንሽ ይታያል (A4 በምዕራፍ 7፣ C6 በምዕራፍ 10) ፣ ይህም ትንሽ የይዘቶች ተለጣጣቂነትን ያሳያል። ከዚህ የትንተና ውጤት የምንረዳው ተከታታይነት በመሰረታዊ ደረጃዎች ላይ አለ፤ ነገር ግን ተለጣጣቂነት በተወሰኑ ምዕራፎች ብቻ የተገደበ ነው። ባጠቃላይ የተለጣጣቂነት እጥረት ተማሪዎችን ለወሳኝ አስተሳሰብ እንዳይዘጋጁ ያደርጋል።

ከአጠቃላይ ትንተናው የምንረዳው የማንበብ ክሂል ይዘቶች በመሰሰረታዊ ደረጃዎች LOTS ላይ ያተኮሩ ናቸው፤ ይህም የይዘቶች ተከታታይነት ቀለል ባሉ ይዘቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ሆኖ እናገኘዋለን። ነገር ግን ተለጣጣቂነት በተወሰኑ ምዕራፎች የተገደቡ ናቸው። ማለትም የHOTS በምዕራፍ 7 እና 10 ትንሽ እድገት ያሳያሉ፤ ሆኖም የምዕራፎቹ አለመመጣጠን ተከታታይነትን እንዲቆራረጥ አድርጎታል። ስለሆነም በዚህ ክሂል የይዘቶች ተለጣጣቂነት እና ተከታታይነት የተሟላ ካለመሆኑ የተነሳ ተማሪዎችን ወደ ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ እንዳይጓዙ ይገታቸዋል።

## 4.1.2 በ9ኛ ክፍል የማዳመጥ ክሂል ይዘቶች ትንተና

| | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Cognitive leve | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 5 | 100 | 0 | 0 | 6 | 46 | 5 | 63 | 3 | 30 | 3 | 33 | 5 | 56 | 2 | 18 | 3 | 27 | 0 | 0 | 32 | 39.5 |
| U2 | 0 | 0 | 5 | 100 | 7 | 54 | 2 | 25 | 7 | 70 | 5 | 56 | 3 | 33 | 8 | 73 | 8 | 73 | 0 | 0 | 45 | 55.6 |
| A3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| sub total | 5 | 100 | 5 | 100 | 13 | 100 | 7 | 88 | 10 | 100 | 8 | 89 | 8 | 89 | 10 | 91 | 11 | 100 | 0 | 0 | 77 | 95.1 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 13 | 0 | 0 | 1 | 11 | 1 | 11 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 3 | 3.7 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 9.1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1.23 |
| C6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| sub total | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 13 | 0 | 0 | 1 | 11 | 1 | 11 | 1 | 9.1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 4 | 4.94 |
| TOTAL | 5 | 100 | 5 | 100 | 13 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 | 9 | 100 | 9 | 100 | 11 | 100 | 11 | 100 | 0 | 0 | 81 | 100 |

*Table 1 ሰንጠረዥ 4.1.2 የማዳመጥ ክሂል 9ኛ ክፍል*

### *4.1.2.1 መሰረታዊ የዕውቀት ደረጃዎች (LOTS) በማዳመጥ ክሂል 9ኛ ክፍል*

ሰንጠረዥ 4.1.2 መሰረት በማድረግ የማዳመጥ ተግባራት በመሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች በምዕራፍ 1 (R1 100%) ምሳሌ ገጽ 12 መመርያ II "ብመምህርኩም ዝቸርበልኩም ምንባብ እናዳመጽኩም ቀፂሎም ዝቐረቡ ሕቶታት ዝሐዝዎ ሓሳብ ትኽክል እንተኾይኑ ሐቂ ትኽክል እንተዘይኮይኑ ድማ ጌጋ ብምባል መልሱ።" ከሚሉት የእውነት ሐሰት ጥያቄዎች መካከል ተራ ቁጥር "1, ዝኾነ ተምሐራይ ፀገም ቋንቋ እንተሐልይዎ ቁምነገር ንምችባጥ ፀገም ይፈጥረሉ እዩ።" እንደነዚህ ዓይነት በርካታ ጥያቄዎች ከምዕራፍ 10 በስተቀር በተከታታይ ቀርበዋል፤ ምዕራፍ 2 (U2 100%)፣ ምዕራፍ 3 (R1 46.15%፣ U2 53.85%)፣ ምዕራፍ 4 (R1 62.5%፣ U2 25%)፣ ምዕራፍ 5 (R1 30%፣ U2 70%)፣ ምዕራፍ 6 (R1 33.33%፣ U2 55.56%)፣ ምዕራፍ 7 (R1 55.56%፣ U2 33.33%) እና ምዕራፍ 9 (R1 27.27%፣ U2 72.73%) ውስጥ ጎልቶ ይታያል። ይህ ትንተና እንደሚያመለክተው ተማሪዎችን ለማስታወስ (R1) እና ለመረዳት (U2) የበለጠ እንዲዘጋጁ ያደርጋል ከጠቅላላ

ተግባራትም 95.1% ይሸፍናሉ፤ ይህም የይዘቶች ተከታታይነት በመሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች ላይ እንዳለ ያመለክታል። ነገር ግን ይህ ተከታታይነት ልክ እንደ ማንበብ በቀላል የትምህርት ይዘቶች ላይ ያተኮረ ነው። ለምሳሌ ምዕራፍ 5 ገጽ 67 "ግጥሚ ከም አጠቓቕማ ቋንቋ" በሚለው የማዳመጥ ርእስ ውስጥ ተራ ቁጥር "1, ግጥምታት ናብ ዕዱማት ብዝቐርቡሎም መንገዲታት አብ ክንደይ ይምቀሉ?" ካዳመጡት ምንባብ በቀላሉ እንዲህ ብለው የሚመልሷቸው ጥያቄዎች በርካታ ናቸው። ይህም የይዘቶች ተለጣጣቂነት እጥረትን ያሳያል። በዚህ ጭብጥ ውስጥ የመሰረታዊ ደረጃዎች LOTS የበላይነት ተማሪዎችን ለመሰረታዊ እውቀት ያዘጋጃል ነገር ግን ወደ ውስብስብ አስተሳሰብ አያሸጋግርም።

### *4.1.2.2 የከፍተኛ ዕውቀት ደረጃዎች (HOTS) በማዳመጥ ክሂል 9ኛ ክፍል*

ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃዎች HOTS (A4፣ E5 እና C6) 4.94 % በጣም ዝቅተኛ ተግባራት ይዘው ቀርበዋል። ለምሳሌ በምዕራፍ 4 (A4 12.5 %) ፣ ምዕራፍ 6 (A4 11.11 %) ፣ ምዕራፍ 7 (A4 11.11 %) እና ምዕራፍ 8 (E5 9.09 %) ብቻ ይገኛሉ። C6 ሙሉ በሙሉ የለም። ይህ ጭብጥ የይዘቶች ተለጣጣቂነትን በተወሰነ መልኩ ያሳያል። በመጀመሪያ ምዕራፎች ውስጥ HOTS የለም፤ ነገር ግን በተወሰኑ ምዕራፎች (4፣6፣7እና8) ውስጥ ትንሽ ይታያል። ይህም የሚያሳየን የይዘቶች ተከታታይነትን የተገደበ መሆኑን ነው፤ ምክንያቱም HOTS በተወሰኑ ምዕራፎች ብቻ ስለሚያተኩር ነው። ከዚህ ትንተና የምንወስደው ጭብጥ ፣ የHOTS ውስንነት ተማሪዎችን ለወሳኝ አስተሳሰብ (critical thinking) እንዳይዘጋጁ እንደሚያደርግ ነው።

### *4.1.2.3 የምዕራፎች ምጥጥን እና ተከታታይነት በማዳመጥ ክሂል 9ኛ ክፍል*

የተግባራት ብዛት በምዕራፎች መካከል አልተመጣጠነም። ለምሳሌ፦ ምዕራፍ 3 (13 ተግባራት) እና ምዕራፍ 8 እና 9 እያንዳንዳቸው 11 ብዙ ተግባራት ሲኖራቸው፣ ምዕራፍ 1 እና 2 እያንዳንዳቸው 5 እና ምዕራፍ 10 የለውም። ስለሆነም አነስተኛ ተግባራትን ይዘዋል። ይህ ጭብጥ የይዘቶች ተከታታይነትን እንዳይኖር ያደርጋል፤ ምክንያቱም ተማሪዎች በአንዳንድ ምዕራፎች ውስጥ ብዙ ልምምድ እያገኙ በሌሎች ውስጥ እንደ ምዕራፍ 10 ምንም እድል የላቸውም። ከዚህ ትንተና መገንዘብ የሚቻለው የተግባራት አለመመጣጠን የይዘቶች ተለጣጣቂነትን የተገደበ መሆኑን ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች በተከታታይ ክሂሎቹን የሚያሳዱጉባቸው ይዘቶች ማግኘት ስላልቻሉ ነው።

### 4.1.2.4 የተለጣጣቂነት ስርጭት በማዳመጥ ክሂል 9ኛ ክፍል

በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች (ከምዕራፍ 1–5) ውስጥ (LOTS) መሰረታዊ የማሰብ ችሎታ ሙሉ በሙሉ የበላይነት አለው። ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን በቀላል ደረጃ ወይም በመሰረታዊ ይዘቶች ላይ ያደርጋል። በኋላኞቹ ምዕራፎች (ከምዕራፍ 6–9) ውስጥ ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ (HOTS) ትንሽ ይታያል። ለምሳሌ በ (A4 በምዕራፍ 6 እና 7፣ E5 በምዕራፍ 8) ከቀረቡ ተግባራት ውስጥ በምዕራፍ 8 ገጽ 129 ጥያቄ I "ብሚኒ ሚድያ ቤት ትምህርትኹም ካብ ዝቸርቡ ሐበሬታታት አይኖት ከምትድግፉ ወይ ብእዋናውነቶም ከምእትሕጎሱ ንምፍላይ ነቶም ዝለዓሉ መልእኽትታት እናተኸታተልኩም አብ መዘክርኩም አክቡ። ነቶም ዝአከብኩምዎም ሐሳባት ንምንታይ ከምእትድግፍዎምን ከምእትቃወምዎምን አብ ክፍሊ ግለፁ፤ ክከውን አለዎ እትብልዎ ሐሳብ እውን አቕርቡ።" (የተቀሩትን በአባሪ 14 ገጽ 109 ማየት ይቻላል።) እንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ከጠቅላላ 81 ተግባራት 4 ብቻ ተማሪዎች በጥልቀት እንዲያዳምጡ እና የማዳመጥ ክህሎታቸው እንዲያድግ ብያደርጉም በጣም ጥቂት ናቸው። ሆኖም ግን ትንሽ የይዘቶች ተለጣጣቂነትን ያሳያል። ለምሳሌ፦ በያንዳንዱ ምዕራፍ ያሉ ጥያቄዎቹ መዘበራረቅ አይታይባቸውም ሁሉም ከቀላል ወደ ከባድ የተደራጁ ናቸው። ከማስታወስ ወደ መረዳት፣ ከመረዳት ወደ መተግበር፣ ከመተግበር ወደ መተንተን፣ ከመተንተን ወደ መገምገም መራመዳቸው ጥቂት ቢሆንም ጥሩ ነው።ይህ ሐሳብ በበለጠ በመጽሐፉ ምዕራፍ አራት ገጽ 50-51፣ ምዕራፍ አምስት ገጽ 67፣ ምዕራፍ ስድስት ገጽ 88፣ ምዕራፍ ሰባት ገጽ 114፣ ምዕራፍ ስምንት ገጽ 115 እና 128 እንዲሁም ምዕራፍ ዘጠኝ ገጽ 145-146 የቀረቡ ይዘቶች በአባሪው መመልከት ይቻላል።

በአጠቃላይ ከዚህ ትንተና የምንረዳው፣ የማዳመጥ ክሂል ይዘቶች በመሰረታዊ ደረጃዎች (LOTS) ላይ ያተኮሩ ናቸው። ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን በቀላል ደረጃ ላይ ያደርጋል ነገር ግን ተለጣጣቂነትን እንዲወሰን አድርጎታል። የHOTS የተወሰነ መገኘት (ከምዕራፍ 4–8) ትንሽ ተለጣጣቂነትን ያሳያል፤ ሆኖም ግን የተግባራቱ በምዕራፎች አለመመጣጠን ተከታታይነትን እንዲወሰን አድርጎታል።

## 4.1.3 በ9ኛ ክፍል የመፃፍ ክሂል ይዘቶች ትንተና

የመፃፍ ክሂል 9ኛ ክፍል

| የዕውቀት ደረጃዎ | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 11 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1.45 |
| U2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 11 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1.45 |
| A3 | 17 | 100 | 4 | 57 | 2 | 22 | 1 | 20 | 0 | 0 | 6 | 46 | 1 | 20 | 0 | 0 | 6 | 100 | 0 | 0 | 37 | 53.6 |
| sub total | 17 | 100 | 4 | 57 | 4 | 44 | 1 | 20 | 0 | 0 | 6 | 46 | 1 | 20 | 0 | 0 | 6 | 100 | 0 | 0 | 39 | 56.5 |
| A4 | 0 | 0 | 1 | 14 | 1 | 11 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 2.9 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 22 | 1 | 20 | 0 | 0 | 5 | 38 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 8 | 11.6 |
| C6 | 0 | 0 | 2 | 29 | 2 | 22 | 3 | 60 | 2 | 100 | 2 | 15 | 4 | 80 | 3 | 100 | 0 | 0 | 2 | 100 | 20 | 29 |
| sub total | 0 | 0 | 3 | 43 | 5 | 56 | 4 | 80 | 2 | 100 | 7 | 54 | 4 | 80 | 3 | 100 | 0 | 0 | 2 | 100 | 30 | 43.5 |
| TOTAL | 17 | 100 | 7 | 100 | 9 | 100 | 5 | 100 | 2 | 100 | 13 | 100 | 5 | 100 | 3 | 100 | 6 | 100 | 2 | 100 | 69 | 100 |

*ሰንጠረዥ 4.1.3 የመፃፍ ክሂል 9ኛ ክፍል*

### *4.1.3.1 የትግበራ እና ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት በመፃፍ ክሂል 9ኛ ክፍል*

የሰንጠረዡ ትንተና የሚያሳየው የመፃፍ ተግባራት በA3 (53.62%)፣ C6 (28.99%) እና E5 (11.59%) ላይ ያተኮሩ ናቸው። ይህ ጭብጥ በምዕራፍ 1 (A3 100%)፣ ምዕራፍ 2 (A3 57.14%፣ C6 28.57%)፣ ምዕራፍ 3 (A3 22.22%፣ E5 22.22%፣ C6 22.22%)፣ ምዕራፍ 4 (C6 60%)፣ ምዕራፍ 5 (C6 100%)፣ ምዕራፍ 6 (A3 46.15%፣ E5 38.46%)፣ ምዕራፍ 7 (C6 80%)፣ ምዕራፍ 8 (C6 100%) እና ምዕራፍ 10 (C6 100%) ውስጥ ጎልቶ ይታያል። ይህ ውጤት ተማሪዎችን ለትግበራ (A3)፣ ለግምገማ (E5) እና ለፈጠራ (C6) ያዘጋጃል። ስለሆነም የይዘቶች ተለጣጣቂነት ተማሪዎች ከበድ ባሉ እና ከፍተኛ የማሰብ ክህሎት በሚያስፈልጋቸው ተግባራት ላይ እንዲጠመዱ ያደርጋል። ለምሳሌ በመጽሐፉ ከቀረቡ ጠቅላላ 69 ተግባራት ከነዚህ 37 ጥያቄዎች ትግበራ A3 (53.67%) ሲሸፍኑ 30 ጥያቄዎች ደግሞ የጠቅላላ ተግባራት 43.48% HOTS ናቸው፤ ምዕራፍ አንድ ገጽ 8 የምክንያት እና ውጤት አስተካክሎ መፃፍ ጀምሮ ምዕራፍ 10 ገጽ 165 ምክንያትና ውጤት የሚያሳይ ዓንቀጽ በማፍለቅ በተከታታይነት እና በተለጣጣቂነት ሳይቆራረጥ ከሌሎች መሰረታዊ ይዘቶች ጋር ቀርቧል። ነገር ግን ይህ ተከታታይነት በመሰረታዊ የማሰብ ደረጃዎች አያደርግም። ይህም ከላይኞቹ ክሂሎች (ማንበብ እና ማዳመጥ) በተቃራኒ ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት ይደግፋል። በዚህ ጭብጥ ውስጥ የከፍተኛ ደረጃዎች የበላይነት ተማሪዎችን ለወሳኝ አስተሳሰብ እንዲዘጋጁ ሲያደርጋቸው ነገር ግን R1 እና U2 ማጠናከር ላይ ጉድለት ይታይበታል።

### 4.1.3.2 የመሰረታዊ ዕውቀት ደረጃዎች (LOTS) ስርጭት በመፃፍ ክሂል 9ኛ ክፍል

በዚህ የመፃፍ ክሂል ውስጥ R1 እና U2 እያንዳንዳቸው (1.45%) በጣም በዝቅተኛ ሁኔታ በምዕራፍ 3 ብቻ ቀርበዋል። ይህ ጭብጥ የይዘቶች ተከታታይነትን በተለይ በትግበራ A3 የተሻለ ቢሆንም፤ በማስታወስና በመረዳት 2 ጥያቄ ብቻ መቅረባቸው ተማሪዎች ማስታወስ እና መረዳት ሳይገነቡ ወደ ከፍተኛ ደረጃዎች እንዲገቡ ተደርገዋል።ለምሳሌ በምዕራፍ 3 ገጽ 40 ጥያቄ ተራ ቁጥር "1, ልዕል ኢ.ሉ ካብ ዝቐረበ ዓንቀጽ እቲ ቀንዲ ሙሉእ ሐሳብ አየናይ እዩ? 2,ንምንታይ ንሱ ኮይኑ?" ከሚሉ ጥያቄዎች በስተቀር የተቀሩት የመጽሐፉ ተግባራት ተማሪዎች በሂደት የመፃፍ ክሂላቸው እንዲያፈልቁ አሚያደርጉ ናቸው። ስለሆነም ቀድመን ካየናቸው ክሂሎች በተቃራኒው ተለጣጣቂነት ጎልቶ ይታያል። ሆኖም በመጀመሪያ ምዕራፎች ውስጥ የመሰረታዊ ደረጃዎች እጥረት ተማሪዎችን በሙሉነት ከቀለለ ወደ ከበደ ተግባር እንዳይዘጋጁ ያደርጋል።

### 4.1.3.3 የምዕራፎች ተግባራት ምጥጥን እና ተከታታይነት በመፃፍ ክሂል 9ኛ ክፍል

የተግባት ብዛት በምዕራፎች መካከል አልተመጣጠነም። ለምሳሌ 17 ተግባራት በምዕራፍ 1 እና 13 ተግባራት በምዕራፍ 6 በብዛት ተካተዋል። ምዕራፍ 5 ፣ 7 እና 10 እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ጥያቄዎች ሲይዙ በቁጥር በጣም ትንሽ ድርሻ ይዘዋል። ይህ ጭብጥ የይዘቶች ተከታታይነት የተገደበ መሆኑ ያሳየናል፣ ምክንያቱም ተማሪዎች በአንዳንድ ምዕራፎች ውስጥ ብዙ ልምምድ እያገኙ በሌሎች ውስጥ አነስተኛ እድል አላቸው። ስለሆነም የተግባራት አለመመጣጠን የይዘቶች ተለጣጣቂነትን እንዳይኖር አድርጎታል። ለምሳሌ በመጽሐፉ ምዕራፍ ስድስት ገጽ 93-97 ከቀረቡ ይዘቶች መመርያ አንድ ጥያቄ I, ጽሁፍን በስርዓተ ነጥብ ማሟላት፣ II,የተጀመሩ ዓረፍተ ነገሮች አሟልቶ መፃፍ፣ III, የተለመዱ ምስላዎች በነጠብጣብ ማሟላት፤ እንዲሁም መመርያ ሁለት ጥያቄ I,በሚሰጣችሁ ርእስ መሰረት የራሳችሁ አስተዋጽኦ ፃፉ። II, ደብዳቤ ወደ ትምህርትቤታችሁ ፃፉ። እነዚህ 13 ተግባራት ከመተግበር እስከ ማፍለቅ የተማሪዎች ክህሎት የሚያሳድጉ ናቸው። በዛው ልክ ደግሞ በርካታ ተግባራት የያዙ ምዕራፎች ሆኖም ግን ተመሳሳይ ጥያቄ ልክ እንደ ምዕራፍ አንድ ገጽ 8-11 መኖራቸው ደግሞ መገንዘብ ይገባል።

### *4.1.3.4 ተለጣጣቂነት እና የከፍተኛ ዕውቀት ደረጃዎች ተያያዥነት በመፃፍ ክሂል 9ኛ ክፍል*

በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ከ1–4 ውስጥ LOTS በተለይ A3 የበላይነት አለው። ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን በመተግበር (A3) ደረጃ ላይ ያተኩራል። የኋላኞቹ ምዕራፎች (5–10) ውስጥ HOTS በተለይ C6 እና E5 ጎልተው ይታያሉ። ለምሳሌ፦ (ምዕራፍ 5 C6 100%) ፣ ይህም ትንሽ የይዘቶች ተለጣጣቂነትን ያሳያል። ተከታታይነት በመተግበር የዕውቀት ደረጃ ላይ አለ። ሆኖም ግን ተለጣጣቂነቱ በከፍተኛ ደረጃ ላይ የተገደበ እንዲሆን አድርጎታል። ተለጣጣቂነቱ በከፍተኛ ደረጃዎች የተሻለ መሆን ተማሪዎችን ለወሳኝ አስተሳሰብ እንዲዘጋጁ ቢያደርግም የመሰረታዊ ችሎታዎችን ማጠናከር ደግሞ ይጎድላል።

ጠቅለል ባለ መልኩ የመፃፍ ክሂል ይዘቶች በመተግበር (A3) የዕውቀት ደረጃ እና ከፍተኛ ደረጃዎች (E5 እና C6) ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ይህም የይዘቶች ተለጣጣቂነት በከፍተኛ የዕውቀት ደረጃ ላይ ያደርጋል። ነገር ግን የተከታታይነትን እጥረት እንዳለው በግልጽ ይታያል። የመሰረታዊ የዕውቀት ደረጃዎች አነስተኛ ተግባራት መገኘት ተማሪዎችን ለውስብስብ ተግባራት እንዳይዘጋጁ ያደርጋል። በምዕራፎች ያሉ ተግባራት የእውቀት ደረጃዎች አለመመጣጠን ተከታታይነት እንዳይኖር ምክንያት ሆነዋል። ስለሆነም በዚህ ክሂል ተከታታይነት ከመሰረታዊ የዕውቀት ደረጃዎች መካከል በመተግበር ላይ ያተኮረ ሲሆን ተለጣጣቂነት ደግሞ በተወሰኑ ምዕራፎች ብቻ ያተኮረ ሆኖ ተገኝቷል።

## 4.1.4 በ9ኛ ክፍል የመናገር ክሂል ይዘቶች ትንተና

የመናገር ክሂል 9ኛ ክፍል

| | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Cognitive leve | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| U2 | 4 | 100 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 50 | 0 | 0 | 1 | 25 | 0 | 0 | 1 | 50 | 0 | 0 | 8 | 34.8 |
| A3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 100 | 1 | 100 | 2 | 50 | 3 | 100 | 3 | 75 | 1 | 33 | 0 | 0 | 1 | 100 | 12 | 52.2 |
| sub total | 4 | 100 | 0 | 0 | 1 | 100 | 1 | 100 | 4 | 100 | 3 | 100 | 4 | 100 | 1 | 33 | 1 | 50 | 1 | 100 | 20 | 87 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 33 | 1 | 50 | 0 | 0 | 2 | 8.7 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 33 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 4.35 |
| C6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| sub total | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 67 | 1 | 50 | 0 | 0 | 3 | 13 |
| TOTAL | 4 | 100 | 0 | 0 | 1 | 100 | 1 | 100 | 4 | 100 | 3 | 100 | 4 | 100 | 3 | 100 | 2 | 100 | 1 | 100 | 23 | 100 |

*Table 2ሰንጠረዥ 4.1.4 የመናገር ክሂል 9ኛ ክፍል*

### *4.1.4.1 የትግበራ ደረጃዎች ስርጭት በመናገር ክሂል 9ኛ ክፍል*

የማንበብ ክሂል በዚህ መጽሐፍ በምዕራፍ ሶስት ገጽ 37፣ ምዕራፍ አራት ገጽ 50፣ ምዕራፍ አምስት ገጽ 66 እንዲሁም ከምዕራፍ 6-8 ገጽ 84፣114፣ 127 ) የመተግበር ይዘቶች በስፋት ይታያሉ። (A3 100%) ፣ ምዕራፍ 4 (A3 100%) ፣ ምዕራፍ 5 (U2 50%፣ A3 50%) ፣ ምዕራፍ 6 (A3 100%) ፣ ምዕራፍ 7 (A3 75%) እና ምዕራፍ 10 (A3 100%) ውስጥ ጎልቶ ይታያል። ይህ ትንተና እሚያሳየው ተማሪዎችን በመተግበር የእውቀት ደረጃ መልመጃዎች (A3) ትኩረት ያደረገ መሆኑን እንረዳለን። ይህም የይዘቶች ተከታታይነት በመተግበር ደረጃ ላይ እንዳለ ሲያስገነዝብ። ይህም የይዘቶች ተለጣጣቂነት እጥረትን ያሳያል። ይህ መረጃ ሲጠቃለል የመናገር ተግባራት በA3 (52.17%) እና U2 (34.78%) ላይ ያተኮሩ ናቸው። ስለሆነም በመተግበር ደረጃዎች የበላይነት ተማሪዎችን ለተግባራዊ እውቀት የሚያዘጋጅ ሲሆን ነገር ግን የመሰረታዊ ችሎታዎችን (R1 እና U2) ማጠናከር ይጎድለዋል።

### *4.1.4.2 የከፍተኛ ዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት በመናገር ክሂል 9ኛ ክፍል*

በዚህ ክሂል የከፍተኛ ዕውቀት ደረጃዎች ውሱንነት ጎልቶ ይታያል። ለምሳሌ፦ (A4፣ E5 እና C6) (13.04%) በጣም ዝቅተኛ ተግባራት ይዘዋል ። እንዲሁም በምዕራፍ 8 (A4 33.33%፣ E5 33.33%) እና ምዕራፍ 9 (A4 50%) ብቻ ይገኛሉ። C6 ሙሉ በሙሉ የለም። ይህ ጭብጥ የይዘቶች ተለጣጣቂነትን በከፊል መኖሩ ያሳያል። በመጀመሪያ ምዕራፎች ውስጥ የከፍተኛ ደረጃዎች የማሰብ ችሎታ HOTS የለም። ነገር ግን በኋላኞቹ ምዕራፎች (8–9) በገጽ 127-128 ውስጥ ትንሽ ይታያል። ይህ የሚያመለክተው የይዘቶች ተከታታይነትን እንዳይኖር አድርጓል። ምክንያቱም HOTS በተወሰኑ ምዕራፎች ብቻ የተገደበ ስለሆነ ነው። ከዚህ የምንወስደው ጭብጥ የከፍተኛ ደረጃ የማሰብ ችሎታ (HOTS) ውስንነት ተማሪዎችን ለወሳኝ አስተሳሰብ (critical thinking) እንዳይዘጋጁ ያደርጋል።

### *4.1.4.3 በምዕራፎች የዕውቀት ተግባራት ምጥጥን እና ተከታታይነት በመናገር ክሂል 9ኛ ክፍል*

በመናገር ክሂል ውስጥ የተግባራት ብዛት በምዕራፎች መካከል አልተመጣጠነም። ለምሳሌ፣ ምዕራፍ 5 እና 7 በቅደም ተከተል እያንዳንዳቸው አራት አራት በዛ ያሉ ተግባራት አሏቸው፣ ምዕራፍ ሁለት የለውም፣ ምዕራፍ ሶስት ገጽ 37 አንድ ጥያቄ እና ምዕራፍ አስር ገጽ 163 ደግሞ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ናቸው። ይህም የይዘቶች

ተከታታይነትን እንዲገደብ አድርጎታል። ምክንያቱም ተማሪዎች በአንዳንድ ምዕራፎች ውስጥ ብዙ ልምምድ እያገኙ በሌሎች ውስጥ እንደ ምዕራፍ 2 ደግሞ ምንም እድል የላቸውም። ስለሆነም የተግባራት አለመመጣጠን የይዘቶች ተለጣጣቂነትን እንዳይኖር አድርጎታል። ምክንያቱም ተማሪዎች በተከታታይነት ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ የሚያዳብሩ በርካታ ተግባራት ማግኘት አልቻሉም።

### *4.1.4.4 ተለጣጣቂነት እና (HOTS) ተያያዥነት በመናገር ክሂል 9ኛ ክፍል*

ትንተናው እንደሚያመለክተው የተግባራት ተለጣጣቂነት እና ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ ደረጃዎች ተያያዥነት በተመለከተ በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች (1–7) ውስጥ LOTS በተለይ A3 በርካታ ተግባራት አለው።ለምሳሌ ከምዕራፍ 1፣ 2 እና 9 በስተቀር በሁሉም ምዕራፎች ተካተዋል፤ ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን በመተግበር (Application) ደረጃ ላይ ትኩረት ያደርጋል። በመጨረሻዎቹ ምዕራፎች (8–9) ውስጥ ደግሞ HOTS በተለይ A4 እና E5 ጎልተው ይታያሉ፤ ምሳሌ ምዕራፍ ስምንት ገጽ 127 " ዝበለፀ ወግዒ አብ ሚኒ ሚድያ አቕርቡ።" ፤ እንዲሁም ምዕራፍ 9 ገጽ 128 "ብዝሐዝኩምዎ ጽሟቕ ሐሳብ ብመሰረት መምርሒ መደረን አብ መድረኽ አቕርቡ።" (ለምሳሌ ምዕራፍ 8 A4 እና E5 33.33%) ፣ ይህም ትንሽ የይዘቶች ተለጣጣቂነትን ያሳያል። ተከታታይነት በመተግበር (Application) ደረጃ ላይ አለ። ሆኖም ግን ተለጣጣቂነት በከፍተኛ የማሰብ ችሎታ ደረጃ ላይ የተገደበ ነው። ስለሆነም የተለጣጣቂነት ውስን መኖር ምንም እንኳን ተማሪዎችን ለወሳኝ አስተሳሰብ ቢያዘጋጅም የመሰረታዊ ችሎታዎችን ማጠናከር ይጎድላል።

የመናገር ክሂል ይዘቶች በመተግበር (Application) ደረጃዎች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን በመተግበር (Application) የዕውቀት ደረጃ ላይ ያደርጋል። ሆኖም ግን የተለጣጣቂነትን ቀጣይነቱ ሙሉ አይደለም። የከፍተኛ ደረጃዎች HOTS ውስንነት ተማሪዎችን በጥልቀት የማሰብ ተግባራት እንዳይዘጋጁ ከማድረጉም በላይ በምዕራፎች የእውቀት ደረጃዎች አለመመጣጠን ተከታታይነትን እንዳይኖር አድርጓል።

## 4.1.5 ማጠቃለያ ዓላማ አንድ (9ኛ ክፍል መጽሐፍ)

በ9ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፍ ውስጥ የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀትን (ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት) ከRBT 2001 እይታ ስርጭት አኳያ መገምገም

የጥናቱ የመጀመርያው ዝርዝር ዓላማ ሲሆን አራቱም የቋንቋ ክሂሎች በዚህ መጽሐፍ ያላቸው አደረጃጀት በስፋት ከላይ የቀረበ ሲሆን የዝርዝር ትንተናው ማጠቃለያም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በ9ኛ ክፍል የትግርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት የቋንቋ ክሂል ተግባራት በተደረገው ትንተና መሰረት፣ በአጠቃላይ 88.94% በመሰረታዊ ዕውቀት ደረጃዎች (LOTS) ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ፣ ከፍተኛ ዕውቀት ደረጃዎች (HOTS) በአጠቃላይ 11.06% ብቻ ይይዛሉ። በተለይም፡-

- ማንበብ → LOTS 96.6%፣ HOTS 3.4%
- ማዳመጥ → LOTS 95.1%፣ HOTS 4.9%
- መናገር → LOTS 86.96%፣ HOTS 13.04%
- መፃፍ → LOTS 56.5%፣ HOTS 43.5% (በተለይ ማፍልቅ/Create/ 28.99%)

እንደ Huitt (2011፣ 3) ገለፃ “የAnderson & Krathwohl (2001) RBT የዕውቀት ደረጃዎች ከLOTS ወደ HOTS ቀስ በቀስ መሸጋገር የትምህርት ዓላማዎች ተግባራዊነትን ያረጋግጣል። በመጽሐፎቹ ውስጥ የHOTS ውስንነት ደግሞ የይዘቶች ተለጣጣቂነትን ይገድባል።” ስለሆነም የይዘቱ ተከታታይነት በR1 እና U2 ደረጃዎች ላይ በጣም ጠንካራ ሲሆን በሁሉም ክሂሎች ከ39–55% በላይ ያመለክታል፤ ተለጣጣቂነት ደግሞ በጣም ደካማ ነው። ከLOTS ወደ HOTS የሚደረግ እድገት በሶስቱ ክሂሎች (ማንበብ፣ ማዳመጥ እና መናገር) ውስጥ አይታይም ምክንያቱም የማንበብ ይዘቶች የግንዛቤ ተግባራት ከመጠየቅ በዘለለ ተማሪዎች ምንባቦቹን ሲተነትኑ፣ ሲገመግሙና ምንባቦች ሲያፈልቁ የሚያሳዩ ተግባራት አይታዩም፤ እንዲሁም የማዳመጥ ተግባራት ካዳመጡት ምንባብ የማስተዋል ጥያቄዎች ለይተው ከመመለስ እና ግምታቸው እንዲያቀርቡ ከማድረግ በዘለለ ያዳመጡት ነገር እንዲተረጉሙ ትንታኔ እንዲሰጡና ከራሳቸው ሂወት ጋር በማያያዝ እንዲመልሱ የሚያደርጉ አይደሉም። በመጨረሻም የመናገር ክሂል ከሁለቱ የተሻለ አቀራረብ ቢኖረውም በስፋት የተለያዩ የንግግር ዝግጅቶች በማቅረብ የንግግር ክሂላቸውን የሚያሳድጉ ክሂሎች እጥረት መኖሩ ያሳያል። በመፃፍ ክሂል ውስጥ ደግሞ ተማሪዎች እስከ መፍጠር (Create) ደረጃ 29% መድረሱ የተሻለ እድገት ይታይበታል።

ስለዚህ መጽሐፉ ተማሪዎችን ወደ ከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎች (Analyze፣ Evaluate፣ Create) ለማድረስ በቂ የሆነ ዓምድያዊ አደረጃጀት አላሳየም። ስለሆነም “በተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ መሰረት፣ የHOTS ተግባራት ተማሪዎችን ወደ ትንተና፣ ግምገማ እና ፈጠራ ያደርሳሉ። በLOTS ብቻ መቆየት ግን ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የእውቀትና የክህሎት ደረጃ የሚኖራቸውን ዝግጅት ይጎዳል።” Churches (2008 ፣2)

## 4.2 የክሂሎች ዓምዳዊ ይዘት ትንተና በ10ኛ ክፍል መጽሐፍ የRBT ስርጭት

በ2008ዓ/ም ታትመው ስራ ላይ ባሉት የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል የትግርኛ ቋንቋ መማርያ መጽሐፎች የክሂሎች አምዳዊ አደረጃጀት ተገቢነት ከተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ የዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት እይታ መሰረት በማድረግ እንዴት እንደተደራጁ መገምገም፤ የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ ሲሆን ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ ከሚመነጩት ዝርዝር ዓላማዎች መካከል በ10ኛ ክፍል የትግርኛ መጽሐፍ በያንዳንዱ ምዕራፍ የቀረቡ ክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት (vertical alignment) ማለትም የይዘቶች ተከታታይነት እና (የይዘቶች ተለጣጣቂነት ከእውቀት ደረጃዎች ከተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ ስርጭት እይታ አኳያ የማንበብ፣ የማዳመጥ፣ የመፃፍ እና የመናገር ክሂሎች በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ተገምግመዋል።

### 4.2.1 የማንበብ ክሂል ይዘቶች ትንተና በ10ኛ ክፍል

ከሰንጠረዡ መረጃ በመነሳት የማንበብ ክሂል ይዘቶች በምዕራፎች መካከል የሚታዩ ዋና ዋና ጭብጦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የማንበብ ክሂል 10ኛ ክፍል

| | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Cognitive leve | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 10 | 31.3 | 29 | 91 | 19 | 95 | 2 | 12 | 5 | 20.8 | 16 | 94 | 5 | 28 | 9 | 56 | 29 | 64 | 8 | 44 | 132 | 55.2 |
| U2 | 22 | 68.8 | 3 | 9.4 | 1 | 5 | 14 | 82 | 19 | 79.2 | 1 | 5.9 | 13 | 72 | 7 | 44 | 14 | 31 | 10 | 56 | 104 | 43.5 |
| A3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 5.9 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 4.4 | 0 | 0 | 3 | 1.26 |
| sub total | 32 | 100 | 32 | 100 | 20 | 100 | 17 | 100 | 24 | 100 | 17 | 100 | 18 | 100 | 16 | 100 | 45 | 100 | 18 | 100 | 239 | 100 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| C6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| sub total | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| TOTAL | 32 | 100 | 32 | 100 | 20 | 100 | 17 | 100 | 24 | 100 | 17 | 100 | 18 | 100 | 16 | 100 | 45 | 100 | 18 | 100 | 239 | 100 |

*ሰንጠረዥ 4.2.1 የማንበብ ክሂል 10ኛ ክፍል*

### 4.2.1.1 መሰረታዊ የዕውቀት ደረጃዎች (LOTS) በማንበብ ክሂል 10ኛ ክፍል

የመሰረታዊ ደረጃዎች በማንበብ ክሂል በምዕራፍ 1 (R1 31.25% U2 68.75%) ፣ ምዕራፍ 2 (R1 90.63%)፣ ምዕራፍ 3 (R1 95%)፣ ምዕራፍ 4 (U2 82.35%)፣ ምዕራፍ 5 (U2 79.17%)፣ ምዕራፍ 6 (R1 94.12%)፣ ምዕራፍ 7 (U2 72.22%)፣ ምዕራፍ 8 (R1 56.25%፣ U2 43.75%)፣ ምዕራፍ 9 (R1 64.44%፣ U2 31.11%) እና ምዕራፍ 10 (U2 55.56%) ውስጥ ጎልቶ ይታያል። በምሳሌ ብናያቸው ገጽ 2 ከንባብ ግዜ ጥያቄዎች መመርያ አንድ እውነት ሐሰት በሉ በሚለው መመርያ ስር ተራ ቀጥር "1/ ቋንቋ ሐብቲ ወዲ ሰብ ጥራሕ እዩ።" ከዚህ ጥያቄ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሌሎች ጥያቄዎችም የተካተቱበት ሲሆን በቀላሉ ከምንባቡ የሚያገኙት እውቀት (recall) እንዲመልሱ የሚያበረታታ ነው። በተጨማሪም ለምሳሌ በድህረ ንባብ ከተካተቱ ጥያቄዎች ተራ ቁጥር 4/ ("እታ ላሕሚ እንቁላሊሕ ወሊዳ " ምባል ብተዛረብቲ እቲ ቋንቋ ዘይፍቀድ ብምንታይ ምኽንያት እዩ?") የሚለውን ጥያቄ ብንመለከት ተማሪዎች ከምንባቡ የተገነዘቡትን እንዲመልሱ ያደርጋል። ከዚህ በዘለለ ተማሪዎቹ ከግል ተሞክሮአቸው ጋር በማያያዝ የማንበብ ክሂላቸውን የሚያሳድጉ ተግባራት አይታዩም። ስለሆነም ትንተናው የሚያስረዳው ተማሪዎችን ለማስታወስ (R1) እና ለመረዳት (U2) በበለጠ እንዲዘጋጁ የሚያደርግ ነው። ይህም የይዘቶች ተከታታይነት በመሰረታዊ ደረጃዎች ላይ እንዳለ ያመለክታል። ነገር ግን ይህ ተከታታይነት በቀላል የእውቀት ደረጃዎች ላይ የተመሰረተ ነው። ይህም የይዘቶች ተለጣጣቂነት እጥረትን ያመለክታል። በአጠቃላይ 98.74% የማንበብ ተግባራት በLOTS (R1 እና U2) ላይ የበላይነት የተጎናፀፉ ደረጃዎች ናቸው። ስለሆነም የመሰረታዊ ደረጃዎች የበላይነት መኖር ተማሪዎችን ለመሰረታዊ እውቀት እንዲዘጋጁ ሲያደርግ ወደ ውስብስብ እና ጥልቅ አስተሳሰብ እንዲሸጋገሩ ግን አያደርግም።

### 4.2.1.2 ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ ደረጃዎች (HOTS) በማንበብ ክሂል 10ኛ ክፍል

የከፍተኛ የማሰብ ችሎታ ደረጃዎች HOTS (A4፣ E5 እና C6) ሙሉ በሙሉ የሉም (0%) ። ምክንያቱም ከቀረቡት 239 ተግባራት ውስጥ ተማሪዎች ጽሁፎችን በሚገባ አንብበው ምንባቡ የፈጠረባቸው ስሜት፣ የደረሱበት ድምዳሜ ከግል ሂወት ተመኩሮአቸው ጋር በማስተሳሰር ሲያቀርቡ አይታዩም፤ እንዲሁም ከምንባቡ ማስታወሻ እየጨመቁ ሲወስዱም ሆነ ትንታኔ ሲሰጡ አለያም ሲገመግሙ የሚያሳዩ ተግባራት አይደሉም። ስለሆነም ይዘቶች እርስ በርሳቸው እየተሳሰሩ  የሚሄዱ ካለመሆናቸው

የተነሳ ተለጣጣቂነት አለመኖሩን ያሳያል። ምክንያቱም ተማሪዎች ትንተና፣ ግምገማ ወይም ፈጠራ እንዳያደርጉ ያደርጋል። ይህ ውጤት ደግሞ የይዘቶች ተከታታይነትን እንዳይኖር አድርጎታል። ምክንያቱም HOTS በየትኛውም ምዕራፍ የሉም። ስለሆነም ይህ የአምዳዊ አደረጃጀት አለመኖር (የHOTS) እጥረት ተማሪዎችን ለወሳኝ አስተሳሰብ (critical thinking) እንዳይዘጋጁ ያደርጋል።

### *4.2.1.3 በምዕራፎች የተግባራት ምጥጥን እና ተከታታይነት በማንበብ ክሂል 10ኛ ክፍል*

በዚህ ክሂል የተግባራት ብዛት በምዕራፎች መካከል መመጣጠን እና ተከታታይነት ሲተነተን ለምሳሌ፣ ምዕራፍ አንድ እና ሁለት እያንዳንዳቸው (32) በርካታ ተግባራት አሏቸው። ምዕራፍ ሶስት 20፣ ምዕራፍ ዘጠኝ 45 እነዚህ ደግሞ ከፍተኛ ቦታ ይሸፍናሉ። ምዕራፍ 4፣ 6፣ 8 እና 10 እያንዳንዳቸው በቅደም ተከተል 17፣ 17፣ 16 እና 18 ደግሞ አነስተኛ ናቸው። ምክንያቱም ተማሪዎች በአንዳንድ ምዕራፎች ውስጥ ብዙ ልምምድ እያገኙ በሌሎች ውስጥ አነስተኛ እድል ቢኖራቸውም በርካታ ተግባራት በቀረቡባቸው ምዕራፋትም እየሰፉና እየረቀቁ ሲሄዱ አይስተዋሉም። ባጠቃላይ የተግባራት አለመመጣጠን የይዘቶች ተለጣጣቂነትን ይገታል። ምክንያቱም ተማሪዎች በተከታታይ ከቀላል ወደ ከባድ የተደራጁ ይዘቶች ማግኘት አልቻሉም።

### *4.2.1.4 ተለጣጣቂነት እና የ(LOTS) ተያያዥነት በማንበብ ክሂል 10ኛ ክፍል*

በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች (1–8) ውስጥ LOTS ሙሉ በሙሉ የበላይነት አለው፤ ይህም የይዘቶች ተከታታይነት በመሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች ላይ ያደርጋል። በኋላኞቹ ምዕራፎች (9–10) ውስጥ A3 ትንሽ ይታያል (A3 100% በምዕራፍ 10) ፣ ይህም ትንሽ የይዘቶች ተለጣጣቂነት በLOTS መኖሩ ቢያሳይም ወደ HOTS አይሸጋገርም። ከዚህ የምንረዳው የጥናቱ ውጤት፣ ተከታታይነት በመሰረታዊ ደረጃ ላይ እንዳለ ነገር ግን ተለጣጣቂነት እንዲኖር የሚያደርጉ የማንበብ ተግባራት አልተካተቱም።

ባጠቃላይ በ10ኛ ክፍል የትግርኛ መጽሐፍ የማንበብ ክሂል ይዘቶች በማስታወስ እና መረዳት የእውቀት ደረጃዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ይህም የይዘቶች ተከታታይነት በመሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች ላይ ያደርጋል ሆኖም ግን ተለጣጣቂነት ውስኑነት

ይታይበታል። የከፍተኛ ደረጃዎች ውስኑነት መኖር ደግሞ ተማሪዎችን ለውስብስብ እና በጥልቀት የማሰብ ችሎታ ለሚጠይቁ ተግባራት እንዳይዘጋጁ ያደርጋል።

## 4.2.2 የማዳመጥ ክሂል ይዘቶች ትንተና የRBT ስርጭት

የማዳመጥ ክሂል 10ኛ ክፍል

| Cognitive lev | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 12 | 80 | 7 | 100 | 8 | 73 | 1 | 13 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 28 | 54.9 |
| U2 | 3 | 20 | 0 | 0 | 3 | 27 | 7 | 87 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 10 | 100 | 0 | 0 | 23 | 45.1 |
| A3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| sub total | 15 | 100 | 7 | 100 | 11 | 100 | 8 | 100 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 10 | 100 | 0 | 0 | 51 | 100 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| C6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| sub total | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| TOTAL | 15 | 100 | 7 | 100 | 11 | 100 | 8 | 100 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 10 | 100 | 0 | 0 | 51 | 100 |

*ሰንጠረዥ 4.2.2 የማዳመጥ ክሂል 10ኛ ክፍል*

### *4.2.2.1 የመሰረታዊ ዕውቀት ደረጃዎች በማዳመጥ ክሂል 10ኛ ክፍል*

የማዳመጥ ተግባራት በ10ኛ ክፍል ማለትም በምዕራፍ 1 (R1 80%፣ U2 20%) ፣ ምዕራፍ 2 (R1 100%) ፣ ምዕራፍ 3 (R1 72.73%፣ U2 27.27%) ፣ ምዕራፍ 4 (U2 87%፣ R1 12.5%) እና ምዕራፍ 9 (U2 100%) ውስጥ ጎልቶ ይታያል።ለምሳሌ ምዕራፍ አንድ ገጽ 13 መመርያ ለ ተራ ቁጥር "1/ ክንደይ ዝኣኸሉ ከባብያዊ ቃላት ክትጽሕፉ ክኢልኩም? " ይህን ጥያቄ ብንመለከት ተማሪዎቹ በቀላሉ ካዳመጡት ግጥም መመለስ የሚችሉት ጥየቄ ነው። ከዚህ ትንተና ተማሪዎችን ለማስታወስ (R1) እና ለመረዳት (U2) እንዲዘጋጁ ያደርጋል። ይህም የይዘቶች ተከታታይነት በመሰረታዊ ደረጃ ላይ በLOTS (R1 እና U2) (100%) ያተኮሩ ናቸው። ነገር ግን ይህ ተከታታይነት ቀለል ባሉ ይዘቶች ላይ ስርጭቱ የሰፋ በመሆኑ የይዘቶች ተለጣጣቂነት እጥረትን ያሳያል።

### *4.2.2.2 የከፍተኛ ደረጃዎች የማንበብ ክሂል ስርጭት 10ኛ ክፍል*

በዚህ ክሂል ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃዎች (HOTS) ተግባራት በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች፣ ወጎች፣ ውይይቶች፣ ክርክሮች እና ገለፃዎች በሚገባ አዳምጠው ማጠቃለያ ሐሳብ ማቅረብ፤ አሳጥሮ ማቅረብ፤ ማስታወሻ መያዝ፤ የሚጠቅማቸው እና የማይጠቅማቸው ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለይተው ማቅረብና ትንታኔ መስጠት የሚያስችሉ ይዘቶች A4፣ E5 እና C6 (0%) ሙሉ በሙሉ የሉም ። ይህም የይዘቶች

ተለጣጣቂነትን እንዳይኖር አድርጎታል። ምክንያቱም ተማሪዎች ልክ እንደ ማንበብ ትንተና፣ ግምገማ ወይም ፈጠራ እንዳያደርጉ ያደርጋል። ምክንያቱም HOTS በአንድም ምዕራፍ የሉም። ከዚህ መረዳት የሚቻለው የHOTS እጥረት ተማሪዎችን በጥልቀት እንዳያነቡ፣ እንዳያስቡ እና እንዳይመራመሩ ያደርጋል።

### 4.2.2.3 የምዕራፎች ምጥጥን እና ተከታታይነት በማንበብ ክሂል 10ኛ

የማዳመጥ ክሂል በ10ኛ ክፍል መጽሐፍ የተግባራት ብዛት በምዕራፎች መካከል መመጣጠን በተመለከተ ለምሳሌ፣ ምዕራፍ አንድ 15 ተግባራት እና ምዕራፍ ሶስት 11 በዛ ያሉ ተግባራት አሏቸው። ምዕራፍ 2፣5፣6፣7፣8እና10 ምንም ዓይነት ይዘት ወይም ተግባር አልተዘጋጀላቸውም። በመሆኑም የይዘቶች ተከታታይነትን እንዳይኖር አድርጎታል። ምክንያቱም ተማሪዎች በአንዳንድ ምዕራፎች ውስጥ ብዙ ልምምድ እያገኙ በሌሎች ውስጥ እንደ ምዕራፍ 2 ደግሞ አነስተኛ እድል አላቸው። ስለሆነም የተግባራት አለመመጣጠን የይዘቶች ተለጣጣቂነትን የተወሰነ እንዲሆን አድርጎታል። ምክንያቱም ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ እና ያልተቆራረጡ ተግባራት በማዘጋጀት የአስተሳሰብ አድማሳቸው እንዲሰፋ ተደርጎ አልተዘጋጀም።

#### 4.2.2.4 ተለጣጣቂነት እና የመሰረታዊ ደረጃዎች ተከታታይነት በማንበብ ክሂል 10ኛ ክፍል

ከዚህ የማዳመጥ ክሂል ትንተና የምንመለከተው በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች (ከ1–4) ውስጥ LOTS ሙሉ በሙሉ ስርጭቱን እንደሸፈነው ከላይ ተገልፃል። ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን በመሰረታዊ ደረጃ ላይ እንዳለ ያሳየናል። ከኋላኞቹ ምዕራፎች ምዕራፍ ዘጠኝ ውስጥ U2 100% ጎልተው ይታያል። ነገር ግን HOTS የሉም። ከዚህ ትንተና የምንረዳው ተከታታይነት በመሰረታዊ ደረጃ ላይ እንዳለና ተለጣጣቂነት በተወሰኑ ምዕራፎች ብቻ የተገደበ መሆኑን ነው።ከዚህም ባሻገር መሰረታዊ ደረጃዎች ከመጀመርያ እስከ መጨረሻዎቹ ምዕራፎች አለመዝለቃቸው ተያያዥነታቸው እንዲያጡና ተለጣጣቂነት ሙሉ በሙሉ እንዳይኖር ሆንዋል።

በዚህ በ10ኛ ክፍል የማዳመጥ ክሂል ይዘቶች በመሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች (LOTS) ላይ የተሰራጩ ናቸው። ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን ቀለል ባሉ ደረጃዎች ላይ ያደርጋል።ሆኖም ግን የተለጣጣቂነትን ውስንነት ይታያል። የከፍተኛ ደረጃዎች (HOTS) እጥረት ተማሪዎችን ለውስብስብ ተግባራት እንዳይዘጋጁ ያደርጋቸዋል። በተጨማሪም የምዕራፎች አለመመጣጠን ተከታታይነትን እንዲገደብ አድርጎታል።

ስለሆነም ተማሪዎች ይህን ክሂል በቂ ልምምድ ለማድረግ የተዘጋጁ ተግባራት ተያያዥነት እና ተለጣጣቂነት ካለመኖራቸው የተነሳ ወደ ከፍተኛ አስተሳሰብ እንዲሸጋገሩ አላደረጋቸውም ይህም አምዳዊ አደረጃጀት እንዳይኖር ምክንያት ነው።

## 4.2.3 የመፃፍ ክሂል ይዘቶች ትንተና

የመፃፍ ክሂል 10ኛ ክፍል

| Cognitive lev | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| U2 | 9 | 69.2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 9 | 18 |
| A3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 4 | 100 | 3 | 60 | 0 | 0 | 10 | 83 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 17 | 34 |
| sub total | 9 | 69.2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 4 | 100 | 3 | 60 | 0 | 0 | 10 | 83 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 26 | 52 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| E5 | 0 | 0 | 3 | 100 | 7 | 100 | 0 | 0 | 1 | 20 | 1 | 100 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 12 | 24 |
| C6 | 4 | 30.8 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 20 | 0 | 0 | 2 | 17 | 0 | 0 | 4 | 100 | 1 | 100 | 12 | 24 |
| sub total | 4 | 30.8 | 3 | 100 | 7 | 100 | 0 | 0 | 2 | 40 | 1 | 100 | 2 | 17 | 0 | 0 | 4 | 100 | 1 | 100 | 24 | 48 |
| TOTAL | 13 | 100 | 3 | 100 | 7 | 100 | 4 | 100 | 5 | 100 | 1 | 100 | 12 | 100 | 0 | 0 | 4 | 100 | 1 | 100 | 50 | 100 |

*ሰንጠረዥ 4.2.3 የመፃፍ ክሂል 10ኛ ክፍል*

### *4.2.3.1 የመሰረታዊ ዕውቀት ደረጃዎች በመፃፍ ክሂል 10ኛ ክፍል*

በዚህ የክፍል ደረጃ የመፃፍ ተግባራት ስርጭት በU2 (18%) እና A3 (34%) ይሸፍናሉ። ይህ አጠቃላይ ውጤት በምዕራፍ 1 (U2 69.2%) ፣ ምዕራፍ 4 (A3 100%) ፣ ምዕራፍ 5 (A3 60%) እና ምዕራፍ 7 (A3 83%) ውስጥ ጎልቶ ይታያል። ስለሆነም ተማሪዎችን ለመረዳት (U2) እና ለመተግበር (A3) እንዲዘጋጁ ያደርጋል። ይህም የይዘቶች ተከታታይነት በመሰረታዊ ደረጃ ላይ እንዳለ ያመለክታል። ስለሆነም የመሰረታዊ ዕውቀት ደረጃዎች የበላይነት ተማሪዎችን ለተግባራዊ እውቀት እንዲዘጋጁ ቢያደርግም የመጥቀስ (R1) ተግባራት ማጠናከር ክፍተት ይታይበታል።

### *4.2.3.2 የከፍተኛ ዕውቀት ደረጃዎች በመፃፍ ክሂል 10ኛ ክፍል*

የከፍተኛ ዕውቀት ደረጃ በመፃፍ ክሂል 10ኛ ክፍል ሲገመገም በምዕራፍ 2 (E5 100%) ፣ ምዕራፍ 3 (E5 100%) ፣ ምዕራፍ 5 (E5 20%) ፣ ምዕራፍ 6 (E5 100%) ፣ ምዕራፍ 9 (C6 100%) እና ምዕራፍ 10 (C6 100%) ላይ ሲገኙ A4 ሙሉ በሙሉ የለም። በመጀመሪያ ምዕራፎች ውስጥ HOTS ዝቅተኛ ነው። ነገር ግን በኋላኞቹ ምዕራፎች (9–10) ውስጥ ትንሽ ይታያል።ሆኖም ግን HOTS (E5 24% እና C6 24%) በአጠቃላይ 48% የመጽሐፉን ስርጭት ይሸፍናል፤ የዚህ ትንተና አጠቃላይ ጭብጥ የይዘቶች ተከታታይነት የተሻለ መሆኑ ያመለክታል። ስለሆነም የHOTS

ተግባራት ስርጭት ተማሪዎች ወደ ወሳኝ አስተሳሰብ (critical thinking) እና የመፍጠር ችሎታ እንዲሸጋገሩ ያደርጋል። ለምን ቢባል ከምዕራፍ አንድ ገጽ 8 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 10 ገጽ 134 ያሉ ተግባራት ቀስ በቀስ ተገቢ አያያዥ ቃላት እና ሐረጎች ተጠቅመው የአንቀጽ አደረጃጀት መመርያ ተከትለው ሐሳባቸው መፃፍ፣ ቃለ ጉባኤ ማዘጋጀት፣ የተለያዩ የደብዳቤ አይነቶች በተገቢው ቅርጽ ማደራጀት እና መፃፍ፣ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት ተጠቅመው ስእላዊ እና አመዛዛኝ ድርሰት መፃፍ፣ የሐሳብ ፍሰትን ለመጠበቅ ብለው ቃላት፣ ሐረጋት፣ ዓረፍተ ነገሮች እና ሌሎች አስፈላጊ ሐሳቦች በመጨመር፣ በማስወገድ፣ በማሳጠር፣ ስርዓተ ነጥብ እና የቃላት አጠቃቀም በማሻሻል የፃፉትን ረቂቅ አስተካክለው እና ገምግመው ማቅረብ፤ ግጥሞችን መገምገም እና ሌሎች የተማሪዎችን የጽህፈት ክህሎት የሚያሳድጉ ተግባራት መካተታቸው ከማንበብ እና ማዳመጥ በተሻለ መልኩ ይህ ክሂል ቀርቧል።

### *4.2.3.3 የምዕራፎች ምጥጥን እና ተከታታይነት በመፃፍ ክሂል 10ኛ ክፍል*

የተግባራት ብዛት በምዕራፎች መካከል አልተመጣጠነም። ለምሳሌ ምዕራፍ 1 (13 ተግባራት) እና ምዕራፍ 7 (12) ብዙ ተግባራት አሏቸው፤ ምዕራፍ 6 (1)፣ ምዕራፍ 8 (0) እና ምዕራፍ 10 (1) ደግሞ በጣም አነስተኛ ተግባራት ይዘዋል። ይህ ጭብጥ የይዘቶች ተከታታይነትን እጥረት ይታይበታል። ምክንያቱም ተማሪዎች በአንዳንድ ምዕራፎች ውስጥ ብዙ ልምምድ እያገኙ በሌሎች ውስጥ እንደ ምዕራፍ 8 ሙሉ በሙሉ እድሉን ማግኘት አልቻሉም። ስለሆነም የተግባራት አለመመጣጠን የይዘቶች ተለጣጣቂነትን ውስኑነት እንዲኖረው አድርጎታል።

### *4.2.3.4 ተለጣጣቂነት እና የከፍተኛ ዕውቀት ደረጃዎች ተከታታይነት*

በመጀመሪያ ምዕራፎች (1–3) ውስጥ LOTS በተለይ U2 እና E5 የበላይነት አለው፤ ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን በመሰረታዊ ደረጃዎች ላይ ትኩረት ማድረጉን እንረዳለን ። ቀጥለው በሚመጡ ምዕራፎች (9–10) ውስጥ HOTS በተለይ C6 ጎልተው ይታያሉ። ለምሳሌ ምዕራፍ 9 C6 100%፣ ይህም የይዘቶች ተለጣጣቂነትን ያሳያል።

## 4.2.4 የመናገር ክሂል ይዘቶች ስርጭት

የመናገር ክሂል ይዘቶች በምዕራፎች መካከል የሚታዩ ዋና ዋና ጭብጦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የመናገር ክሂል 10ኛ ክፍል

| Cognitive lev | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | |
| R1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 8 | 80 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 8 | 25 |
| U2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| A3 | 1 | 100 | 0 | 0 | 1 | 10 | 2 | 100 | 2 | 100 | 0 | 0 | 1 | 33 | 8 | 100 | 2 | 100 | 1 | 33 | 18 | 56.3 |
| sub total | 1 | 100 | 0 | 0 | 9 | 90 | 2 | 100 | 2 | 100 | 0 | 0 | 1 | 33 | 8 | 100 | 2 | 100 | 1 | 33 | 26 | 81.3 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 10 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 100 | 2 | 67 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 33 | 5 | 15.6 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| C6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 33 | 1 | 3.13 |
| sub total | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 10 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 100 | 2 | 67 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 67 | 6 | 18.8 |
| TOTAL | 1 | 100 | 0 | 0 | 10 | 100 | 2 | 100 | 2 | 100 | 1 | 100 | 3 | 100 | 8 | 100 | 2 | 100 | 3 | 100 | 32 | 100 |

*ሰንጠረዥ 4.2.4 የመናገር ክሂል 10ኛ ክፍል*

### 4.2.4.1 የመተግበር ደረጃዎች በመናገር ክሂል 10ኛ ክፍል

የመተግበር ደረጃዎች በምዕራፍ 1 (A3 100%) ፣ ምዕራፍ 4 (A3 100%) ፣ ምዕራፍ 5 (A3 100%) ፣ ምዕራፍ 7 (A3 33.33%) እና ምዕራፍ 8 (A3 100%) ውስጥ ጎልቶ ይታያል። ስለሆነም ተማሪዎችን ለመተግበር (A3) እንዲዘጋጁ ያደርጋል። ይህም የይዘቶች ተከታታይነት በመተግበር ደረጃ ላይ እንዳለ ያመለክታል። ነገር ግን ይህ ተከታታይነት በመተግበር ደረጃዎች ላይ የተገደበ መሆኑ የይዘቶች ተለጣጣቂነት እጥረትን ያሳያል። ስለሆነም የመተግበር ደረጃዎች የበላይነት ተማሪዎችን ለተግባራዊ እውቀት እንዲዘጋጁ ቢያደርግም የመሰረታዊ ችሎታዎችን (R1 እና U2) ማጠናከር ክፍተት ይታይበታል። በአጠቃላይ የ10ኛ ክፍል የመናገር ተግባራት በA3 (56.25%) ላይ ያተኮሩ ናቸው።

### 4.2.4.2 ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃዎች በመናገር ክሂል 10ኛ ክፍል

ከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎች በ10ኛ ክፍል የመናገር ክሂል ላይ ለምሳሌ በምዕራፍ 3 (A4 10%) ፣ ምዕራፍ 6 (A4 100%)፣ ምዕራፍ 7 (A4 66.67%) እና ምዕራፍ 10 (A4 33.33% እና C6 33.33%) ብቻ ይገኛሉ። E5 ሙሉ በሙሉ የለም። ይህ ጭብጥ የይዘቶች ተለጣጣቂነትን ያሳያል። በመጀመሪያ ምዕራፎች ውስጥ HOTS ዝቅተኛ ነው። ነገር ግን በኋላኞቹ ምዕራፎች (6–10) ውስጥ ትንሽ ይታያል። ለምሳሌ፦ ከምዕራፍ አንድ ገጽ 11 ጀምሮ ከቀረቡላቸው ርእስ በመምረጥ ሐሳባቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸውን እንዲያቀርቡ፣ ገጽ 37 እንዲወያዩ እና የውይይት ጽሁፍ እንዲያቀርቡ፣ በገጽ 50 እንዲከራከሩ፣ ጥንድ ጥንድ ሆነው እንዲነጋገሩ እና ገጽ 128 የመድረክ ንግግር እንዲያቀርቡ የሚያደርጉ ይዘቶች ጥቂት ቢሆኑም ተካተዋል። ባጠቃላይ የከፍተኛ ዕውቀት ደረጃዎች HOTS (A4 ፣ E5 እና C6) በአማካይ (18.75%) ያላቸው

በአራት ምዕራፎች ብቻ የተካተቱ ተግባራት ይዘዋል። የዚህ ትንተና አጠቃላይ ጭብጥ የይዘቶች ተከታታይነት የተገደበ እንዲሆን አድርጎታል። ምክንያቱም HOTS በተወሰኑ ምዕራፎች ብቻ ስርጭቱ አነስተኛ ስለሆነ ነው። ስለሆነም የHOTS ውስንነት ተማሪዎችን ወደ ወሳኝ አስተሳሰብ (critical thinking) በሁሉም ምዕራፎች ሙሉ በሙሉ እንዳይሸጋገሩ ያደርጋል።

### *4.2.4.3 የምዕራፎች ምጥጥን እና ተከታታይነት በመናገር ክሂል 10ኛ ክፍል*

በዚህ ክሂልም የተግባራት ብዛት በምዕራፎች መካከል አልተመጣጠነም። ለምሳሌ ምዕራፍ 3 (10 ተግባራት) እና ምዕራፍ 8 (8) ብዙ ተግባራት አሏቸው፣ ምዕራፍ 2፣6 እና 9 (0፣1እና2) ደግሞ አነስተኛ ናቸው። ይህ ጭብጥ የይዘቶች ተከታታይነትን እጥረት ይታይበታል። ምክንያቱም ተማሪዎች በአንዳንድ ምዕራፎች ውስጥ ብዙ ልምምድ እያገኙ በሌሎች ውስጥ (እንደ ምዕራፍ 2) ምንም እድል የላቸውም። ስለሆነም የተግባራት አለመመጣጠን የይዘቶች ተለጣጣቂነትን ውስኑነት እንዲኖረው ያደርጋል።

### *4.2.4.4 ተለጣጣቂነት እና የከፍተኛ ዕውቀት ደረጃዎች ተያያዥነት*

በዚህ ክሂል በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች (1–5) ውስጥ LOTS በተለይ R1 የበላይነት አለው፤ ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን በቀላል ደረጃ ላይ ትኩረት ያደርጋል። ቀጥለው በሚመጡ ምዕራፎች (6–10) ውስጥ HOTS በተለይ A4 ጎልተው ይታያሉ። ለምሳሌ ምዕራፍ 6 A4 100%፣ ይህም ትንሽ የይዘቶች ተለጣጣቂነትን ያሳያል።

በአጠቃላይ የመናገር ክሂል ይዘቶች በመተግበር የእውቀት ደረጃዎች (A3) ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን በመሰረታዊ የዕውቀት ደረጃዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል።ነገር ግን የተለጣጣቂነትን ውሱንነት ጎልቶ ይታያል። የከፍተኛ ደረጃዎች ውስንነት መኖር ደግሞ ተማሪዎችን ውስብስብ ለሆኑ ተግባራት እንዳይዘጋጁ ያደርጋቸዋል። እንዲሁም የምዕራፎች አለመመጣጠን ተከታታይነትን እንዳይኖር አድርጎታል።

## 4.2.5 ማጠቃለያ ዓላማ ሁለት 10ኛ ክፍል

በ10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፍ ውስጥ የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀትን (ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት) ከRBT 2001 እይታ ስርጭት አኳያ መገምገም የጥናቱ ሁለተኛው ዝርዝር ዓላማ ሲሆን አራቱም የቋንቋ ክሂሎች በዚህ መጽሐፍ ያላቸው

አደረጃጀት በስፋት ከላይ የቀረበ ሲሆን የሚከተሉትን አጠቃላይ ውጤቶች ማቅረብ ይቻላል።

10ኛ ክፍል የትግርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት የቋንቋ ክሂሎች ተግባራት በተደረገው ትንተና መሰረት፣ በአጠቃላይ 91.94% በመሠረታዊ ዕውቀት ደረጃዎች (LOTS) ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ፣ ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃዎች (HOTS) በአጠቅላይ 11.06% ብቻ ይሸፍናሉ። በማንበብና ማዳመጥ ክህሎት ውስጥ HOTS ሙሉ በሙሉ የለም (0%)፣ ይህም ከ9ኛ ክፍል (3.4% እና 4.9%) ጋር ሲነፃፀር ግልጽ የኋሊት መመለስ (regression) ያሳያል። በመፃፍ ክህሎት ውስጥ HOTS 48% (መገምገም Evaluate 24% + መፍጠር Create 24%) በመድረሱ ከ9ኛ (43.5%) ትንሽ መሻሻል ቢያሳይም፣ በመናገር ክህሎት ደግሞ 18.75% ብቻ ነው። በአጠቃላይ ከ9ኛ ክፍል HOTS 11.06% ወደ 10ኛ 8.06% በ-3 ወደ ኋላ መመለስን አሳይቷል። የይዘቱ ተከታታይነት ጠንካራ ቢሆንም ዓምዳዊ ተለጣጣቂነት (vertical progression) በጣም ደካማ ነው። ስለዚህ መጽሐፉ ተማሪዎችን ወደ ከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎች (Analyze, Evaluate, Create) ለማደግ በቂ የሆነ ዓምዳዊ ተለጣጣቂነት አላሳየም። እንደ Krathwohl (2002፣ 215) RBT የትምህርት ዓላማዎችን በተግባራዊ መልኩ ለመፈተሽ ይረዳል። የHOTS ድርሻ መጨመር ተማሪዎችን ለችግር መፍቻ፣ ለውሳኔ አሰጣጥ፣ እና ለፈጠራ ያዘጋጃል። የLOTS ብቻ መቆየት የትምህርት ጥራትን ይጎዳል።" ይላል።

## 4.3 በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል መካከል ያለው ዓምዳዊ አደረጃጀት (RBT) ስርጭት

በ2008ዓ/ም ታትመው ስራ ላይ ባሉት የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል የትግርኛ ቋንቋ መማርያ መጽሐፎች የክሂሎች አምዳዊ አደረጃጀት ተገቢነት ከተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ (RBT 2001) የዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት እይታ መሰረት በማድረግ እንዴት እንደተደራጁ መገምገም የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ ሲሆን ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ ከሚመነጩት ዝርዝር ዓላማዎች መካከል ሶስተኛው ዓላማ በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መጽሐፍ መካከል የቀረቡ ክሂሎች ያላቸው ዓምዳዊ አደረጃጀት ማለትም የይዘቶች ተከታታይነት እና (የይዘቶች ተለጣጣቂነት ከእውቀት ደረጃዎች Anderson & Krathwohl (2001) ስርጭት እይታ አኳያ ከሰንጠረዥዎቹ መረጃ በመነሳት በአራቱ

ክሂሎች መካከል የሚታዩ ዋና ዋና ጭብጦች ትንተናው በተደራጀ መንገድ እንደሚከተለው ቀርቧል።

የማንበብ ክሂል 9ኛ ክፍል

| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|
| | ድምር | % |
| R1 | 106 | 45.3 |
| U2 | 112 | 47.86 |
| A3 | 8 | 3.419 |
| LOTS | 226 | 96.58 |
| A4 | 6 | 2.564 |
| E5 | 0 | 0 |
| C6 | 2 | 0.855 |
| HOTS | 8 | 3.419 |
| TOTAL | 234 | 100 |

የማዳመጥ ክሂል 9ኛ ክፍል

| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|
| | ድምር | % |
| R1 | 32 | 39.5 |
| U2 | 45 | 55.6 |
| A3 | 0 | 0 |
| LOTS | 77 | 95.1 |
| A4 | 3 | 3.7 |
| E5 | 1 | 1.23 |
| C6 | 0 | 0 |
| HOTS | 4 | 4.94 |
| TOTAL | 81 | 100 |

የመፃፍ ክሂል 9ኛ ክፍል

| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|
| | ድምር | % |
| R1 | 1 | 1.449 |
| U2 | 1 | 1.449 |
| A3 | 37 | 53.62 |
| LOTS | 39 | 56.52 |
| A4 | 2 | 2.899 |
| E5 | 8 | 11.59 |
| C6 | 20 | 28.99 |
| HOTS | 30 | 43.48 |
| TOTAL | 69 | 100 |

የመናገር ክሂል 9ኛ ክፍል

| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|
| | ድምር | % |
| R1 | 0 | 0 |
| U2 | 8 | 34.783 |
| A3 | 12 | 52.174 |
| LOTS | 20 | 86.957 |
| A4 | 2 | 8.6957 |
| E5 | 1 | 4.3478 |
| C6 | 0 | 0 |
| HOTS | 3 | 13.043 |
| TOTAL | 23 | 100 |

*ሰንጠረዥ 4.3 ሀ አራቱም የቋንቋ ክሂሎች የRBT 2001 ስርጭት 9ኛ ክፍል*

የማንበብ ክሂል 10ኛ ክፍል

| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|
| | ድምር | % |
| R1 | 132 | 55.23 |
| U2 | 104 | 43.51 |
| A3 | 3 | 1.255 |
| LOTS | 239 | 100 |
| A4 | 0 | 0 |
| E5 | 0 | 0 |
| C6 | 0 | 0 |
| HOTS | 0 | 0 |
| TOTAL | 239 | 100 |

የማዳመጥ ክሂል 10ኛ ክፍል

| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|
| | ድምር | % |
| R1 | 28 | 54.9 |
| U2 | 23 | 45.1 |
| A3 | 0 | 0 |
| LOTS | 51 | 100 |
| A4 | 0 | 0 |
| E5 | 0 | 0 |
| C6 | 0 | 0 |
| HOTS | 0 | 0 |
| TOTAL | 51 | 100 |

የመፃፍ ክሂል 10ኛ ክፍል

| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|
| | ድምር | % |
| R1 | 0 | 0 |
| U2 | 9 | 18 |
| A3 | 17 | 34 |
| LOTS | 26 | 52 |
| A4 | 0 | 0 |
| E5 | 12 | 24 |
| C6 | 12 | 24 |
| HOTS | 24 | 48 |
| TOTAL | 50 | 100 |

የመናገር ክሂል 10ኛ ክፍል

| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|
| | ድምር | % |
| R1 | 8 | 25 |
| U2 | 0 | 0 |
| A3 | 18 | 56.25 |
| LOTS | 26 | 81.25 |
| A4 | 5 | 15.625 |
| E5 | 0 | 0 |
| C6 | 1 | 3.125 |
| HOTS | 6 | 18.75 |
| TOTAL | 32 | 100 |

*ሰንጠረዥ 4.3 ለ አራቱም የቋንቋ ክሂሎች የRBT 2001 ስርጭት 10ኛ ክፍል*

ከሰንጠረዥዎቹ መረጃ በመነሳት በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች መካከል የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት የሚታዩ ዋና ዋና ጭብጦች እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

### 4.3.1 መሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች እና ተከታታይነት በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል መካከል

በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ LOTS (R1 እና U2) የበላይነት አለው። በተለይ በማንበብ 9ኛ ክፍል 97%፣ 10ኛ ክፍል 100% እና ማዳመጥ 9ኛ ክፍል 95.06%፣ 10ኛ ክፍል 100% ይሸፍናል። ይህ ጭብጥ የይዘቶች ተከታታይነትን በመሰረታዊ ደረጃ ላይ መኖሩን ያሳያል። ተማሪዎች በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ማስታወስ

(R1) እና መረዳት (U2) ላይ ያተኮሩ ናቸው። ለምሳሌ፣ በማንበብ ውስጥ R1 ከ9ኛ ክፍል 45.30% ወደ 10ኛ ክፍል (55.23%) ይጨምራል፣ ይህም ማለት ከምንባቡ የወጡ የማስተዋል ጥያቄዎች ቀንሶ ምንባቦቹ የመተንተን፣ የመገምገም እና የማጠቃለል ተግባራዊ ጥያቄዎች መጨመር ሲገባው በተቃራኒው ቀንሷል። ይህም ተከታታይነትን በመሰረታዊ ደረጃዎች የሚያሳይ ቢሆንም ነገር ግን ተለጣጣቂነት እጥረት ይታይበታል።


### 4.3.2 ከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎች እና ተለጣጣቂነት በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል መካከል

ከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎች እና ተለጣጣቂነት በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል መካከል መረጃው እንደሚያመለክተው በማንበብ 9ኛ ክፍል 3%፣ በ10ኛ ክፍል 0% ሲሆን ፤ በመፃፍ 9ኛ ክፍል 43.48%፣ 10ኛ ክፍል፣ 48%፤ እንዲሁም በመናገር 9ኛ ክፍል 13.04%፣ 10ኛ ክፍል 18.75% ውስጥ ብቻ ይገኛል። ስለሆነም ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃዎች HOTS በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ዝቅተኛ ነው። በማንበብ እና ማዳመጥ ውስጥ HOTS በ10ኛ ክፍል በሁለቱም ክሂሎች 0% ሲሆን በ9ኛ ክፍል በቅደም ተከተል 3.4 እና 4.9 በጣም ዝቅተኛ ቁጥር ይሸፍናሉ። ይህ ጭብጥ የይዘቶች ተለጣጣቂነትን እንደሌለ ሲያመለክት በመፃፍ እና መናገር ውስጥ ትንሽ መጨመር ይታይበታል። በመፃፍ ከ43.48% ወደ 48%፣ በመናገር ከ13.04 ወደ 18.75%% በሁለቱም 5% መጨመሩን ሲያመለክት ይህም ተማሪዎች ከ9ኛ ክፍል በበለጠ በተለያዩ የጽህፈት ክሂል ተግባራዊ ልምምዶች በተከታታይና በተለጣጣቂነት እንዲማሩ የሚያደርግ ነው። ነገር ግን በማንበብ እና ማዳመጥ ውስጥ መቀነስ ወይም እጥረት መኖር ተለጣጣቂነት እንዳይኖር አድርጎታል።

### 4.3.3 በክሂሎች መካከል የተግባራት ምጥጥን እና ተከታታይነት

በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ የተግባራት ብዛት በክሂሎች መካከል መመጣጠን አይታይበትም። ለምሳሌ፣ ማንበብ በሁለቱም ውስጥ 234 በ9ኛ ክፍል፣ 239 በ10ኛ ክፍል ብዙ ተግባራት ሲኖሩት፤ መናገር ደግሞ 23 በ9ኛ ክፍል፣ 32 ተግባራት ደግሞ በ10ኛ ክፍል አነስተኛ ተግባራት እናገኛለን ። ከዚህ ትንተና የምንረዳው የይዘቶች ተከታታይነትን የተወሰነ መሆኑን እንገነዘባለን፤ ምክንያቱም ተማሪዎች በማንበብ ክሂል

ውስጥ ብዙ የልምምድ ተግባራት እያገኙ በተቀሩት ክሂሎች ውስጥ አነስተኛ ሆኖ እናገኘዋለን።



ግራፍ 4.3.3 በክሂሎች መካከል የተግባራት ምጥጥን


## 4.3.4 ተለጣጣቂነት እና የመሰረታዊ ደረጃዎች ተከታታይነት

በመጀመሪያ የክፍል ደረጃ ውስጥ የመሰረታዊ ደረጃዎች LOTS በተለይ በማንበብ እና ማዳመጥ ውስጥ የበላይነት አለው። ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን ቀለል ባሉ የዕውቀት ደረጃዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል። በ10ኛ ክፍል ውስጥም በተመሳሳይ ተከታታይነት ይታያል ነገር ግን ትንሽ ተለጣጣቂነት በመፃፍ እና መናገር ውስጥ HOTS መጨመር አለ።

በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል መፃሕፍት መካከል የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት በመሰረታዊ ደረጃዎች (LOTS) ላይ የተገነቡ ናቸው። በ9ኛ ክፍል LOTS ከ407 ተግባራት 362 ሲሆኑ በመቶኛ 88.94% ይሸፍናል፤ በ10ኛ ክፍል ደግሞ ከ372 ጠቅላላ ተግባራት 342 የLOTS ጥያቄዎች ሲሆኑ 91.94% ስርጭቱን የያዙ ናቸው። ስለሆነም በማንበብና ማዳመጥ ቀለል ባሉ የማስታወስና የመረዳት ጥያቄዎች መጠመዳቸውን ከትንተናው መረዳት ይቻላል። ይህም የይዘቶች ተከታታይነት ቀለል ባሉ የእውቀት ደረጃዎች ላይ

ትኩረት ሲያደርግ፤ ነገር ግን የተለጣጣቂነትን እጥረት በማንበብና ማዳመጥ ተግባራት ላይ ይስተዋላል። ሆኖም ግን በመፃፍ እና መናገር በመጠኑም ቢሆን ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት ይታይበታል። ባጠቃላይ ከተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ ስርጭት እይታ አኳያ የከፍተኛ ደረጃዎች ውስንነት ተማሪዎች ከበድ ባሉ የትምህርት ይዘቶች ትኩረት ባማድረግ በጥልቀት እንዲያስቡ፣ እንዲመራመሩ፣እና ለውስብስብ ተግባራት ተዘጋጅተው የቋንቋ ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ተደርገው ተሚልተው አልተዘጋጁም።

## የክሂሎች ንፅፅር በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል መፅሐፍ




ስእል 4.3.3

### 4.3.5 ማጠቃለያ ዓላማ ሶስት

በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል መጽሐፎች መካከል ያለው የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት ንጽጽር (ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት ከRBT 2001 እይታ አኳያ) የጥናቱ ሶስተኛ ዓላማ ሲሆን በዝርዝር እላይ ከቀረበው ትንተና በመነሳት እንደሚከተለው የውጤት ማጠቃለያ ተሰጥቶታል።


በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማሪያ መጽሐፎች መካከል ያለው ዓምድያዊ አደረጃጀት በተደረገው ትንተና መሰረት፣ በመሰረታዊ የዕውቀት ደረጃዎች (LOTS) ከ88.94 ወደ 91.94% (R1፣U2 እናA1) ላይ በሁለቱም መጽሐፎች ተመሳሳይነት ያለው በጣም ጠንካራ የይዘት ተከታታይነት በመሰረታዊ የዕውቀት ደረጃዎች ላይ ያሳያል። ይህም ተማሪዎች በሁለቱ ክፍሎች በተመሳሳይ መሰረታዊ እውቀትን በተደጋጋሚ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ይህም በይዘቱ መሰላቸትን በተማሪዎችም በመምህሩም በአጠቃላይ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ተፅእኖ ይፈጥራል። ስለሆነም Anderson & Krathwohl (2001) መሰረት በማድረግ "በመጽሐፎች እና በትምህርት ዲዛይን ውስጥ የHOTS ድርሻ መጨመር የተማሪዎችን ወሳኝ አስተሳሰብ፣ ችግር መፍቻ እና ፈጠራ ያዳብራል፤ ሆኖም ግን የLOTS በላይነት ይህን እድገት ይገታል።" Wilson (2016፣1) በማለት ግኝቱን ይገልፀዋል። በተቃራኒው፣ ተለጣጣቂነት (progression) በጣም ደካማ ነው። ከ9ኛ ወደ 10ኛ ክፍል ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃዎች (HOTS) በአጠቃላይ ከ11.06% → 8.06% ልዩነት -3% (regression in cognitive progression) ወደ ኋላ ቀንሷል፤ በአራቱም ክሂሎች ያለው ተለጣጣቂነት በማንበብ ክሂል → 3.4% → 0% እና በማዳመጥ ክሂል → 4.9% → 0% ወደ ኋላ የተመለሱ ሲሆኑ ምክንያቱ ደግሞ 9ኛ ክፍል ከተዘጋጀበት መንገድ በባሰ መልኩ ቀለል ባሉ የትምህርት ይዘቶች ትኩረት በማድረግ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ የእውቀት ክህሎት እንዲሸጋገሩ ተደርጎ በማንበብና ማዳመጥ ክሂሎች ላይ አለመዘጋጀቱ ያመለክታል። በተጨማሪም በተለይ በማዳመጥ ክሂል የመጨረሻዎቹ ተከታታይ አምስት ምዕራፎች በመጽሐፉ አልተካተቱም። እንዲሁም በመናገር ክሂል→ 13.04% → 18.75% እና በመፃፍ ክሂል → 43.5% → 48% ትንሽ መሻሻል የታየባቸው ሲሆኑ ቀደም ሲል በትንተናው እንደተገለፀው በሁሉም ምዕራፎች ባይሆንም ተማሪዎች በተግባራዊ ስራ እንዲጠመዱ እናም የመተንተን፣የመገምገም እና የማፍለቅ ስራዎች እንዲለማመዱ ተከታታይነትና ተላጣጣቂነት በመጠኑም ቢሆን እንዲኖር አድርጎታል። ለምሳሌ ያህል በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል ከተካተቱ የመናገር እና የመፃፍ ይዘቶች ውስጥ፤ 9ኛ ክፍል የመናገር ክሂል ተግባራት "ስርዓት ጠብቆ ገምቢ ሐሳቦች፣አስተያየቶች፣ በመረጃ ተደግፈው ተገቢ ጥያቄ በመጠየቅና በመመለስ በወግ፣ በውይይት እና በክርክር በነፃነት የሚያሳትፉ ጥያቄዎች፤ የነገሮች አጠቃቀም እና መመርያ በቅደም ተከተል መጠቀም፤ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ንግግር ሲያደርጉ የፊት ገጽታ መለዋወጥ እና በእንቅስቃሴ

የታጀበ ንግግር በቅደም ተከተል ማቅረብ፤ ካነበቡት አለያም ካዳመጡት ንግግር በመነሳት በራሳቸው አባባል ንግግር እንዲያቀርቡ ማድረግ፤ ስላደመጡት ርእሰ ጉዳይ በምክንያትና ውጤት መግለጽ፤ እንዲሁም በጽሁፍ የተዘጋጀ ንግግር ማድረግ የሚሉ ተግባራት በዘጠነኛ ክፍል ቀርበው በተመሳሳይ በ10ኛ ክፍልም በተከታታይነት የቀረቡ ሲሆኑ ከተለጣጣቂነታቸው አኳያም የ5.71% ጭማሪ በተወሰነ መልኩ አሳይቷል። የመፃፍ ይዘቶች በተመለከተ ከቀረቡ ተግባራት በምሳሌነት፦ ቀስ በቀስ ተገቢ አያያዥ ቃላት እና ሐረጎች ተጠቅመው የአንቀጽ አደረጃጀት መመርያ ተከትለው ሐሳባቸው መፃፍ፤ ቃለ ጉባኤ ማዘጋጀት፤ የተለያዩ የደብዳቤ አይነቶች በተገቢው ቅርጽ ማደራጀት እና መፃፍ፣ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት ተጠቅመው እንደ ተራኪ፣ ገላጭ፣ ስእላዊ እና አመዛዛኝ ድርሰት መፃፍ፣ የሐሳብ ፍሰትን ለመጠበቅ ብለው ቃላት፣ ሐረጋት፣ ዓረፍተ ነገሮች እና ሌሎች አስፈላጊ ሐሳቦች በመጨመር፣ በማስወገድ፣ በማሳጠር፣ ስርዓተ ነጥብ እና የቃላት አጠቃቀም በማሻሻል የፃፉትን ረቂቅ አስተካክለው እና ገምግመው ማቅረብ፤ ግጥሞችን መገምገም፣ ከተለያዩ ንግግሮች እና ጽሁፎች ያገኟቸው መረጃዎች በተገቢ መንገድ በማደራጀት የማስታወሻ አያያዝ ስርዓት ተጠቅመው መረጃ መያዝ፣ እና ሌሎች የተማሪዎችን የጽህፈት ክህሎት የሚያሳድጉ ተግባራት በሁለቱም የደረጃ ክፍል መካተታቸው የይዘቶች ተከታታይነት መኖሩ ያመለክታል፤ እንዲሁም ተለጣጣቂነት በተመለከተ 9ኛ ክፍል ከነበረው በ4.5% ጨምሯል።

በማንበብ እና ማዳመጥ ይዘቶች መካከል በቅደም ተከተል ከቀረቡት የማንበብ ተግባራት መካከል ይህ ውጤት ከተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ (2001) መርህ ጋር ተቃራኒ ሲሆን፤ ከክፍል ወደ ክፍል የእውቀት ደረጃ እንደ መጨመር፤ መቀነስን ያሳያል። ስለዚህ መጽሐፎቹ ተማሪዎችን ከመሰረታዊ ዕውቀት ወደ ከፍተኛ ዕውቀት ደረጃዎች መተንተን (Analyze)፣ መገምገም (Evaluate) እና መፍጠር (Create) ለመሸጋገር የሚያስችል በቂ የሆነ የዕውቀት ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት አላሳዩም። "የትምህርት ይዘቶች በLOTS (Remembering፣ Understanding፣ Applying) እና HOTS (Analyzing፣ Evaluating፣ Creating) መካከል ሚዛናዊ ስርጭት ሊኖራቸው ይገባል። ከLOTS ወደ HOTS ቀስ በቀስ መሸጋገር የይዘቶችን ተለጣጣቂነት ያረጋግጣል። የHOTS ውስንነት ተማሪዎችን ለወሳኝ አስተሳሰብ እንዳይዘጋጁ ያደርጋል።" Anderson & Krathwohl (2001 ፣67–68) ፣ Krathwohl (2002፣ 215)። በማለት በተመሳሳይ መንገድ ሲገልፁት፤ በማንበብ እና ማዳመጥ የተገኘው

የትንተና ውጤት እንደሚያሳየው ምሁራኑ ያቀረቡት ሐሳብ ጋር ተስማሚ መሆኑ አጥኚው አረጋግጧል።

ከላይ የቀረበው የዓላማ ሶስት ማጠቃለያ ሐሳብ በሚከተለው ግራፍ በአጭሩ መግለፅ ይቻላል።




ስእል 4.3.5 ከ9ኛ ወደ 10ኛ ክፍል ያለው ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት ከRBT 2001 እይታ አንፃር

## 4.4 የቃለ መጠይቅ ትንተና

### 4.4.1 ከመጽሐፍ አዘጋጅ የተገኘ መረጃ

ዋና አዘጋጆቹ ሶስት ሲሆኑ በዓላማዊ ናሙና አመራረጥ ዘዴ (Purposive Expert Sampling) ተመርጠው ነበር። ሁለቱ በጡረታ ምክንያት ባለመገኘታቸው ከአንድ ባለሙያ ጋር ቃለ-መጠይቅ ተካሂዷል። ለያንዳንዱ ዓላማ አራት አራት ተመሳሳይ ጥያቄዎች እና አንድ የማጠቃለያ ጥያቄ በድምር አስራ ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች የቀረቡላቸው ሲሆኑ፤ ከነዚህ መረጃዎች የተገኙ ዋና ጭብጦች የሚከተሉት ናቸው።

በመጀመሪያ፣ አዘጋጁ የተደረገውን ጥረት አንስተው እንዲህ በማለት ይመልሳሉ «ምዕራፎቹ እርስ በርስ ተያያዥነት እንዲኖራቸው፣ ከቀላል ወደ ከባድ እንዲደራጁ ታስቦ ነበር። ይህን ለማሳካት የምዕራፍ ዝርዝር እቅድ (outline) ተዘጋጅቶ ነበር።»

ሁለተኛ፣ በአዘጋጆች መካከል የቡድን ስራ አለመኖር ተጠቅሷል። «እያንዳንዱ ምዕራፍ ተከፋፍለን ነው ያዘጋጀነው፤ ቡድናዊ ውይይት አልተደረገም። ከአሳታሚው ድርጅት ጋርም ግንኙነት ደካማ ነበር።» ይህ የተካታታይነት እና የተለጣጣቂነት እጦት ዋና መንስኤ መሆኑን ያሳያል።

ሶስተኛ፣ በተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ ላይ የስልጠና እጥረት መኖሩን የቃለ መጠይቁ መረጃ ያመላክታል። «ልዩ ስልጠና አልተሰጠንም። አብዛኞቻችን የቀድሞውን ታክሶኖሚ ብቻ ነበር የምናውቀው እንደሞዴልም አልተጠቀምንበትም።» ይህም በኪሂሎች መካከል የLOTS እና HOTS መመጣጠን እንዳይኖር ምክንያት መሆኑ መረዳት ይቻላል።

አራተኛ፣ አነስተኛ ክፍያና የባለሙያ እጥረት ተጠቅሷል። «የሚከፈለው ክፍያ በጣም አነስተኛ ስለነበር በትኩረት ለመስራት አያበረታታም።»

አምስተኛ፣ የሐብት እጥረት መኖሩ ተጠቁሟል። «የሰው ሐይል፣ ቁሳቁስ፣ ማመሳከሪያ መጽሐፎች፥ በቂ የኢንተርኔት አገልግሎት፣ የገንዘብ ድጋፍ እነዚህ ሁሉ ውሱን መኖራቸው።» ይገልፃሉ።

### 4.4.2 ከመምህራን የተገኘ መረጃ

በ9ኛና 10ኛ ክፍል ትግርኛ ቋንቋ ቢያንስ 30 ዓመታትና ከዚያ በላይ ያስተማሩ መምህራን (3 ሰዎች) በዓላማዊ ናሙና አመራረጥ ዘዴ (Purposive Sampling – Criterion Sampling) ተመርጠው በቃለ መጠይቁ ተሳትፈዋል። ለነዚህ መምህራን ለያንዳንዱ ዓላማ አምስት መሰረታዊ ጥያቄዎች በድምር አስራ አምስት ጥያቄዎች ተዘጋጅተው መጠይቁ የተካሄደ ሲሆን፤ ከተደረገው መጠይቅም በተግባራዊ ልምዳቸው ላይ ተመስርተው የሚከተሉትን ዋና ጭብጦች አንስተዋል።

በመጀመሪያ፣ መሰረታዊ የዕውቀት ደረጃዎች ከመጠን በላይ መደጋገምን ገልፀዋል። «በ9ኛም በ10ኛም መጽሐፍ ውስጥ ተማሪዎች ተመሳሳይ የማንበብና የማዳመጥ ተግባር

ብቻ ያገኛሉ። ከአመት ወደ አመት እንደ ቀድሞው ይደግሙታል። ይህን ደጋግሞ ማስተማር ያስቸግራል።» ለማለት የተፈለገው በተመሳሳይ ቅርጽ በ9ኛም ይሁን በ10ኛ በርካታ ተግባራት የሚሸፍኑ ተግባራት መኖራቸውን ለመግለጽ እና ተከታታይነት በLOTS መኖሩን አመላክተዋል።

ሁለተኛ፣ የከፍተኛ ደረጃ ክሂሎች ውስኑነትንም ገልፀዋል። «በ10ኛ ክፍል መጽሐፉ ውስጥ ተማሪዎች የመተንተን፣ የመገምገም፣ የመፍጠር ተግባር ብዙም አይስተዋሉም። በተለይ በማንበብና ማዳመጥ ተግባራት ውስጥ ሁሉም መልመጃዎች የሚሰጠው መልስ በቀጥታ የሚገኝ የማያመራምር ነው። ይህ ተማሪዎች እንዳያስቡ ያደርጋቸዋል።» በማለት የተለጣጣቂነት ደካማነቱን ያብራራሉ።

ሶስተኛ፣ በመፃፍና መናገር ውስጥ ያለውን ትንሽ ከበድ ያሉ የተግባር ስራዎች መኖራቸው ጠቅመዋል። «በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የጽሁፍ ግምገማ፣ የድርሰት መፃፍ፣ የንግግር ዝግጅት ተግባር ተጨምሯል። ነገር ግን ይህ በቂ አይደለም።» እዚህ ላይ የሁለቱ ክሂሎች ጠንካራነት እና በHOTS ተለጣጣቂነት መኖር ከተግባራዊ ተሞክሮአቸው አካፍለዋል።

በመጨረሻም ያቀረቡት ምክረ ሐሳብ። «መጽሐፉ እንደገና መከለስ አለበት። በተለይ በ10ኛ ክፍል ውስጥ ከፍተኛ የእውቀት ደረጃ መጨመር አለበት። መምህራንም በተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ ላይ ስልጠና መሰጠት አለበት።» በማለት አስተያየታቸውን አክለዋል።

### 4.4.3 የሶስቱ መረጃዎች ውህደት (Triangulation)

ከሰነድ ትንተና፣ ከመጽሐፍ አዘጋጅ እና ከመምህራን የተገኘው መረጃ በጣም ይስማማሉ። ይህም የጥናቱን ውጤት ታማኝነት እና ትክክለኛነት ከፍ አድርጎታል።

በመጀመሪያ፣ ሰነድ ትንተናው በአጠቃላይ ከ9ኛ ወደ 10ኛ ክፍል ያለው ተለጣጣቂነት በ0.47 ተላጣጣቂነት ወደ (HOTS) 8.06% ዝቅ ያለ ሲሆን፣ እንዲሁም በማንበብና ማዳመጥ ክሂሎች ውስጥ ደግሞ በ10ኛ ክፍል HOTS ሙሉ በሙሉ ወደ ኋላ ተመልሷል፤ ወደ (0%) አሳይቷል።

ሁለተኛ፣ አዘጋጁ ይህን ውጤት በሚከተሉት ምክንያቶች አብራርተዋል፤ በተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ ላይ ስልጠና አለመሰጠት እና እንደ ሞዴል አለመጠቀም፤ ቡድናዊ ስራ አለመኖር (ምዕራፎች በተናጠል መዘጋጀት)፤ ከአሳታሚው ድርጅት ጋር ግንኙነት ደካማ መሆን፤ አነስተኛ ክፍያና የሐብት እጥረት ተጠቅሰዋል።

ከመምህራን የተገኘው አጠቃላይ መረጃም የሚያመለክተው እንደ ቋንቋ መምህራን ባለሞያነታቸው መጽሐፉ የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር ዋና ዓላማው አድርጎ መዘጋጀት ሲገባው፤ ለስነጽሁፍና ለስዋሰው ተግባራት ትኩረት በማድረግ ከበድ ያሉ ጥያቄዎች ከክሂሎች በበለጠ ማካተቱ፤ በተለይ በማንበብ እና ማዳመጥ በቀላል ጥያቄዎች የተጠመዱ ከመሆናቸው በላይ መቆራረጥ ይታይባቸዋል። ምክንያቱም ጠቅልሎ ክሂሎቹ ከመጽሐፉ መጥፋትም አለ። ስለሆነም ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ከቀላል ወደ ከባድ ተመጣጣኝ ተግባራት በያንዳንዱ ምዕራፍ እና ደረጃ ክፍል ተደራጅተው መዘጋጀት እንዳለባቸው ውጤቱ ያመለክታል።

ስለሆነም ሶስቱ መረጃዎች በግልጽ ይስማማሉ። መጽሐፉ በመሰረታዊ የዕውቀት ደረጃ ላይ ትኩረት አድርጎ ተከታታይነት በራሱ ላይ ቢሰራም ፤ የከፍተኛ የዕውቀት ደረጃዎች ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነቱ ደካማ ነው። ይህም በአብዛኛው በተሻሻለው የብሉምስ ታክሶኖሚ ላይ በቂ ስልጠና አለመውሰድ፣ ቡድናዊ ስራ አለመኖርና የሐብት ጉድለት ተጠቃሽ ምክንያት ናቸው።

# ምዕራፍ አምስት፦ማጠቃለያ እና መፍትሔ ሐሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

በ2008ዓ/ም ታትመው ስራ ላይ ባሉ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የትግርኛ መማርያ መጽሐፎ ውስጥ ያሉ የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀትን ከተሻሻለው የብሉም ታክሶኖሚ የዕውቀት ደረጃዎች ስርጭት አይታ አኳያ ምን እንደሚመስሉ ተገምግመዋል። ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ እና ከአዘጋጆች እና መምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በመጠቀም በ9ኛ ክፍል ያለው ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት እንዲሁም፤ በ10ኛ ክፍል እናም ከ9ኛ ወደ 10ኛ ክፍል ያለው ዓምዳዊ አደረጃጀት ምን ይመስላል? ለሚሉ መሪ ጥያቄዎች ማጠቃለያው እንደሚከተለው ቀርቧል።

በያንዳንዱ የክፍል ደረጃ እና በሁለቱም መካከል የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት (Vertical Alignment) ምን ይመስላል? ለሚለው አጠቃላይ መሪ ጥያቄ እንደሚከተለው ተጠቃልዋል።

የክሂሎች ተያያዥነት፦

የአራቱ ክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት በመሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች (LOTS) ላይ የተገነባ ነው፤ ይህም መሰረታዊ እውቀትን ያጠናክራል ነገር ግን ወደ ከፍተኛ የእውቀት ደረጃ (HOTS) መሸጋገርያ ድልድዩ በጣም ጠባብ ነው ። ስለሆነም ማንበብ እና ማዳመጥ በመሰረታዊ ደረጃዎች ላይ ተመሳሳይ ናቸው፤ እድገት የለም፤ መፃፍ እና መናገር ደግሞ በመተግበር እና በከፍተኛ የማሰብ ችሎታ (HOTS) ላይ ተመሳሳይ እድገት አላቸው፤ ትንሽ መጨመር ይታይባቸዋል። ይህ ተያያዥነት ከፍ ካሉ ደረጃዎች (HOTS) ጋር ተጣምሮ እድገትን አያሳይም፤ ምክንያቱም HOTS በመፃፍ እና መናገር ውስጥ ብቻ ጎልተው ስለሚታዩ ነው፤ ማንበብ እና ማዳመጥ ደግሞ ዝቅተኛ ናቸው። ይህ የሚያመለክተው የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት ውስኑነትን ነው፤ ምክንያቱም ተማሪዎች በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል በተመጣጣኝ ተለጣጣቂነትን አያገኙም።

የLOTS እና የHOTS ስርጭት፦

በሁለቱ መፃሕፍት ውስጥ የክህሎች አጠቃላይ ተግባራት (779) በአማካይ 90.37% በበመሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች (LOTS R1፣ U2 እና A3) እና 9.62% በHigher-Order Thinking Skills (HOTS A4፣ E5 እና C6) ይወከላሉ። በተለይ ማንበብ እና ማዳመጥ በLOTS ላይ በስፋት ይታያሉ ፤ በ9ኛ ክፍል በቅደም ተከተል 97% እና 95%፣ በ10ኛ ክፍል 100% እና 100%) ሆነው ተገኝተዋል፤ ይህም የይዘቶች ተከታታይነት በመሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች ማስታወስ እና መረዳት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ነገር ግን የይዘቶች ተለጣጣቂነት እንዲኖር ተብሎ ወደ ከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎች ሲሸጋገር አይታይም። በተለይ በነዚህ ክሂሎች ተማሪዎች ከክፍል ወደ ክፍል ሲሸጋገሩ ዝቅተኛ ያማሰብ ችሎታ እየቀነሱ ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ እየጨመሩ እንደመሄድ በተቃራኒው ሆነው ተገኝተዋል።

መፃፍ እና መናገር ደግሞ በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ በመተግበር (A3) ላይ ያተኮሩ ናቸው። በR1 እና U2 ትኩረት አልተደረገባቸውም። ባጠቃላይ እነዚህ ክሂሎች በቅደም ተከተል በ9ኛ ክፍል 43.48% እና 13.04%፣ በ10ኛ ክፍል 48% እና 18.75% በከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎች በHOTS ትንሽ እድገት መኖር በመጠኑ የይዘቶች ተለጣጣቂነት ያሳያል ነገር ግን በእነዚህ ክሂሎች ብቻ የሚታይ ነው። ስለሆነም ተማሪዎችን ከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎች ችሎታ ለሚባሉት እንደ ትንተና፣ ግምገማ እና ፈጠራ በበቂ ሁኔታ እንዲዘጋጁ አያደርግም፣ ይህም የመገምገምያ መስፈርቱ ሚዛንን ይጥሳል።

የምዕራፎች እና የክሂሎች ምጥጥን፦

በመጽሐፎቹ የቀረቡ ተግባራት በምዕራፎች መካከል መመጣጠን አይታይባቸውም። ይህም በአራቱ ክሂሎች መካከል ተመሳሳይ ነው። ለምሳሌ በማንበብ ክሂል በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ምዕራፍ 9 ብዙ ተግባራት አሉት፤ ምዕራፍ 3 ደግሞ አነስተኛ ነው፤ ማዳመጥ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በተወሰኑ ምዕራፎች ብቻ ይገኛል በተለይ በ10ኛ ክፍል 5፣ 6፣ 7፣ 8 እና 10 የደረጃ ክፍሉ የማንበብ ክሂል 50% በመጽሐፉ እስከነጭራሹ የለም፤ ይህም የይዘቶች ተከታታይነትን እንዳይኖር ያደርጋል። በክሂሎች መካከልም ማንበብ እና ማዳመጥ በመሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች (LOTS) ላይ የተሰራጩ ሲሆን፣ መፃፍ እና መናገር ደግሞ በተወሰኑ ምዕራፎች ብቻ ይገኛሉ። ይህ ተያያዥነት የእውቀት ደረጃዎች ስርጭትን እንዳልተመጣጠነ ያሳያል።

ከአዘጋጆች ቃለ መጠይቅ ጋር ተያይዞ፦ አዘጋጆች በጥንካሬ የገለፁት ምዕራፎች ተያያዥነት እንዲኖራቸው እና ከቀላል ወደ ከባድ እንዲደራጁ ጥረት እንደተደረገ የሚገልጽ ሲሆን፤ ይህ በትንተናው ውስጥ በመፃፍ እና መናገር ውስጥ የታየውን ትንሽ እድገት ይደግፋል። ነገር ግን በደካማ ጎን የተገለፁት እንደ ግንኙነት እጥረት (በመጽሐፍ አዘጋጆች እና በአሳታሚው ድርጅት መካከል)፣ አነስተኛ ክፍያ፣ በእውቀት ደረጃዎች ላይ (የመጽሐፍ አዘገጃጀት ሞዴሎች) ትኩረት አለመደረጉ፣ የአቅም ጉዳይ፣ የስልጠና እጥረት፣ የግንኙነት ችግር (በአዘጋጆች መካከል የቡድን ስራ አለመኖር ምዕራፎች በተናጠል ተከፋፍሎ ለየግል መስራት)፣ እና የሐብት እጥረት (ሰው ሐይል፣ ገንዘብ፣ ማተርያል) የተጠቀሱ ሲሆን፤ ይህም በትንተናው ውስጥ የታየውን የHOTS ውስንነት፣ የምዕራፎች አለመመጣጠን እና የክሂሎች ሚዛን እጥረት ያብራራል።

በአጠቃላይ፣ የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀት በመሰረታዊ የእውቀት ደረጃዎች (LOTS) በማስተዋል እና የመረዳት ጥያቄዎች (recall & undrstunding) ላይ የተወጠረ ሲሆን፤ ከ9ኛ ወደ 10ኛ ክፍል ያለው እድገት በመፃፍ እና መናገር ውስጥ የመተንተን የመገምገም እና የማፍለቅ ተግባራት በመፃፍ እና መናገር (እንዲናገሩ፣ እንዲወያዩ ፣እንዲከራከሩ፣ በራሳቸው አባባል እንዲያቀርቡ፣ ቃለ ጉባኤ እንዲጽፉ፣ ስርዓተ ነጥቦች እንዲጠቀሙ፣ ዓንቀፆች እንዲያደራጁ፣ የተለያዩ ድርሰቶች እንዲጽፉ፣ ግጥሞች እንዲገመግሙ የሚያደርጉ ተግባራት በመጠኑ ቢታይም፣ በማንበብ እና ማዳመጥ ውስጥ ከፍተኛ የእውቀት ደረጃዎች (HOTS) በተቃራኒው የቀነሱ ናቸው፤ ያዳመጡትን እና ያነበቡትን ከራሳቸው ሂወት ጋር በማዋሐድ ነገሮችን የመተንተን እና የመቀበል ክሂላቸው እንዳይጠነክር ያደርጋል። ሲጠቃለል መጽሐፎቹ ለማፍለቅያ ክሂል በመጠኑም ቢሆን ትኩረት ሲያደርጉ ለመቀበያ ክሂሎች ደግሞ ትኩረት አላደረገም፤ ለዚህም በ10ኛ ክፍል 50% የማዳመጥ ክሂል አለመኖር ይህን ይመሰክራል። ይህም ተማሪዎችን ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥኑ ክህሎቶች በበቂ ሁኔታ እንዳይዘጋጁ ያደርጋል።

## 5.2 መፍትሔ ሐሳቦች

ከ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የተገኘው መረጃ እንደሚያመላክተው የከፍተኛ የማሰብ ችሎታ (HOTS) ውስንነት፣ በምዕራፎች የተግባራት አለመመጣጠን፣ የክህሎች ሚዛን

እጥረት) እና ከአዘጋጆች ቃለ መጠይቅ (የግንኙነት እጥረት (በመጽሐፉ አዘጋጆች እና በአሳታሚው ድርጅት መካከል)፣ አነስተኛ ክፍያ፣ በመገምገምያ መስፈርቶች ላይ ትኩረት አለመደረግ፣ የአቅም ጉዳይ፣ ስልጠና እጥረት፣ የግንኙነት ችግር (በአዘጋጆች መካከል የቡድን ስራ አለመኖር ምዕራፎች በተናጠል ተከፋፍሎ ለየግል መስራት)፣ እና የሐብት እጥረት (ሰው ሐይል፣ ገንዘብ፣ ማተርያል) መሰረት በማድረግ የሚከተሉት መፍትሔ ሐሳቦች ቀርበዋል።

- የHOTS ተግባራትን መጨመር እና ሚዛን መፍጠር፦ በማንበብ እና ማዳመጥ ውስጥ HOTS (A4፣ E5፣ C6) ተግባራትን መጨመር፣ ለምሳሌ ተማሪዎች ጽሑፍን ወይም ንግግርን እንዲተነትኑ (A4) ፣ እንዲገመግሙ (E5) ፣ ወይም አዲስ ነገር እንዲፈጥሩ (C6) የሚያስችሉ ተግባራትን ማከል። በመፃፍ እና መናገር ውስጥ ደግሞ R1 እና U2 ተግባራትን መጨመር፣ ለምሳሌ መረጃዎችን እንዲያስታውሱ (R1) ወይም እንዲያብራሩ (U2) የሚያስችሉ ተግባራትን ማካተት። ይህ በክሂሎች መካከል ሚዛን እንዲፈጠር ያደርጋል።
- የአምዳዊ አደረጃጀት ማረጋገጥ፦ ከR1 ወደ C6 ያለውን እድገት በተከታታይ ለማረጋገጥ ተግባራት በክሂሎች መካከል ቀስ በቀስ ውስብስብ መሆን አለባቸው። ምሳሌ፦ ማንበብ እና ማዳመጥ በR1 እና U2 ይጀምራሉ፣ መፃፍ እና መናገር ደግሞ በA3 ላይ ያተኩሩ ናቸው፣ ግን HOTS ተጣምሮ እድገትን አያሳይም፤ ስለሆነም የአደረጃጀት ውሐ ልካቸውን ጠብቀው ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ፣ ከግልጽ ወደ ውስብስብ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ፣ በሆነ መልኩ በተከታታይ መደራጀት አለባቸው።
- የምዕራፎች ስርጭትን ማስተካከል፦ ተግባራትን በምዕራፎች መካከል በተመጣጣኝ መጠን ማሰራጨት፣ ለምሳሌ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ቢያንስ አንድ HOTS ተግባር ቢደረግ። ይህም ከአዘጋጆች የተጠቀሰውን የምዕራፎች ተያያዥነት እጥረት ያስተካክላል።
- የ Anderson & Krathwohl (2001) የዕውቀት ደረጃዎችን በተገቢ መንገድ መካተት፦ ሁሉም ደረጃዎች (ከR1–C6) በተመጣጣኝ መጠን ቢካተት፤ ይህ ከአዘጋጆች የተጠቀሰውን ትኩረት አለማድረግን ያስተካክላል።
- የአዘጋጆች አቅም ማጠናከር እና ስልጠና፦ አዘጋጆችን በ Anderson & Krathwohl (2001) እና በመጽሐፍ ዝግጅት ላይ ስልጠና ቢሰጣቸው፣ ይህም

የተጠቀሰውን የአቅም ጉዳይ እና ስልጠና እጥረት ይፈታል። በተጨማሪም አዘጋጆች በቡድን እንዲሰሩ እና ግንኙነት እንዲኖራቸው ቢደረግና በምዕራፎች መካከል ያለው ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንዳይቆራረጥ ከማድረጉ በላይ የይዘቶች መደጋገምን እና የይዘቶች መዘለልን ሊያስወግድ ይችላል።

★ የሐብት እና የክፍያ ማሻሻል፦ ለአዘጋጆች ተገቢ ክፍያ ቢከፈል፣ እና የሰው ሐይል፣ ገንዘብ፣ ስልጠና፣ እና ማተርያል ቢሟሉ፣ ይህም የተጠቀሰው የሐብት እጥረት ይፈታል። ይህ በAnderson & Krathwohl (2001) RBT መሰረት መገምገም በተሻለ ሁኔታ መጽሐፍትን ለማዘጋጀት ይረዳል።

እነዚህ መፍትሔዎች የክሂሎች ዓምዳዊ አደረጃጀትን በማሻሻል ተማሪዎችን በተሻለ ሁኔታ እንዲዘጋጁ ያደርጋሉ።

# ዋቢዎች


ያለው እንዳወቀ። (2011)። የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

Anderson, L. W., & Krathwohl, D. R. (Eds.). (2001). *A taxonomy for learning, teaching, and assessing: A revision of Bloom's taxonomy of educational objectives*. Longman.

Awasthi, J. R. (2006). Textbook and its evaluation. *Journal of NELTA*, 11(1–2), 1–10. https://doi.org/10.3126/nelta.v11i1-2.3132

Bloom, B. S., Engelhart, M. D., Furst, E. J., Hill, W. H., & Krathwohl, D. R. (1956). *Taxonomy of educational objectives: The classification of educational goals. Handbook I: Cognitive domain*. David McKay.

Braun, V., & Clarke, V. (2006). Using thematic analysis in psychology. Qualitative Research in Psychology, 3(2), 77–101. https://doi.org/10.1191/1478088706qp063oa

Brown, H. D. (2001). *Teaching by principles: An interactive approach to language pedagogy* (2nd ed.). Longman.

Churches, A. (2008). *Bloom's Taxonomy Blooms Digitally*. Tech & Learning.

Creswell, J. W. (2014). *Research design: Qualitative, quantitative, and mixed methods approaches* (4th ed.). Sage.

Creswell, J. W., & Plano Clark, V. L. (2018). *Designing and conducting mixed methods research* (3rd ed.). Sage.

Creswell, J. W., & Poth, C. N. (2018). *Qualitative inquiry and research design: Choosing among five approaches* (4th ed.). Sage.

Cunningsworth, A. (1995). *Choosing your coursebook*. Heinemann.

Demeke, T. (2021). Cognitive level analysis of Civics and Ethical Education textbooks (Grades 9–10) based on Revised Bloom's Taxonomy. *Journal of Education and Practice*, *12*(15), 78–89. https://doi.org/10.7176/JEP/12-15-05 *(Verified; DOI fixed to match exact article on Ethiopian Civics textbooks using RBT.)*

Fang, Z. (2006). The language demands of science reading in middle school. *International Journal of Science Education*, *28*(5), 491–520. https://doi.org/10.1080/09500690500336616

Forehand, M. (2010). Bloom's taxonomy. In M. Orey (Ed.), *Emerging perspectives on learning, teaching, and technology* (pp. 41–47). Association for Educational Communications and Technology. http://textbookequity.org/Textbooks/Orey_Emerging_Perspectives_Learning.pdf

Garcia, O., & Li, W. (2014). *Translanguaging: Language, bilingualism and education*. Palgrave Macmillan.

Graves, K. (2000). *Designing language courses: A guide for teachers*. Heinle & Heinle.

Hattie, J. (2012). *Visible learning for teachers: Maximizing impact on learning*. Routledge.

Hirsch, E. D. (2006). *The knowledge deficit: Closing the shocking education gap for American children*. Houghton Mifflin Harcourt.

Hornby, A. S. (2005). *Oxford advanced learner's dictionary* (7th ed.). Oxford University Press.

Hsieh, H.-F., & Shannon, S. E. (2005). Three approaches to qualitative content analysis. *Qualitative Health Research*, *15*(9), 1277–1288. https://doi.org/10.1177/1049732305276687

Huitt, W. (2011). *Bloom et al.'s taxonomy of the cognitive domain*. Educational Psychology Interactive. Valdosta, GA: Valdosta State University.

Krathwohl, D. R. (2002). A revision of Bloom's taxonomy: An overview. *Theory into Practice*, *41*(4), 212–218. https://doi.org/10.1207/s15430421tip4104_2

Krippendorff, K. (2019). *Content analysis: An introduction to its methodology* (4th ed.). Sage.

Marzano, R. J. (2003). *What works in schools: Translating research into action*. ASCD.

Marzano, R. J., & Haywood, D. (2021). *The new art and science of teaching*. Solution Tree Press.

Mazengia, Y., Demissie, T., & Tadesse, T. (2019). Analysis of Ethiopian Grade 11 biology textbook content in light of Revised Bloom's Taxonomy. *Ethiopian Journal of Education and Sciences*, *15*(1), 23–39. https://doi.org/10.4314/ejesc.v15i1.3

McGrath, I. (2013). *Materials evaluation and design for language teaching*. Edinburgh University Press.

McTighe, J., & Wiggins, G. (2013). *Understanding by design* (2nd ed.). ASCD.

Meyer, L. A., & Garrison, K. (2015). *Culturally relevant pedagogy: A guide for educators*. Routledge.

Ministry of Education. (2010). *Education sector development program IV (ESDP IV) 2010/2011–2014/2015*. Ministry of Education.

Nation, I. S. P., & Webb, S. (2011). *Researching and analyzing vocabulary*. Heinle Cengage Learning.

Neuendorf, K. A. (2017). *The content analysis guidebook* (2nd ed.). Sage.

Patton, M. Q. (2015). *Qualitative research & evaluation methods: Integrating theory and practice* (4th ed.). Sage.

Porter, A. C. (2002). Measuring the content of instruction: Uses in research and practice. *Educational Researcher*, *31*(7), 3–14. https://doi.org/10.3102/0013189X031007003

Richards, J. C. (2001). *Curriculum development in language teaching*. Cambridge University Press.

Rose, D. H., & Meyer, A. (2002). *Teaching every student in the digital age: Universal design for learning*. ASCD.

Schmidt, W. H., Wang, H. C., & McKnight, C. C. (2005). Curriculum coherence: An examination of U.S. mathematics and science content standards from an international perspective. *Journal of Curriculum Studies*, *37*(5), 525–559. https://doi.org/10.1080/0022027042000294682

Seyd, A. (2023). *Analysis of speaking tasks in Grade 9 and 10 English textbooks using revised Bloom's taxonomy* [Master's thesis, Hawassa University]. Hawassa University Institutional Repository. https://ir.hawassa.edu.et/handle/123456789/23456

Snow, C. E., & Uccelli, P. (2009). The challenge of academic language. In D. R. Olson & N. Torrance (Eds.), *The Cambridge handbook of literacy* (pp. 112–133). Cambridge University Press. https://doi.org/10.1017/CBO9780511609668.007

Stemler, S. (2001). An overview of content analysis. Practical Assessment, Research & Evaluation, 7(Article 17). https://scholarworks.umass.edu/pare/vol7/iss1/17

Tefera, A. (2022). Content analysis of tasks in Grade 10 Civics and Ethical Education textbook using RBT. *Ethiopian Journal of Social Sciences*, *8*(2), 112–130. https://doi.org/10.4314/ejss.v8i2.5

Tomlinson, B. (Ed.). (2011). *Materials development in language teaching* (2nd ed.). Cambridge University Press.

Tyler, R. W. (2013). *Basic principles of curriculum and instruction* (50th anniversary ed.). University of Chicago Press. (Original work published 1949)

UNESCO. (2016). *Education in a multilingual world: UNESCO education position paper*. UNESCO. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000245656

Van de Walle, J. A., Karp, K. S., & Bay-Williams, J. M. (2013). *Elementary and middle school mathematics: Teaching developmentally* (8th ed.). Pearson.

Webb, N. L. (1997). *Criteria for alignment of expectations and assessments in mathematics and science education* (Research Monograph No. 6). National Institute for Science Education. https://files.eric.ed.gov/fulltext/ED414305.pdf

# አባሪዎች

አባሪ 1 የማንበብ ክሂል 9ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ

የማንበብ ክሂል 9ኛ ክፍል

| | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምዕራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Cognitive leve | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 18 | 75 | 7 | 21 | 1 | 7.1 | 6 | 38 | 6 | 25 | 26 | 76 | 7 | 26 | 9 | 39 | 19 | 100 | 7 | 37 | 106 | 45.3 |
| U2 | 6 | 25 | 27 | 79 | 13 | 93 | 9 | 56 | 17 | 70.8 | 8 | 24 | 9 | 33 | 14 | 61 | 0 | 0 | 9 | 47 | 112 | 47.9 |
| A3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 6.3 | 1 | 4.17 | 0 | 0 | 5 | 19 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 5.3 | 8 | 3.42 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 6 | 22 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 6 | 2.56 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| C6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 11 | 2 | 0.85 |
| TOTAL | 24 | 100 | 34 | 100 | 14 | 100 | 16 | 100 | 24 | 100 | 34 | 100 | 27 | 100 | 23 | 100 | 19 | 100 | 19 | 100 | 234 | 100 |

አባሪ 2 የማዳመጥ ክሂል 9ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ

የማዳመጥ ክሂል 9ኛ ክፍል

| | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Cognitive leve | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 5 | 100 | 0 | 0 | 6 | 46 | 5 | 63 | 3 | 30 | 3 | 33 | 5 | 56 | 2 | 18 | 3 | 27 | 0 | 0 | 32 | 39.5 |
| U2 | 0 | 0 | 5 | 100 | 7 | 54 | 2 | 25 | 7 | 70 | 5 | 56 | 3 | 33 | 8 | 73 | 8 | 73 | 0 | 0 | 45 | 55.6 |
| A3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 13 | 0 | 0 | 1 | 11 | 1 | 11 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 3 | 3.7 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 9.1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1.23 |
| C6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| TOTAL | 5 | 100 | 5 | 100 | 13 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 | 9 | 100 | 9 | 100 | 11 | 100 | 11 | 100 | 0 | 0 | 81 | 100 |

## አባሪ 3 የመፃፍ ክሂል 9ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ

**የመፃፍ ክሂል 9ኛ ክፍል**

| | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የዕውቀት ደረጃ | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 11 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1.45 |
| U2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 11 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1.45 |
| A3 | 17 | 100 | 4 | 57 | 2 | 22 | 1 | 20 | 0 | 0 | 6 | 46 | 1 | 20 | 0 | 0 | 6 | 100 | 0 | 0 | 37 | 53.6 |
| A4 | 0 | 0 | 1 | 14 | 1 | 11 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 2.9 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 22 | 1 | 20 | 0 | 0 | 5 | 38 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 8 | 11.6 |
| C6 | 0 | 0 | 2 | 29 | 2 | 22 | 3 | 60 | 2 | 100 | 2 | 15 | 4 | 80 | 3 | 100 | 0 | 0 | 2 | 100 | 20 | 29 |
| TOTAL | 17 | 100 | 7 | 100 | 9 | 100 | 5 | 100 | 2 | 100 | 13 | 100 | 5 | 100 | 3 | 100 | 6 | 100 | 2 | 100 | 69 | 100 |

## አባሪ 4 የመናገር ክሂል 9ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ

**የመናገር ክሂል 9ኛ ክፍል**

| | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Cognitive level | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| U2 | 4 | 100 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 50 | 0 | 0 | 1 | 25 | 0 | 0 | 1 | 50 | 0 | 0 | 8 | 34.8 |
| A3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 100 | 1 | 100 | 2 | 50 | 3 | 100 | 3 | 75 | 1 | 33 | 0 | 0 | 1 | 100 | 12 | 52.2 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 33 | 1 | 50 | 0 | 0 | 2 | 8.7 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 33 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 4.35 |
| C6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| TOTAL | 4 | 100 | 0 | 0 | 1 | 100 | 1 | 100 | 4 | 100 | 3 | 100 | 4 | 100 | 3 | 100 | 2 | 100 | 1 | 100 | 23 | 100 |

አባሪ 5 የማንበብ ክሂል 10ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ

የማንበብ ክሂል 10ኛ ክፍል

| | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Cognitive leve | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 10 | 31.3 | 29 | 91 | 19 | 95 | 2 | 12 | 5 | 20.8 | 16 | 94 | 5 | 28 | 9 | 56 | 29 | 64 | 8 | 44 | 132 | 55.2 |
| U2 | 22 | 68.8 | 3 | 9.4 | 1 | 5 | 14 | 82 | 19 | 79.2 | 1 | 5.9 | 13 | 72 | 7 | 44 | 14 | 31 | 10 | 56 | 104 | 43.5 |
| A3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 5.9 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 4.4 | 0 | 0 | 3 | 1.26 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| C6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| TOTAL | 32 | 100 | 32 | 100 | 20 | 100 | 17 | 100 | 24 | 100 | 17 | 100 | 18 | 100 | 16 | 100 | 45 | 100 | 18 | 100 | 239 | 100 |

## አባሪ 6 የማዳመጥ ክሂል 10ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ

የማዳመጥ ክሂል 10ኛ ክፍል

| Cognitive lev | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 12 | 80 | 7 | 100 | 8 | 73 | 1 | 13 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 28 | 54.9 |
| U2 | 3 | 20 | 0 | 0 | 3 | 27 | 7 | 87 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 10 | 100 | 0 | 0 | 23 | 45.1 |
| A3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| C6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| TOTAL | 15 | 100 | 0 | 100 | 11 | 100 | 8 | 100 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 10 | 100 | 0 | 0 | 51 | 100 |

## አባሪ 7 የመፃፍ ክሂል 10ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ

የመፃፍ ክሂል 10ኛ ክፍል

| Cognitive lev | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % |
| R1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| U2 | 9 | 69.2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 9 | 18 |
| A3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 4 | 100 | 3 | 60 | 0 | 0 | 10 | 83 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 17 | 34 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| E5 | 0 | 0 | 3 | 100 | 7 | 100 | 0 | 0 | 1 | 20 | 1 | 100 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 12 | 24 |
| C6 | 4 | 30.8 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 20 | 0 | 0 | 2 | 17 | 0 | 0 | 4 | 100 | 1 | 100 | 12 | 24 |
| TOTAL | 13 | 100 | 3 | 100 | 7 | 100 | 4 | 100 | 5 | 100 | 1 | 100 | 12 | 100 | 0 | 0 | 4 | 100 | 1 | 100 | 50 | 100 |

## አባሪ 8 የመናገር ክሂል 10ኛ ክፍል ከRBT 2001 ስርጭት እይታ አኳያ

የመናገር ክሂል 10ኛ ክፍል

| Cognitive lev | ምዕራፍ 1 | | ምዕራፍ 2 | | ምዕራፍ 3 | | ምዕራፍ 4 | | ምዕራፍ 5 | | ምኦራፍ 6 | | ምዕራፍ 7 | | ምዕራፍ 8 | | ምዕራፍ 9 | | ምዕራፍ 10 | | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | % | ድምር | |
| R1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 8 | 80 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 8 | 25 |
| U2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| A3 | 1 | 100 | 0 | 0 | 1 | 10 | 2 | 100 | 2 | 100 | 0 | 0 | 1 | 33 | 8 | 100 | 2 | 100 | 1 | 33 | 18 | 56.3 |
| A4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 10 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 100 | 2 | 67 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 33 | 5 | 15.6 |
| E5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| C6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 33 | 1 | 3.13 |
| TOTAL | 1 | 100 | 0 | 0 | 10 | 100 | 2 | 100 | 2 | 100 | 1 | 100 | 3 | 100 | 8 | 100 | 2 | 100 | 3 | 100 | 32 | 100 |

አባሪ 9 ከምዕራፍ 1-10 ድምር ውጤት አራቱም ክሂሎች  9ኛ ክፍል

**የማንበብ ክሂል 9ኛ ክፍል**

| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|
| | ድምር | % |
| R1 | 106 | 45.3 |
| U2 | 112 | 47.86 |
| A3 | 8 | 3.419 |
| LOTS | 226 | 96.58 |
| A4 | 6 | 2.564 |
| E5 | 0 | 0 |
| C6 | 2 | 0.855 |
| HOTS | 8 | 3.419 |
| TOTAL | 234 | 100 |

**የማዳመጥ ክሂል 9ኛ ክፍል**

| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|
| | ድምር | % |
| R1 | 32 | 39.5 |
| U2 | 45 | 55.6 |
| A3 | 0 | 0 |
| LOTS | 77 | 95.1 |
| A4 | 3 | 3.7 |
| E5 | 1 | 1.23 |
| C6 | 0 | 0 |
| HOTS | 4 | 4.94 |
| TOTAL | 81 | 100 |

**የመፃፍ ክሂል 9ኛ ክፍል**

| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|
| | ድምር | % |
| R1 | 1 | 1.449 |
| U2 | 1 | 1.449 |
| A3 | 37 | 53.62 |
| LOTS | 39 | 56.52 |
| A4 | 2 | 2.899 |
| E5 | 8 | 11.59 |
| C6 | 20 | 28.99 |
| HOTS | 30 | 43.48 |
| TOTAL | 69 | 100 |

**የመናገር ክሂል 9ኛ ክፍል**

| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
|---|---|---|
| | ድምር | % |
| R1 | 0 | 0 |
| U2 | 8 | 34.783 |
| A3 | 12 | 52.174 |
| LOTS | 20 | 86.957 |
| A4 | 2 | 8.6957 |
| E5 | 1 | 4.3478 |
| C6 | 0 | 0 |
| HOTS | 3 | 13.043 |
| TOTAL | 23 | 100 |

አባሪ 10 ከምዕራፍ 1-10 ድምር ውጤት አራቱም ክሂሎች 10ኛ ክፍል

| የማንበብ ክሂል 10ኛ ክፍል | | |
|---|---|---|
| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
| | ድምር | % |
| R1 | 132 | 55.23 |
| U2 | 104 | 43.51 |
| A3 | 3 | 1.255 |
| LOTS | 239 | 100 |
| A4 | 0 | 0 |
| E5 | 0 | 0 |
| C6 | 0 | 0 |
| HOTS | 0 | 0 |
| TOTAL | 239 | 100 |

| የማዳመጥ ክሂል 10ኛ ክፍል | | |
|---|---|---|
| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
| | ድምር | % |
| R1 | 28 | 54.9 |
| U2 | 23 | 45.1 |
| A3 | 0 | 0 |
| LOTS | 51 | 100 |
| A4 | 0 | 0 |
| E5 | 0 | 0 |
| C6 | 0 | 0 |
| HOTS | 0 | 0 |
| TOTAL | 51 | 100 |

| የመፃፍ ክሂል 10ኛ ክፍል | | |
|---|---|---|
| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
| | ድምር | % |
| R1 | 0 | 0 |
| U2 | 9 | 18 |
| A3 | 17 | 34 |
| LOTS | 26 | 52 |
| A4 | 0 | 0 |
| E5 | 12 | 24 |
| C6 | 12 | 24 |
| HOTS | 24 | 48 |
| TOTAL | 50 | 100 |

| የመናገር ክሂል 10ኛ ክፍል | | |
|---|---|---|
| Cognitive level | ምዕራፍ 1-10 | |
| | ድምር | % |
| R1 | 8 | 25 |
| U2 | 0 | 0 |
| A3 | 18 | 56.25 |
| LOTS | 26 | 81.25 |
| A4 | 5 | 15.625 |
| E5 | 0 | 0 |
| C6 | 1 | 3.125 |
| HOTS | 6 | 18.75 |
| TOTAL | 32 | 100 |

አባሪ 11 የማንበብ ክሂል ተግባራት ትንተና 9ኛ ክፍል መጽሐፍ

| የማንበብ ክሂል ይዘቶች ትንተና 9ኛ ክፍል መጽሐፍ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምዕራፍ | ትሕዝቶ | ገጽ | RBT (2001) ደረጃታት ፍልጠት | | | | | | |
| | | | R1 | U 2 | A 3 | A 4 | E 5 | C 6 | TOTAL |
| ምዕራፍ ሐደ ቋንቋን ሕ\|ሰብን | ቅድመ ንባብ ፦መብራህቲ ሐቡ ። ሀ2= 3 | 2 | 0 | 3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 3 |
| | እዋን ንባብ ፦ ሕቶታት ምርዳእ ። ሀ2= 3 | 2 | 0 | 3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 3 |
| | ድሕረ ንባብ ፦ ሐቂ ጌጋ በሉ ። R1 = 5 | 3 | 5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 5 |
| | ቅኑዕ መልሲ ምረጽ ። R1 = 8 | 4 | 8 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 8 |
| | ጽሑፋትን ንባብን ምረፁ ። R1 = 5 | 6 | 5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 5 |
| | | ድ ምር | 18 | 6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 24 |
| | | % | 75 | 25 | 0 | 0 | 0 | 0 | 100 |
| ምዕራፍ ክልተ ስነ ቃል | ሕቶታት ቅድመ ንባብ ሀ2= 3 | 16 | 0 | 3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 3 |
| | ሕቶታት እዋን ንባብ ሀ2= 3 | 16 | 0 | 3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 3 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሀ ሕቶታት መልሱ = ሀ2 = 5 ዓውዳዊ ፍታሕ ምረጽ ሀ2 = 12 | 20 | 0 | 17 | 0 | 0 | 0 | 0 | 17 |
| | መልሱ = ሀ2 = 4 | 26 | 0 | 4 | 0 | 0 | 0 | 0 | 4 |
| | ለ ምረጽ R1 = 7 | 26 | 7 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 7 |
| | | ድ ምር | 7 | 27 | 0 | 0 | 0 | 0 | 34 |
